እንዘ ስወር እምኔነ ይዕዜሰ ክሱተ ኮነ /2/
ተዐምረ ወመንክረ ገብረ መድኃኒነ በቃና
ዘገሊላ
ክብካበ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ /2/

### 211. ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ/2/
ተጠምቀ ሰማያዊ በእደ ሜሬታዊ/2/
አምላክ ሆይ ህዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ
አምላክ ሆይ ህዝቦችህ ዳኑ በልደትህ

### 212.መፅአ ቃል

መፅአ ቃል እምደመና ዘይብል ዘይብል/2/
ዝንቱ ወፅቱ ወልድየ ዘአፈቅር

### 213.በዕደ ዮሐንስ

በዕደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ

ሰሞዊ/5/ ኢየሱስ ናዝራዊ

## 214.ወተመሰሉ

ውተመሰሉ ሰብአ አይን አባግ አላባ ወሜይ
ወጥምቀተ አባይ/2/ ወጥምቀተ አባይ

## 215.ዮሐንስ አጥምቆ

የሐንስ አጥምቆ ለኢየሱስ/2/
በፈለገ ዮርዳኖስ/2/ ፈለገ ርዳኖስ

## 216.ሃዲጎ ተሰአ

ሀዲጎ ተሰአ ወተስአተ ነገድ/2/
እኸ ሜከለ ባህር ቆመ ሜከለ ባህር/2/

## 217.እንዘ ህፃን

እንዘ ህፃን በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/
በዮርዳኖስ/4/ ተጠምቀ በእደ ዮሃንስ/2/

## 218. አማን በአማን

አማን በአማን (2)

መንክር ስብሀተ ጥምቀቱ (2)

እውነት በእውነት (2)

ድንቅ ነው የጌታ ጥምቀት (2)

## 219.መድሃኒነ

መድሃኒነ ተወልደ ነዋ
መድሃኒነ ተጠምቀ ነዋ
ይዕዜኔ በሰላም ንትልዋ

## 220. ውስተ ማህፀነ ድንግል

ወስተ ማህፀነ ድንግል ሀደረ ማህፀነ ድንግል
ሰሜ ወምድር ዘኢያገሞሮ
ሰሜ ወምድር በሜይ ተጠምቀ

## 221.በ30 ክረምት

በ30 ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/
በዮርዳኖስ/4 ተጠምቀ በዮሀንስ

## 222. በወንጌሉያመናችሁ

በወንጌሉ ያመናችሁ
እንኳን ለብርሀነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ

## 223. መፅአለነ

መፅአለነ እኸ መፅአለነ ዘመነ ጥምቀት

ዘመነ ጥምቀት(4) መፅአለነ ዘመነ ጥምቀት

መጣልን እኸ መጣልን የጥምቀት ዘመን

የጥምቀት ዘመን (4) መጣልን የጥምቀ ትዘመን

## 224. አስተርእዮ

አስተርእዮ(2) በሰማይ ኮነ

በሰማይ ኮነ(4) አስተርእዮ በሰማይ ኮነ

ትርጉም፡-በሰማይ መገለጥ ሆነ (ተደረገ)

## 225. እንዘ ሕፃንልህቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ

እንዘ ሕፃንልህቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ

በዮርዳኖስ(2) ዮርዳኖስ(2) ተጠምቀበዮሐንስ

ትርጉም፡- ሕፃንሆኖጥቂትበጥቂቱአደገ፤

በዮርዳኖስወንዝበዮሐንስእጅተጠመቀ

## 226. ነድለ ማየ

ነድለ ማየ ባሕር ከበቦ (2)

ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ፀበቦ (4)

ትርጉም፡- እሳት የባሕሩን

ውሃከበበውባሕሩምየሚሄድበትጨነቀው

## 227. ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ

ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ (2)

በኄኖን በቅሩ በሳሌም (4)

ትርጉም፡- ዮሐንስ

በሳሌምአቅራቢያባለችበኄኖንያጠምቅነበር

## 228. ተጠመቀ

ተጠመቀ ኸህ ኢየሱስ ናዝራዊ (2)

ኢየሱስናዝራዊ (4) ተጠመቀ

## 229. አዳምንያልተወውእንደተሰደደ

አዳምንያልተወውእንደተሰደደ (2)

እሰይየምስራችዛሬተወለደ

እሰይየምስራችዛሬተወለደ (2)

አዳምንያልተወውእንደተጨነቀ (2)

እሰይየምስራችዛሬተጠመቀ

እሰይየምስራችዛሬተጠመቀ(2)

## 230. በትፍስህት ወበሀሴት

በትፍስህት ወበሀሴት

አብእዋቤታ ለታቦት

ትርጉም፡- በደስታናበሀሴትታቦቷንወደቤቷአስገቧት

## 231. ነዓምን በአብ ወነዓምን በወልድ

ነዓምን በአብ ወነዓምን በወልድ (2)

ወነዓምን (4) ነዓምንበመንፈስቅዱስ

እናምናለንበአብእናምናለንበወልድ (2)

እናምናለን (4) እናምናለንበመንፈስቅዱስ

## 232. ዘነቢያት ሰበከዎ

ዘነቢያት ሰበከዎ (2)

ወአስተርዓየገሀደከመሰብ (2)

ትርጉም፡- ነቢያትየሰበኩትሰውሆኖተገለጠ

## 233. በጎል በጎል

በጎል በጎል ሰብዓ ሰገል/2/
በጎል ሰብአ ሰገል ሰገዱለት/2/
ጸሀይ ጸሐይ ጸሀይ ሰረቀ/2/
ጸሀይ ሠረቀ ክርስቶስ ተጠምቀ/2/
አንቺ ዮርዳኖስ ምንኛ ታደልሽ/2/
የእግዚአብሔር ማደሪያ ከላይ
ወርዶብሽ/2/
የዓለም መድሃኒት ተጠመቀብሽ/2/
ድንግል ሚርያም ንጽሀይት ቅድስት/2/
የጌታዬ እናት ምሥጋና ይገባሻል
ከሴቶች ሁሉ አንቺን መርጦሻል
እልል እልል ደስ ይበለን/2/
ወልድ ተወልዶ ነጻ አወጣን
ዮሐንስ አጥምቆ ድልን አገኘን

## 234. ግነዮ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም/2/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/2/
የዓለም ቤዛ ነወና የማህፀንሽ ፍሬ/2/
ብርሃነ ማኅቶት ያደረብሽ አዳራሽ/2/
ቅድስተ ቅዱሳን ሚርያም ድንግል አንቺ
ነሽ/2/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺ ፅንስ
ለደከሞቾች ብርታት ነው ለህመማን ፈውስ/2/
ከሰማይት ሰማት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ/2/
ማኅቶት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ/2/
በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ዕዳችንን ፋቀ/2/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን/2/
እማቢታችን እናታችን ሚርያም/2/ሽ
የተማጸነሽ ይኖራል ለዘለዓለም/2/
ሥጋሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ/2/
በመንግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ

## 235. ዮሐንስኒ

ዮሐንስኒ ያጠምቅ/2/ በሐኖን/5/
በማዕዶተ ዮርዳኖስ
ዮሐንስ ሲያስተምር ያጠምቅ
በጫካ በሜዳ ያጠምቅ
ግምል ፀጉር ለብሶ ያጠምቅ
ሆኖ ምድረ በዳ ያጠምቅ
በሐኖን/4/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ
አምላኩን የሚወድ ያጠምቅ
ብዙ ሰው እያለ ያጠምቅ
ጌታውን ለማጥመቅ ያጠምቅ
ዮሐንስ ታደለ ያጠምቅ
በሐኖን/4/ በማዕዶተ ዮርዳኖስ
ከሃጢያት ተለዩ ያተምቅ
በወሃ ተጠመቁ ያጠምቅ
መንግስተ ሰማይት ያጠምቅ
እንዳለች እወቁ ያጠምቅ

በሐኖን/4/ በሚወርዶት ዮርዳኖስ

## 236. የአለምን በደል

የአለምን በደል_የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላዕክቱን ትቶ
ጽድቅን ለመመስረት በደልን አጥፍቶ
የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ
የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉስ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደ ፈረስ
ባህር ተጨነቀች ጠበባት ሜዳቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሰርት
መጣ በደመና ሠማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት
ባህር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምስጢር
እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ
በዕርግብ ምሳሌነት ክንፉን አሰይፎ

**እሰይ እሰይ**
እሰይ እሰይ ተጠመቀ
እሰይ እሰይ ተወለደ
ከሰማያት ሰማይ ወረደ
ከድንግል ማርያም ተወለደ
በቅዱስ ዮሃንስ ተጠመቀ
እርሱ ባይወለድ // ቸሩ አባታችን //
እርሱ ባይጠመቅ // ቸር አባታችን //
መች ትገኝ ነበር // ገነት ርስታችን //
እንደጠል ወረደ // ከሰማይ ወደኛ
>>
ወገኖቹን ሊያድን >> ከክፉ ቁራኛ
>>
ብርሃን ወጣላቸው >> ለእምነት ወገኖቹ >>
በጨለማው ጉዞ >> እንዳያ ሰሰለቹ >>
እግዚአብሔር አብ ላከ >> አንድያ
ልጁን >>
እርሱም ወደልና >> እንዲሁ ዓለሙን

## 237. ከድንግል ተወልዶ

ከድንግል ተወልዶ እኛን ሊቀድስ
ተጠመቀ ኢየሱስ በባሕረ ዮርዳኖስ

መጥምቁ ዮሐንስ ምንኛ ታደለ
ዮርዳኖስም ሸሽቶ ለምን ኮበለለ

ትንቢቱ ሊፈጸም አስቦ ክርስቶስ
ተጠምቆ አዳነን በባህረ ዮርዳኖስ

ምሥጢረ ሥላሴ ታዩ የዚያን ለታ
በምን ይከፈላል የጥምቀት ውለታ

እመቤቴ ማርያም ምንኛ ታደልሽ
ከአዳም ልጆች ሁሉ አንቺን መረጠሽ

ቸሩ አምላካችን መድኃኔዓለምን
ኑ እናመስግነው በአንድ ላይ ሆነን

## 238. . የሰላሙ መሪ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ/2/
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ/2/

ወለደን በጥምቀት በመንፈስ ዳግመኛ/2/
የንጉሶች ንጉስ የፃድቃን እረኛ/2/

ለመልካሙ ሥራ በእምነት እንበርታ/2/
ከሰይጣን ባርነት ነጻ አወጣን ጌታ/2/

የዛሬው ጥምቀቱ ተነግሮ በአዋጅ/2/
ነጻነት አገኘን በእግዚአብሔር አብ ልጅ/2/

እግዚአብሔር አብ ላከ አንድያ ልጁን/2/
እርሱ ወዷልና እንዲሁ ዓለሙን/2/

## 239. ተጠመቀተጠመቀልን

ተጠመቀተጠመቀልንእኛንሊያድን (4)
ተጠመቀአምላክበዮርዳኖስእኛንሊያድን
ተጠመቀተጠምቆሲወጣእኛንሊያድን
ተጠመቀሰማያትተከፍተውእኛንሊያድን
ተጠመቀከሰማይቃልወጣእኛንሊያድን

ተጠመቀቃሉምእንዲህነበርእኛንሊያድን
ተጠመቀየምወደውልጄእኛንሊያድን
ተጠመቀይሄነውየሚልነውእኛንሊያድን
ተጠመቀአብየነገረለትእኛንሊያድን
ተጠመቀበደመናሆኖእኛንሊያድን
ተጠመቀተጠምቆአዳነንእኛንሊያድን
ተጠመቀከድንግልተወልዶእኛንሊያድን

ተጠመቀእፁብነውድንቅነውእኛንሊያድን

ተጠመቀይገርማልበውኑእኛንሊያድን

ተጠመቀሰማያዊውአምላክእኛንሊያድን

ተጠመቀምድራዊመሆኑእኛንሊያድን

# የሆሳዕና መዝሙራት

## 240. ሆሳዕና እምርት

ሆሳዕና እምርት እንተ አበሳ ዳዊት/2/
በሩክት እን ትመጽእ መንግስት/2/

## 241.እም አፈ ደቂቅ

**እም አፈ ደቂቅ ወሕጻናት አስተዳሎከ ስብሐት/2/**
**በእንተ ጸላኢ/4/ ከመትንሥቶ ለጸላዒ ወለገፋኢ/2/**
**ትርጉም፡- ከህጻት አንደበት ምስጋናን አዘጋጀህ**
**የጠላት ዲያብሎስ ምክሩን ታፈርስ ዘንድ**

## 242. ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም

ሰላምሽ ዛሬ ነው ኢየሩሳሌም
ወደ አንቺ መጥቷልና አምላክ ዘለዓለም/2/
ሆሳዕና በአርያም
እያሉ ዘሙ ህፃናት በኢየሩሳሌም
አንቺ ቤተልሔም የዳዊት ከተማ
የህዝቦችሽ ብርሀን መጣልሽ በግርማ/2/
ሆሳዕና እያሉ አማነጉት
በኢሩሳሌም ያሉት ሕፃናት/2/
ከሩቤል መንበሩን የሚከመት
ማሰቀል ተሸከሞ ሆነ መድሃኒት/2/
የኢያሰሰን ህማም ደናግልም አይተው
እያለቀሱለት ሄዱ ተከትለው/2/

## 243. ሆሳዕና በአርያም

ሆሳዕና በአርያም ሆሳዕና
ሆሳዕና ብለን እናቅርብ ምስጋና
ሆሳዕና በሉ ሆሳዕና
ለወልደ አምላክ //
ትህትናን አሳየን //
ስሙ ይባረክ //
ሆሳዕና በሉ //
ለሰማይ ንጉስ //
ግርማን ለብሶ መጣ //
እኛን ሊቀድስ //
ሆሳዕና በሉ //
ለወልደ ዳዊት //
ነብያት በትንቢት //
ለተናገሩለት //
ሐዋርያት በወንጌል //
ለሰበኩለት //
ሆሳዕና በሉ //
ለአምላክ ምህረት //
ተወልዶ ከድንግል //
እንደ ህጻናት //
እረኞች በዋሻ //
የሰገዱለት //
የአዳም ልጆች ሁሉ //
ደግሞም ማዕከት //

## 244. ሆሳዕና

ሆሳዕና/3/ ለወልደ ዳዊት
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም/2/
ሆሳዕና በይው መጥቷል ወደ ዓለም/2/
በአህያ ላይ ሆኖ ወደ አንቺ የመጣው/2/
አያሰሰ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው
ኃይልና ስልጣን በአንድ ላይ ስላለው/2/
ጠላቶችሽ ፈሩ ህዝብሽም ደስ አለው/2/
በዝባነ አህያ አምላክ ተቀምጦ/2/
አሳየ ለህዝቡ ትህትናውን ገልጦ/2/
እናውቃለን ባዮች ግብዞች ሲቀሩ/2/
ወጣት ሽማግሌ ህፃናት ዘመሩ/2/
ሰውማ ቢዘምር ምን ያስገርማል/2/
ሆሳዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል/2/
ይሁዳ ደመቅሽ በእልልታ ዝማሬ
ያ የክብር ንጉስ መጥቷልና ዛሬ
ቤተመቅደስ ገብቶ የሠላሙ ዳኛ
ይወጡ ብሎ አዘዘ ሌባና ቀማኛ

# የስቅለት መዝሙራት

## 245. እኸ በቀራንዮ

እኸ በቀራንዮ እኸ በፈሰሰው ደምህ / 2/
እኸ በቅዱስ ስምህ ጌታ ሆይ ሚሮን እባክህ

## 246. ፍቅር ሰሃቦ

ፍቅር ሰሃቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ/2/
ወአብፅአ/3/ እከለሞት

## 247. ስለእኛ ብሎ

ስለእኛ ብሎ ልጅሽ ተሰቅሎ
ልብሽ በሃዘን ተወግቶ ቆስሎ/2/

ከማቀሉ አወርደውት
በአንቺ ደረት ደግፈውት
ያለቀሸው የእንባሽ ብዛት
ይጠብቅልን የእኛን ሀጢያት/2/

## 248. የአብርሃም አምላክ

የአብርሃም አምላክ የይስሃቅም ቤዛ/2/
ወገኖቹን ሁሉ በራሱ ደም ገዛ/2/
የሃሰት ምስክር አቁመው ከሰሱት/2/
በሞት እንዲቀጣ ሁሉም ፈረዱበት/2/
ጲላጦስ ገረፈው በሰንሰለት አስሮ/2/
ከሮማዊው መንግስት እንዲኖር ተፋቅሮ/2/
ድንግል አልቻለችም እምባዋን ልትገታ/2/
እያየች በማቀል ልጇ ሲንገላታ/2/
በብርሃን ዙፋን ላይ የቆመት እግሮቹ
በችንካር ላይ ቆሙ ምንም ሳይሰለቹ/2/
የብርሃን አክሊልን ለሰሜኔታት የደለ/2/
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀራንዮ ዋለ/2/

## 249. ወደደን ያለ ልክ

እርሱ ፃድቅ ሲሆን ፍፁም <u>ቡሩክ አምላክ/2/</u>
በማቀል ተሰቅሎ <u>ወደደን ያለልክ/2/</u>
ስለበደላችን ለእኛ ተሰቀለ
በሥጋው ታመመ ግፍን ተቀበለ
በሲኦል እስራት ለተጎሳቆሉት
ሰላምን አደለ ሆናቸው ደህነት
ወህኒ የነበሩ የታሰሩ ነፍሳት
በማቀል ተሰብሯል የእጃቸው ሰንሰለት
        የሲኦል አበጋዝ ያኔ ግራ ገባው
        ሞትን ቢያሸንፈው በማቀል የሞተው
        በፍጡራን ችንካር ሲቸነከር ቢያየው
        ዲያብሎስ ታለለ ፍጡሬ ማሰሎ ታየው
ይሄ ማን ነው አለ የሞት ሃይል ያልያዘው
በሃይለ ሥልጣኑ ፍጥረት የሚዛዘው
ይሄ ማን ነው አለ ምርኮዬን የቀማኝ
መንግስቴን የሻረ የሚያንቀጠቅጠኝ

## 250. ጌታ ሆይ

ጌታ ሆይ አይሁድ አሜኔያን ሰቀሉህ ወይ
ዓለም መድሃኒት የዓለም ሲሳይ ሰቀሉህ
ወይ/2/
የአዳም በደል አደረሰህ አንተን ለማቀል
የሔዋን ስህተት አበቃህ ለሞት ቸሩ አባት/2/
ንጹህ ክርስቶስ ሆንክ በደለኛ ብለህ ስለእኛ
ማቀል አሸከመው አስረው ገረፉህ
እያዳፉህ/2/
እጅና እግርህ በሚስማር ተመታ የዓለም ጌታ
የሾህ አክሊል ደፍተህ ጎንህን ተወጋህ አልፋ
ኦሜጋ/2/
ግብዞች እንደ ራሳቸው ማሰለኣቸው
ምራቅ እየተፉ በፊትህ ቀለዱ አንተን
ሊጎዱ/2/
በማቀል ላይ ተጠማሁ ስትል ታላቅ በደል
ሃሞትና ከርቤ ሰጡሀ ቀላቅለው ጠጣ ብለው/2/
ይቅር ባይ ግልፅ በደላችን ሁሉን ሳታይ
አንተ ይቅር በለን በእኛ ሳትከፋ
እንዳንጠፋ<u>/2/</u>

## 251.የሃሰት ዳኝነት

እወነት ስለሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዋለ በአደባባይ ሲሰደብ ሲከሰስ
የሃሰት ዳኝነት አምላክን ወቀሰው
ህይወት ሰጠን እንጂ ጥፋቱ ምንድነው
ከቃሉ እብለትን ባያገኙበትም
ዝምታወን ቢያዩ አላዘኑለትም
ባላወቁት ማጠን ጠሉት ካለበደል
ጥፋቱ ምን ይሆን የሚያደርስ ከማቀል/2/
        የልቡን ትህትና ፍቅሩን ሳያስተውሉ
        ቸሩ ጌታችንን አቻኩለው ሰቀሉት
        ሩህሩሁን ጌታ አቻኩለው ሰቀሉት
        ሞትን አስወግዶ ቢሰጣቸው ህይወት/2/
ስለቸርነቱ ስድብን ከፈሉት
ስለርህራሄው የሾህ አክሊል ሰጡት
ሃሞትና ከርቤ ሆምጣጤ ደባልቀው
ሜራር አስጎነጩት ጨክነው ልባቸው/2/
        ፈወስን ለሰጣቸው ልባወን ሞልተው
        አሉት ወንበዴ ነው ስቀለው ስቀለው
        ከእጁ በረከትን የተሻሙ ሁሉ
        ይጮሁ ነበረ ይገደል እያሉ/2/

## 252. እስመ ለዓለም ምህረቱ

እስመ ለዓለም ምህረቱ/2/
አያልቅም ብዙ ነው የአምላክ ቸርነቱ
አመስግኑት ጌታን ሁላችሁ በአንድነት
መሃሪ ነውና ለሰው ልጆች ህይወት
እስመ ለዓለም ምህረቱ/2/
የሚይሞተው ሞቶ የተቀበረው
ከገሃም እሳት እኛን ሊያድነን ነው
እስመ ለዓለም ምህረቱ/2/
ከማርያም የነሳው ያ ቅዱስ ስጋው
ቀራንዮ ሲወል የሚያሳዝን ነው
እስመ ለዓለም ምህረቱ/2/
በፈጠረው ፍጥረት እጅግ ተሰቃይቶ
ነፍሳትን አወጣ ከሲኦል ጎትቶ

## 253. ሞተሃልና ስለ እኔ

ሞተሃልና ስኔ ምንም ሳይኖርብህ ጥፋት
ተከሰህ ተወቀስክ በጲላጦስ ፊት
ኢየሱስ አምላከ ምህረት ስብሃት ለከ
የአንተ መንገላታት ሁልጊዜ ያሳዝኛል ሲወራ
በማቀል ላይ ሆነህ የየኸው መከራ
ኢየሱስ የህይወት እንጀራ ስብሃት ለከ
ከልዑል ቦታ ዝቅ ብለህ ፈጣሬ ፍጡራን
አምላክ
በሰው ፊት ተዋርደህ ስለ ሰው የሞትክ

በማስቀል ላይ ተጠምሁ እያልክ ስብሃተ ለከ
ክፉ አድራጊዎች ተነስተው በምቀኝነት ማንፈስ
ብዙ ሲጣጡ ለደምህ መፍሰስ
ሞትከላቸው ደስ እንዲላቸው ስብሃተ ለከ
መሀሪ ጌታ አሁንም አንደ ቸርነትህ ብዛት
የእኛን በደል ሁሉ ሳትማለከት
አድነን ከዳግም ሞት ስብሃት ለከ

## 254. አዳምን ሲያወጣው

አዳምን ሲያወጣው ከገሃነም ቀንበር
በጌቴ ሰሜ /2/ ጸሎት አርጎ ነበር
ኢየሱስ በዚያች ማስቀል ላይ በቀራንዮ
ምህረት ለማ ለጠላቶቹ እንዲህ እያለ
የማያወቁትን በሚድረጋቸው
አባት ሆይ አንተ ይቅር በላቸው/2/
ይህች ፅዋ ትለፍ አባት ሆ ቢቻልህ
ደግሞም ባይቻልህ የአንተ ፈቃድ ትድረስ
ለእኛ ወገኖህ ሀጢያት ላደከማን
ማስቀልህ ጥላ /2/ ሚፈያ ትሁነን

## 255. በጌቴ ሰማኔ

በጌቴ ሰሜ በአታክልቱ ቦታ/2/
ለእኛ ሲል ጌታችን በዓለም ተንገላታ/2/
አዳምና ሄዋን ባጠፉት ጥፋት/2/
ለእኛም ደረሰብን የዘላላም ሞት/2/
ማስቀል ተሸከሞ ሲወጣ ተራራ/2/
ይገርፉት ነበረ ሁሉም በየተራ/2/
ድንግል አልቻለችም እንባዋን ልትገታ
እያየች በማስቀል ልጇ ሲንገላታ

## 256. አለምን ለማዳን

አለምን ለማዳን የተሰቀለው
ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው/2/
ጌታችን ተሰቅሎ ቢያዩት ማለዕከት
በዝማሬ ፈንታ አለቀሰሉለት
ሚከኤል ዝ አለ ገብርኤል ገረመው
አምላኩ እርቃኑን ተሰቅሎ ስላየው/2/
ነፍሱን ለወዳጁ የሚሰጥ ቢገኝም
ለጠላቱ የሚሞት በጭራሽ አይኖርም
ጠላቶቹ ሳለን ለእኛ የሞተው
ክርቶስ ልዩ ነው ወደር የሌለው/2/
ዕወርን ቢያበራ የሞተ ቢያስነሳ
በመማስገን ፈንታ ሆነ ማዛበቻ
ሰማያዊው ዳኛ ሊፈረድበት
ተከሶ ቀረበ በጲላጦስ ፊት
በጸሎተ ሐሙስ ዕለት እራት የሆነው
አርብ በማስቀል ላይ የተሰቀለው
ፍቅር አስገድዶት ለእኛ የሞተው
ሚልካሙ እረኛችን መድሃኔዓለም
ነው/2/

## 257. የመስቀሉ ፍቅር ቢገባን

የማስቀሉ ፍቅር ቢገባን/4/ እማቤታችንን
እንወዳታልን
የማስቀሉ ፍቅር የገባቸው/4/ እማቤታችን
አለች ከጎናቸው
አባ ህርቆያስ አባታችን የማስቀሉ ፍቅር
ቢገባው
ልቤ አፈለቀ አለ ሚልካም ነገር ከእማቤቴ ጋራ
ሊነጋገር/2/
የማስቀሉ ነገር ቢገባን/2/ እማቤታችንን
እናያታለን
ነይ ነይ እምዬ ሚርያም ነይ ነይ ቤዛዊት
ዓለም/2
ለመናኔው ጸሎት ልዩ እጣን
የዋሻ ሻማ ነሽ እመብርሃን
መኣዛሽ ሸተተኝ ከግሸን
ትናፍቂኛለሽ ምን ልሁን/2/
የማስቀሉ ፍቅር ቢገባን/4/ እማቤታችንን
እንወዳታልን
ዳዊት በማዝሙሩ የነሳሻል
የያዕቆብ ድንኳን ነሽ ይልሻል
የእግዚአብሔር ሀገር የሚሉሽ
እማቤቴ ሚርያም አንቺ ነሽ / 2/
ቤተልሔም ስሔድ አይሻለሁ
ቀራንዬ ስሔድ አይሻለሁ
ፍጹም አትለይም ከልጅሽ
አንቺስ ልዩ ነው ፍቅርሽ/2/
የማስቀሉ ፍቅር ቢገባን/4/ እማቤታችንን
እናያታለን
ነይ ነይ እምዬ ሚርያም ነይ ነይ ቤዛዊት
ዓለም/2/

## 258. ኢየሱስም አለ

ኢየሱስም አለ ሐዋርያትን ጠርቶ
ስርዓት ሊያስተምራቸው ከሁሉ ለይቶ
ይህን የአዲስ ኪዳን የፍቅር ስጦታ
ታላቅ ሥንስለት እጅግ የበረታ
ስጋዬንም ብሉ ደሜንም ጠጡት
ስለሚሰጣችሁ የእውነት ህይወት
ሂዱና አዘጋጁ የፋሲካን ማዕድ
ይገባዋልና ንጹህ በግ ሊታረድ
ደቀ ማዛሞቹ ጴጥሮስና ዮሐንስ
በፍጥነት ተጓዙ እከተማው ድረስ
አዩና ሚድጋ የተሸከመ ሰው
ከተማ ሲደርሱ ሄዱ ተከትለው
እጅግ ተደሰተ የቤቱ ባለቤት
ጌታው በአዳራሹ ስለተገኘለት
ሰዓቱ ሲደርስ የተወሰነለት
ከማኣድ ሊቀመጥ ተገኘ ከዚያ ቤት
የቤቱ ባለቤት እጅግ የታደለው
ስምኦን ነበር ጌታን የጋበዘው
እጅግ እመኝ ነበር ከማከራ በፊት
ከዐመድ ልቀመጥ ከእናንተ ጋር በእውነት
የእግዚአብሔር መንግስት እስከትመጣ ድረስ
ከወይኑም አልጠጣም ከማኣዱም አልቀምስ
ህብስቱንም ቆርሶ ባርኮ አደላቸው
ስለ እናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ይሔ ነው

ወይኑንም ባርኮ አንስቶ ሠጣቸው
ስለ እናንተ የሚፈስ ደሜ ነው
አላቸው
ይህን የአዲስ ኪዳን የፍቅር ስጦታ
ታላቅ ሠንሠለት ነው እጅግ የበረታ
ስጋዬንም ብሉት ደሜንም ጠጡት
ስለሚሰጣችሁ የእውነት ህይወት
መዝሙሮም ዘምሩ እጅግ የተዋበ
ጌታም እግር ሊያጥብ ውሃን አቀረበ
ጴጥሮስ ግን ፈፅሞ አታጥበንም አለ
ትሁት ነበርና እየተቻከለ
እግርህን ካሳጠበኩ ዛሬ በዚህ ምሽት
ዕጣ ክፍል የለህም ከእኔ ጋር
በእውነት
እንዲህ ባለው ጊዜ ጴጥሮስ ደነገጠ
መላ ሠውነቱን ለማታጠብ ሰጠ
እኔ ጌታ ስሆን አምላክ የምከብር
እግራችሁን ሳጥብ ስኖር ከእናንተ ጋር
ይህንን ምሳሌ ተከተሉ በፍቅር
የእኔ ስጦታ ነው በትህትና መኖር

# የትንሳኤ መዝሙራት

### 259. ወምድረኒ

ወምድርኒ ተገብር ፋሲካ / ምድር ፀዳች
ሀሴት አደረገች/
ተሀፂባ በደመ ክርስቶስ /
በክርስቶስ ደም ታጠበች/

### 260. አማን በአማን

**አማን በአማን/4/**
**ተንሥአ እምነ ሙታን/2/**
**እውነት በእውነት/2/**
**ተነሣ ዛሬ ከሙታን**
**ተነሣ የኣለም መድኃኒት**

### 261.በትንሣኤከ

**በትንሣኤከ እግዚኦ ተዘከረነ**
**እመ ትመጽእ በመንግሥትከ**
**ምስለ ከሎሙ ቅዱሳኒከ**
**ወምስለ አዕላፍ መላዕክትከ**

**ትርጉም፡ – ከቅዱሳንህ ሁሉ ጋር ከአዕላፍ**
**መላዕክትህ ጋር በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ**
**አቤቱ በትንሣኤህ አስበን፡፡**

### 262. ሰላም ሰላም

**ሰላም ሰላም/2/**
**እኸ እምይእዜሰ ይኩን ሰላም/2/**
**ሰላም ሰላም/2/**
**እኸ እንግዲህስ ይሁን ሰላም/2/**

### 263. ኃይለ ጽልመት ተሰደ

**ኃይለ ጽልመት ተሰደ/4/**
**በሰንበት ኃይለ ጽልመት ተሰደ/4/**
**ተስፋ ሕይወት ተሰርዐ/4/**
**በሰሞኖት ተስፋ ሕይወት ተሰርዐ/4/**

### 264. እም እቶነ እሳት

**እም እቶነ እሳት ዘይነድድ አንገፈነ/2/**
**ብርሃናተ ዘይትአጸፍ ተንሥአ ለነ/4/**
**ከሚነደው እሳት ከነበልባሉ አውጣን/2/**
**ብርሃናትን ተጎናጽ ፎ ተነሳልን/4/**

### 265. ተገርፎ ተሰቅሎ

**ተገርፎ ተሰቅሎ የሞተው አንበሳ**
**ተገንዞ በጨርቅ ተቀብሮ እንደ ሬሳ**
**በሞት እጅ ተይዞ አልቀረም ተነሣ/2/**
**እናምናለን ትንሣኤህን**
**በሥልጣንህ መነሣትህን**
**አርአያ ነወና ለሁላችን**
**ሐሮድስ ፈልጎ ተቀብሮ እንዲቀር**
**በመቃብሩ ዙሪያ ጭፍሮቹን ቢያሰፍር**
**ምድር አልቻለችም ትንሣኤን ልታስቀር/2/**
**ክርስቶስ ስትነሣ ከህቱም መቃብሩ**
**ትንሣኤህን ደፍረው ተናገሩ**
**እንሞታለን ብለው ማንንም**
**ሳይፈሩ/2/**
**እንግዲህ አልፈራም ሞትና ኩነኔ**
**አምላክ ከሞተልኝ ተሰቅሎ ስለእኔ**
**ተደምስሶአልና የሞት ሥልጣኔ/2/**

### 266. አማኑኤል አምላክ

አማኑኤል አምላክ ምስጋና ይገባሃል
ለአዳም ልጆች ሁሉ ህይወትን ሰጥተሃል
እልልታ ይገባል ለታላቁ ጌታ
ምህረትን ለሰጠን በሀጢያታች ፋንታ
እንደ ምስኪን ደሃ አንገቱን ቀልሶ እሰይ
የምስራች
ምህረት ላረገልን እንባችን አብሶ እሰይ
የምስራች
ከባርነት ቀንበር ፍፁም ነፃ አወጣን
ደስ ይለናል በአንተ በትንሳኤው ብርሃን
ከለሜዳ ለብሶ ዕርቃኑን የቆመው
የእኛ መድሃኔኣለም ሞትን ድርል አረገ
ጨፈቃና ከዋክብት ደም ያለቀሱለት
ሞትን ድል ለነሳው እናመስግን
በእውነት
መግደላዊት ማርያም በጣም ደስ ይበልሽ
አምላክሽ ተነስቷል ከሃጢያት ሊያነፃሽ
እናንተ ሃዋርያት በእምነት የፀናችሁ
ፍራቻ ይወገድ ተነስቷል ጌታችን

ንገሩ ለዓለም ያረገላችሁን
ከሲኦል እስራት ያላቀቃችሁን
እሰይ የምስራች ሰይጣን ድል ------
-
ዝማሬን እናቅርብ ሁላችን--------

## 267. እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይ የምስራች ደስ ይበለን
ሞትን አሸንፎ ተነሳልን
በሞቱ የእኛን ሞት አጠፋልን
ሲኦል ባዶ ሆነች ዘንዶው ድል ተመታ
ሞትን በሞት ሽሮ የትንሳኤው ጌታ
እንባችን ታብሰ አገኘን ነፃነት
ከሲኦል እስራት ወጣን ከባርነት
ቁልፎቿ ሲወድቁ የሲኦል መዝጊያዋ
ከዘፋኑ ሲወርድ ዲያብሎስ ጌታዋ
አርነት ስንወጣ በጌታ ትንሳኤ
በዕልልታ ደመቀ የሰማዩ ጉባኤ
የሞታችን መውጊያው ተሰበረ ቀስቱ
ጥልም በማስቀሉ ፈረሰ በሞቱ
የትንሳኤው ብርሃን ወጣ በላያችን
አምላክ መድሃኔዓለም ሲነሳ ጌታችን
እንደ ህልም አለፈ የከንቱ ዘመን
ዲያብሎስን አስሮ አሳየን ብርሃን
ሞትና መከራ ከእኛ ተወግዷል
መቅበዝበዙ ቀርቶ ክብርን
አቀዳጅቶናል

## 268. ሞትን ድል አድርጎ ተነሳ

ሞትን ድል አድጎ ተነሳ ክርስቶስ ተነሳ
እሰይ/2/
እኛንም ከሞት ሊያስነሳ/2/ ክርስቶስ ከሙታን
ተነሳ
ሰላም/3/ ለሰው ልጆች በምድር ሆነ
ሰላም/2/
ነፍሳትን ነፃ አወጣ ከጨለማ ኑሮ እሰይ /2/
የሲኦልን በር ሰብሮ/2/ ሃይሉንም በሃይሉ
ሽሮ
ሰላም/3/ ለሰው ልጆች በምድር ሆነ
ሰላም/2/
ሞት በትንሳኤ ተሻረ የሰው ልጅ ከበረ
እሰይ/2/
ጠላት ዲያብሎስ አፈረ/2/ እጅና እግሩንም
ታሰረ
ሰላም/3/ ለሰው ልጆች በምድር ሆነ
ሰላም/2/
እንዳይኖር ለዘላለም ሞት በአዳም ላይ ነግሶ
እሰይ/2/
ክርስቶስ ተነሳ ሞትን ደምስሶ/2/ ግርማ
ማለኮቱን ለብሶ
ሰላም/3/ ለሰው ልጆች በምድር ሆነ
ሰላም/2/

## 269. ዘምሩ ለአምላክ ዘምሩ

ዘምሩ ለአምላክ ዘምሩ ተነስቷል በሚያስደንቅ
ክብሩ
የትንሳኤውን ዜና ለአለም ንገሩ
ሞት ሆይ መውጊያህ የታል ሃያልነትህ
ዛሬ ድል ነስቶሃል ተገልጦ ጌታህ
መቃብሩን ሳይከፍት መግነዝ ሳይፈታ
በግርማ ተነሳ የሰራዊት ጌታ
በሞት አገር ላለን ብርሃን ወጣለን
ነፃነት ታወጀ ቀንበር ወለቀልን
የዕዳ ፅኅፈታችን ከመንገድ ተነሳ
በአንዱ በእግዚአብሄር ልጅ በይሁዳው
አንበሳ
ማለከትን ንፉ ትንሳኤውን አወሩ
በቅኔ ማህሌት ካኅናት ዘምሩ
ነጭ ልብስ ለብሰናል ለነፃነታችን
እንደተናገረው ተነስቷል ጌታችን
ድል መንሳት ሊሰጠን ሞትን አሸነፈ
ድቅድቁ ጨለማ በእርሱ ተገፈፈ
ላንቀላፉት ሁሉ በኩራት ሆኖ ጌታ
ጠላቶቹን ሁሉ በኋላቸው መታ

## 270. እልል በሉ

እልል በሉ በአንድነት ዘምሩ
አመስግኑ ለክብሩ ዘምሩለት
እንደ እግዚአብሄር ያለ ማንም የለም በሉ
ከሃጢያት ባርነት ስንኖር ተገዝተን
ከቤቱ ስንርቅ ትዕዛዙን አፍርሰን
አይቶ ዝም ላለን ጠላቶቹ ስንሆን
ወለታው ግሩም ነው ክብር ለእርሱ
ይሁን/2/
ራሱን አዋርዶ እኛን አከበረን
ሥጋወና ደሙን ብሉ ጠጡ አለን
ሚልካም እረኛ ነው የሚያሳጣን የለም
ምስጋና ይድረሰው ለመድሃኔዓለም/2/
ህይወቱን የሰዋ እንደ አምላክ ማን አለ
ለሰው ልጆች ብሎ በመስቀል የዋለ
ፍቅሩ የማይለካ አያልቅም ቢወራ
ከሰማያት ወርዶ ሆነ ከእኛ ጋራ/2/
ሥራውን እናድንቅ እንዲህ ለወደደን
በማያልቀው ፍቅሩ በረከት ላደለን
ለማይነገረው ለአምላክ ስጦታ
ውዳሴን እናቅርብ እንዘምር በዕልልታ/2/

## 271. ጌታ ተነስቷል

ጌታ ተነስቷል እልል እልል በሉ
አምላክ ተነስቷል የምስራች በሉ
ሞትና መቃብርን በኃይሉ አጥፍቶ
ሁላችን አየነው ክርስቶስ ተነስቶ
አዳምን ለማዳን ቃል ኪዳን ገብቶለት
ዘመኑን ጠብቆ ካሣ ሊከፍልለት
ከሰማያት ወርዶ የተሰቀለው
ሞትን በሞት ሽሮ ይኸው አየነው
ደቀ መዛሙርቱ እጅጉን ተጨንቀው
በጌታቸው ሞት በኃዘን ተመተው

በተዘጋ ደጃፍ ተሰብስበው ሳለ
እጆቹን ዘርግቶ ሰላም ለእናንተ አለ
ማርያም መግደላዊት እየገሰገሰች
በሌሊት ተነስታ ወደ አምላኳ ሄደች
አይሁድ አንገላተው የሰቀሉት ጌታ
ተነስቶ አግኝታው ተመላች በደስታ

### 272. ተነሳልን

**ተነሳልን/2/ ህዝብ ሆይ ደስ ይበለን**
ኃያል አምላክ ኃያል ጌታ ሞትን ረታልን
ተነሳልን እልል እልል እንበል

ተነሳልን ወገኖች ዘምሩ
>> ሞትን ለሻረልን
>> በመስቀል ተሰቅሎ
>> ሕይወቱን ለሰጠን
>> ሰዎች ዝም አንበል
>> እናመስገን በእውነት
>> ከኃጢአት ላዳነን
>> ወረት ለሌበት

ተነሳልን ጴጥሮስ ገሰገሰ
>> ከመቃብሩ ሥፍራ
>> ጌታ ግን ተነስቷል
>> የለም በዚያ ቦታ
>> ሰዎች ደስ ይበለን
>> ሞትን ለረታልን
>> በመስቀል ላይ ሆኖ
>> ከእስራት ለፈታን
ተነሳልን ስያውሩ ስለአንተ
>> እነቀለዮጳ
>> ስለፍቅራቸውም
>> መሃላቸው ገባህ
>> ማሕዱንም ባርከህ
>> ተገለጽክላቸው
>> ሞትን የሚረታ
>> እንደአንተ ያለ ማን ነው
>> ሕይወትን የሚሰጥ
>> እንደ አንተ ያለ ማ ነው
>> ተአምርን የሚያደርግ
>> እንደ አንተ ያለ ማን ነው
>> ከሞት የሚያወጣን
>> አንደ አንተ ያለ ማን ነው

# የዕርገት መዝሙራት

### 273. አምላካችን አረገ

አምላካችን አረገ/2/ ወደ ሰማየት
የሰማይ መላዕክት በክብር እያጀቡት

### 274. ይቤሎሙ ኢየሱስ

**ይቤሎሙ ኢየሱስ ለአርዳኢሁ ኢየሱስ ይቤሎሙ/2/
ሰማይ አዓርግ ኀበ አቡየ ወአቡክሙ/2/
ትርጉም፦ - ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወደ ሰማይ ወደ አባቴ ወደ አባታችሁ አርጋለሁ አላቸው፡፡**

### 275. ዐረገ በስብሀት

**ዐረገ በስብሀት ዐረገ በእልልታ
በስብሀት በዕልልታ ዐረገ/2/ በእልልታ
ሞትን ድል አድርጎ የሰራዊት ጌታ
ዐረገ/2/ በዕልልታ**

# የጰራቅሊጦስ መዝሙራት

### 276. አንተሙሰ ንበሩ

አንተሙሰ ንበሩ ሀገረ ኢየሩሳሌም
እስከትለብሱ ሀይል እምአርያም

### 277. መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ ወረደ ለዕለ ሃዋርያት
ተመሲሎ/5/ በነደ እሳት

### 278. ሀይሉን እንድትለብሱ

ሃይሉን አንደትለብሱ ክብሩን እንድታዩ
በኢየሩሳሌም/2/ በመቅደሱ ቆዩ
በማሪያም ቤት በኢየሩሳሌም
ሲጠበቁ ሃይልን ከአርያም
መንፈስ ቅዱስ ከሰማየት መጥቶ
ክብር ሆናቸው ዕወቀት ጥበብ ሰጥቶ
መላዕክቱ በሰረጋላቸው
አጥረዋታል በእሳት ሰይፋቸው
ቃልኪዳኗን ደጆቿን አትርሱ
በበጉ ደም እንድትቀደሱ
ፈሪዎቹ ደፋሮች ሆነዋል
ቋንቋ ጥበብ ፀጋን አግኝተዋል
የፀኑባት የሞቱላት ሁሉ
ዛሬ በክብር በገነት ወስጥ አሉ
በክርስቶስ ደም ላይ ተመሰርታ
በልጆቿ ሰሜትነት ጸንታ
ትኖራለች በክብር በዝና
መሰረቷ የፀና ነወና

# የምጽአት መዝሙራት

### 279. አንድ ቀን አለ

አንድ ቀን አለ የሚያስፈራ ለፃድቃን
የሚያበራ/2/

ጌታ በዚያች ቀን ይመጣል በክብርም
ይገለጣል/2/
አብረው ከእርሱ ጋር ይመጣሉ ቅዱሳን መላዕክት
ሁሉ/2/
ጌታ በዚያች ቀን ይመጣል በዙፋን
ይቀመጣል/2/
የምህረት አዋጅ ይጠበቃል ነፍስ ሁሉ
ይጨነቃል/2/
ኃጥአን በሞት ያለቅሳሉ በግራው ይቆማሉ/2/
ቅዱስ ቃሉን ሰምተው ያመኑ የጸኑ በኪዳኑ/2/
አብረው በቀኙ ይቆማሉ ከሃዘን ይሰወራሉ/2/
መሃሪ ጌታ ፈጣሪያችን ይድረስህ
ልመናችን/2/
በዚያች ግሩም ቀን እባክህ አቁመኝ
ከጎንህ/2/

## 280. ምሳሌው ደረሰ

ምሳሌው ደረሰ አምላከ ምህረት/2/
ፍሬው ከገላባ የሚለይበት/2/
ክብርን ተጎናጽፎ ዳግመኛ ሲመጣ/2/
ፃድቃንን ለመሾም ኃጥአንን ሊቀጣ/2/
ለአብርሃም ለይስሃቅ የሰጠኸውን/2/
ዛሬም ለህዝቦችህ ስጠን ሰላምን
ዛሬም ለህዝቦችህ ስጠን ህይወትን/2/

## 281.በመጨረሻ

**በመጨረሻውእንነሳለን ከሞትን/2/**
**ጌታሲመጣበአየር ሆነን እያየን/2/**
ብርሃን ነውለሚኖሩ ይህ ክብር
የሚኖፈቅ ነውበልቦናቸውየሚኖር
የስንዴቅንጣት ትንሳኤ ከአላት በምድር
ተስፋ አለን እኛ በሰማይ አገር ልንኖር
ፀሐይ ስትጨልምከዋከብትምሲረግፉ
ምድርና ሞላዋ ለዘለዓለምሲያልፉ
በሰማይ ኃይላት ንወፅወፅታ ሲሰማ
ጌታ ይመጣል በማኮቱ ግርማ
እልፍ አእላፋት መላእክቱ ሲታዩ
ብርሃን ሲሞላ ምድርና ሰማዩ
የምድር ዳርቻ በንፋስ ሀይል ሲመታ
ከጫፃቅ አድነን አማኑኤል የኛ ጌታ
ለሚታመኑ በሀይማኖት ለፀኑ
ይታያል በግልጽ የጌታችን ማዳኑ
በምድር እያሉ ኃጢአትን ለሚሰሩ
ያስደነግጣል ያስፈራቸዋል ክብሩ
ጌታ በዚያን ቀን እንዳንጣል በሲኦል
ቅዱስ ስምህን ይዘናል ተማፅነናል
በበደላችን እንዳትከፍለን አደራ
እንደ ሞገምነውጌታሆይ የኛ ስራ

## 282. ጸንተን እንጠብቀው

ከመላዕክት ጋራ ሲገለፅ በሰማይ
ጸንተን እንጠብቀው ክብሩን ሁሉ እንድናይ
በግርማ ሲመጣ በአስደንጋጭ ሁኔታ
ወዮልሽ ነፍሴ ሆይ ወየው የዛን ለታ
እኽ ምስጋና ይድረስህ ሁል ጊዜ ጠዋት ማታ
ሃሌ ሃሌ ሉያ የሰራዊት ጌታ
ሰማዩና ምድር ከፊቱ ሲሸሹ
መግቢያ አጥቶ ይጮሃል ትልቁ ትንሹ
ፃድቃን ሲደሰቱ በሃጥአን ፋንታ
ሆኖ ጠበቃቸው ለቅሶና ዋይታ
ሰለሚይታወቅ አምላክ አመጣጥህ
በመንፈስህ አፅናን ጸንተን እንጠበቅህ
ሰይጣን እንዳይገዛን በመንግስትህ ቦታ
እግዚኦ ከልለን ከዚህ ዓለም ዋይታ

## 283. አምላክ ሆይ ወደ እኛ ባትመጣ

አምላክ ሆይ ወደኛ ባትመጣ ለብሰህ የሚያምን
ሥጋ/2/
ባክኖ የነበረው የአዳም ዘር ወጡቱ ነበር
የሚያስፈራ/2/
በዚያ ዓመት በዚያች ወር በዚያች ቀን
ደህትን ለሰው ልጅ
ምን የበዛ ነበር ትህትናህ ትዕግስትህ
የማይለወጥ/2/
የሾህ አክሊል ደፍተው በራስህ በራስህ ጎንህን
ሲወጉህ በጦር/2/
አንተ ግን ለእነርሱ ከአባትህ ምህረትን
ትለምን ነበር/2/
ግን መቼ አወቁት እነርሱ በኃጢአት ደንድኖ
ልባቸው/2/
መድኃታቸውን ገረፉህ ሰቀሉህ አንተም
ሞትክላቸው/2/
ዳግም ስትመጣ ለፍርድ ከዓለም ፍጻሜ
በኋላ/2/
እረ እንዴት እድለኖች ናቸው በፊትህ
የሚያገኙት ተድላ/2/
በዚያች በደብረዘይት ቦታ ደስታና ለቅሶ
ሲፈልቅ/2/
ከቶ ከየት ይሆን እጣዬ ያን ጊዜ የእኔ
አወዳደቅ/2/
የፀፀት እሮሮ በፊትህ እንዳያቃጥለኝ
እኔን/2/
እርዳኝ ፈጣሪዬ ከአሁኑ አድሰው የዛገው
ልቤን/2/

## 284. የክብርን አክሊል

የክብርን አክል እንድትቀዳጁ
የእግዚአብሔርን መንገድ በቶሎ አዘጋጁ/2/
ምንም ብንሸነፍ ከቶም ብንሸበር
እግዚአብሔር አለልን ከክፉ የሚከወር/2/
ጉዞአችን የግብ ነው የሚያስፈራን የለም
ነግሶ የሚኖር ነው ጌታችን ዘለዓለም/2/

እጅግ ቸከለናል ቀኑ አመት ሆኖብን
የሚያስብልንን ልናኝ አምላክን/2/

እስከዚያው እንጽና እንኑር በትግስት
ከአምላ፤ክ እንድናገኝ የድል ሽልማት/2/

ልጆችህም ሽሹ ከምህረትህ ወጥተው
ጸጋህ ላክና አንተው መልሳቸው/2/
ጸጋወን ለብሰን ስንቆም በፊቱ
ይባርከናል በቸርነቱ/2/

በሚመጨሻው ቀን ሲገለጥ ጌታችን
ዙፋኑ ስር ሆነን በክብር እየዘመርን/2/
እርሱ ከፍ ብሎ እኛ ብርሃን ለብሰን
እንደሰታለን መዝሙር እየዘመርን/2/

# *የደብረታቦር መዝሙራት*

### *285. አማን በአማን*

አማን በአማን/2/
ተሰብሀ በደብረታቦር
**ትርጉም፦ –** እወነት በእወነት በደብረታቦር
ከበረ ተማሰገነ

### *286. የታቦር ተራራ*

**የታቦር ተራራ/2/ የአርሞንኤም/2/**
**ተደሰቱ ዛሬ በእንተ ስም እኽ**

### *287. አሐደ ለከ*

*አሐደ ለከ ወአሐደ ለሙሴ*
*ወአሐደ ለኤልያስ ንግበር ማኅደረ/2/ እኽ*

*ትርጉም፦- አንድ ለአንተ አንድ ለሙሴ አንድ ለኤልያስ ቤት እንስራ*

### *288. የታቦር ተራራ*

የታቦር ተራራ በጣም ደስ ይበልሽ/2/
እግዚአብሔር መለኮቱን ስለገለጠብሽ/4/

በስመ ዚአከ

በስመ ዚአከ ይትፌሥሑ ዮም/ 2/
ታቦር ወአርሞንኤም/4/

ትርጉም፦- ታቦርና አርሞንኤም በስምህ ዛሬ ደስ ይላቸዋል፡፡

### *289. .ቡሔ በሉ*

ቡሄ በሉ ሆ /2/
ልጆች ሁሉ ሆ
የእኛማ ጌታ የአለም ፈጣሪ
የሰላም አምላክ ሆ ትሁት መሃሪ
በደብረታቦር የተገለፀው
ፊቱ እንደ ፀሀይ በርቶ የታየው
ልብሱ እንደ ብርሃን ያንፀባረቀው
ድምፅህን ሠማኽ በብሩህ ደመና
የቡሄው ብርሃን ለእኛ መጣልን
ያዕቆብ ዮሃንስ እንዲሁም ጴጥሮስ
አምላክን አዩት ሙሴ ኤሊያስ
አባትም አለ ልጄን ስሙት
ቃሌ ነወና የወለድኩት
ታቦር አርሞኒየም ብርሃን ታየባቸው
የቅዱስ ተራራ በጣም ደስ አላቸው
ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ
ብርሃነ ማለኮት በአንቺ ላይ አበራ
በተዋህዶ ወልድ የከበረው
የእግዚአብሄር አብ ልጅ ወ/ሚርያም ነው
ቡሄ በሉ/2/ የአዳም ልጅ ብርሃንን ተቀበሉ
አዝ
አባቴ ቤት አልኝ ለከት
እናቴም ቤት አልኝ ለከት
አጎቴም ቤት አልኝ ለከት
አክስቴም ቤት አልኝ ለከት
ተከምሯል እንደ ኩብት
የአመት ልምዳችን ከጥንት የመጣ
ከተከሚረው ከሙኩብ ይወጣ
ከደብታቦር ጌታ ስለመጣ
የተጋገረው ሙልሙሉ ይምጣ
ኢትጵያወያን ታሪክ ያላችሁ
ባህላችሁን ያዙ አጥብቃችሁ
ችቦወን አብሩት እንደ አባቶቻችሁ
ምስጢር ስላለው ደስ ይበላችሁ
አባቶቻችን ያወረሱን የቡሄን ትርጉም ያሳወቁን
እንድንጠበቀው ለእኛ የሰጡን
ይህን ነወና ያስረከቡን
ለድንግል ሚርያም አስራት የሆንሽ
ቅዱሳን ፃድቃን የሞሉብሽ
በረከታቸው ያደረብሽ
ሁሌም እንግዶች የሚያርፉብሽ
ሀገረ እግዚአብሔር ኢትዮጵያ ነሽ
ለሃዋርያት የላከ መንፈስ
ዛሬም ለኢትዮጵያ ፀጋወን ያፍስስ
በበጎ ምግባር እንድንታደስ
በቅን ልቡና በጥሩ መንፈስ
በረከተ ቡሄ ለሁላችን ይድረስ
አመት አወደ አመት ድገምና
በጋሽዬ ቤት ድገምና አመት ግገምና
ያወፎድ በረከት ድገምና አመት ድገምና
ወርቅ ይፍሰስበት ድገምና አመት ድገምና
በእሙዬ ቤት ድገምና አመት ድገምና
ይግባ በረከት ድገምና አመት ድገምና
ሚርና ወተት ድገምና አመት ድገምና
ይትረፍረፍ በእወነት ድገምና አመት ድገምና

አንዲሁ እንዳላችሁ በክብር
አይለያችሁ በክብር
ለአመቱ በሰላም በክብር ያድሳችሁ
ክርስቶስ በቀኙ ያቁማችሁ
የመንግስቱ ወራሽ ያድጋችሁ
እንዲሁ እንዳለን በክብር
አይለየን በክብር
ለአመቱ በሰላም በክብር ያድርሰን
አማኑኤል በቀኙ በክብር ያቁመን
የመንግስቱ ወራሽ ያድርገን
የቅዱሳን ሰሜት የፃድቃን ሰሜታት
ረድኤት በረከት ይግባ በሁሉም ቤት
በሁሉም ቤት /2/ ይግባ በረከት

# የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም መዝሙሮች

## 290. መንክረ ግርማ

ማንከረ ግርማ ሀይለ ልኡል ፀለላ
አማን/2/ መላዕክት ይኬልልዋ
በሚያስደንቅ ግርማ የልዑል ሀይል ጋረዳት
በእውነት/2/ መላዕክት አማሰገኗት/

## 291.መሰረተ ህይወት

ማሰረተ ህይወት ማርያም በረድኤት ነይ/2/
ምህረት ቸርነትን ይዘሽ ከሰማይ/2/
ማርያም ድንግል በረድኤት ነይ

## 292. እስከማዕዜኑ

እስከሚዕዜኑ እግዝእትየ ወስተ ሀገርኪ ነኢ ትሄልዊ
ገሊላ እትዊ/4/ ሀገርኪ ገሊላ እትዌ
እስከመቼ ድረስ እማቤቱ በሰው ሀገር ትኖሪያለሽ
ገሊላ ግቢ/4/ አገርሽ ገሊላ ግቢ

## 293. አንቺ የወይን ሀረግ

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ
የበዛ/2/
ምግብ ሆኖ/2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለእኛ ቤዛ/2/
በአንቺ ኃይማኖትነት ድንግል የወጣው ፀሀይ/2/
ብርሀን ነው/2/ ለፃድቃን ስመም አዶናይ
ፊደል ትማሪያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ/2/
ለመላዕክት/2/ የሚይቻል ነበልባሉን የቻልሽ/2/
የማኅብ ምሳሌ ድንግል የኮከብ ማኛ/2/
በስጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለእኛ

## 294. ማርያም እመ ብዙሃን

ማርያም እመ ብዙሃን/2/
እመ ብዙሃን /2/ ማርያም

## 295. የመላዕክት እህት

የመላዕክት እህት የሠማዕታት እናት የፃድቃን እማቤት
ለምኝልን/2/ ከልጅሽ ማርያም ቅድስት

## 296. እመቤቴ ጥላ ከለላዬ

እማቤቴ ጥላ ከለላዬ እረዳቴ/2/
የፅዮን ማኛራ/4/ ማርያም የልዑል ሚሪያ

## 297. ማህደረ መለኮት

ማህደረ መለኮት
ማርያም እመ ብዙሃን

## 298. ምስለ ሚካኤል

ምስለ ሚከኤል ወገብርኤል ንኢ ሰናይተ ማርያም/2/
ነይ/8/ እም አምላክ ንኢ ማርያም
ከሚከኤል ጋር ከገብርኤል ጋር ነይ/2;
ርግብየ ነይ/2/ ነይ ሚሪያም/2/

## 299. መሶበ ወርቅ

ማሶበ ወርቅ ዘመና እግዝዕትነ ማርያም ቅድስት/2/
ቅድስተ ቅዱሳን ይብልዋ ካህናት/2/

## 300. ነይ ነይ ማርያም

ነይ ነይ ማርያም ወላዲተ አምላክ
የጻድቃን እማቤት የመላዕክት እህት
ሁላችን እንመጣት ከልብ
አማኣጅ ናትና በዕውነት
እናማስግናት እናወድሳት እንወደዳት
አማኣጅ ኪዳነ ምህረት

## 301.መሠረተ ህይወት

ማኅረት ህይወት ሚርያም ወጥንተ መድሃኒት
ዘእምቀዲሞ
ለወልድ/2/ አምሳለ ደሙ
**ትርጉም፡ –**ቅድመ አለም የነበረ መድሃኒት
ከሚቢል የተገኘሽ የህይወት መሠረት ሚርያም
አንቺ ነሽ ማኅረትሽም የልጅሽ ደሙ ምሳሌ ነው

## 302. በምድራዊ ህይወት

በምድራዊ ህይወት/2/ በፈተና ቦታ
ድንግል ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ
ሚርያም ትጠብቀን እጆቿን ዘርግታ

## 303. ቅድስተ ቅዱሳን

ቅድስተ ቅዱሳን ሚርያም ድንግል
ለምኝልን አሜልጅን ከልጅሽ ከመድሃኔዓለም

## 304. ሰላም ለኪ

ሰላም ለኪ ሚርያም እመ አምላክ
ወልድኪ ይጼወአኪ ወስተ ህይወተ ወመንግስተ
ክብር

**ሚርያም ፊደል**

ሚርያም ፊደል የሁሉ መሜሪያ/2/
በንፅህና/2/ ተፅፋለችና/2/

**እንተ በምድር**

እንተ በምድር ስረዊሃ ወበሰሜዬ አእዖኪያ
ሐረገ ወይን/2/ ድንግል ሐረገ ወይን/2/

## 305. ንፅህይተ ንፁሃን

ንፅህተ ንጹሃን ከዊና ከመቃቦር ዘዶር ዘሲና
ወስተ ቤተ መቅደስ ነበረት በድንግል ነበረት
ሲሳያ ህብስተ መና ወስቴ ሃኔ ስቴ ፅሞና
ትርጉም፡ – ከንፁህንም ንጹህ ሆና በሲና እንደ
ነበረችው ታቦት በድንግልና በቤተ መቅደስ
ወስጥ ኖረች ምግቧ ህብስተ መና ማጠጧም
የፀጥታ ማጠጥ ነበር

## 306. ማርያም ተአቢ

ሚርያም ተአቢ እምኩሉ ፍጥረት/2/
ኢያወአያ እሳተ ማለኮት
ሚርያም ትበልጣለች ከሁሉ ፍጥረት
ስለያዘች እሳተ ማለኮት

## 307. እምነ እምነ ነይ

እምነ እምነ ንኢ/2/
በሰላም/2/ ንኢ ሚርያም

## 308. ክነፈ ርግብ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲ ሃኒ
ሐሜልሚለ ወርቅ/2/
አንቲ ምስራቀ ወወልድኪ ፀሀየ ፅድቅ **<u>አሚነ
በአሚነ /</u>**3/
ኢይሀልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ/2/

## 309. ልቤን አነሳስቶ

ልቤን አነሳስቶ ያማለክተኛል
የአምላክን እናት እመናት ይለኛል
እመን/4/ የአምላክን እናት አዛኝቷን/2/

## 310.ይዌድስዋ

ይዌድስዋ መላዕክት/2/ ለሚርያም/2/
በወስጠ ወሳጤ መንጦላዕት ወይብልዋ
በሃኪ ሚርያም ሃዳስዩ ጣዕዋ

## 311. በመኑ

በሙ በአምሳለ ሙ ናስተማስለኪ
እሚቤቴ የእኔ አማላጅ አዛኝቱ ድንግል ምልዕተ
ውዳሴ

## 312.ድንግል ማርያም እናታችን

ድንግል ሚርያም እናታችን/2/
የጌታችን እናት ለምኝልን ለእኛ
የአማኑኤል እናት ለምኝልን ለእኛ

## 313.የፍቅር እናት የሰላም

የፍቅር እናት የሠላም/2/
ይናፍቀኛል ስምሽ ሳልጠራው ስቀር ሚርያም
በህይወቴ ወስጥ በኑሮዬ ቅደሚ ከፊት
ከኋላዬ
ተደላደለ ልቤ አንቺ አለሽና አጠገቤ
ምኞቴም ይስመር ድብቅ ህልሜ ልለፍ ወጀቡን
ተቋቁሚ
የጌታዬ እናት ነሽ ኃይልን ያደርጋል ጸሎትሽ
እንዴት እቀራለሁ ከመንገድ አደራ እናቴ
አስቢኝ
ለሚያስጩቀኝ ጠላት ለሚያሳድደኝ
አትስጪኝ
ትላንትም ዛሬም አማኃኝ ነኝ የለም ለነገ
የሚያስፈራን
ሜዳ ይሆናል ተራራ ልጅሽ ስላለ ከእኔ ጋራ

## 314.ማርያም እንወድሻለን

ማርያም እንወድሻለን/2/
ስለወለድሽ የህይወት ምግብን
ማርያም እንወድሻለን
ድካሜን አትይ ማርያም
በሃጢያት መውደቄን //
ተስፋዬ አንቺ ነሽ //
እስከ ዕለተ ሞቴ //
ላልከዳሽ ምያለሁ //
ከስርሽ ላልጠፋ //
ገፀ በረከቴ //
የህይወቴ ዋስትና //
የምዕመናን ወብት //
ዘወድ አክሊላቸው //
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ //
መንገድ ስንቃቸው //
ምስክር ነኝ ለአንቺ //
እንደ ነብያቱ //
ስጦታ መሆንሽን //
ለአዳም ልጆች ሁሉ //
ሞገስና ጸጋ //
በጌታ ፊት ያለሽ //
ከሰይጣን ማሻሻ //
ዋስ ጠበቃችን ነሽ //
እንዴት ነበር ያኔ //
ጌታን ስትወልጂው //
የእረኞቹ ደስታ //
የመላዕክት ዝማሬ

## 315.ስድቤን አርቀሽ

ስድቤን አርቀሽ ነወሬን ሸፈንሽው
እመ አምላክ በአንቺ መቼም አላፍርም
ስምሽን ጠርቼ እፅናናለሁ
ሀዘኔን በአንቺ እረሳለሁ
ነወር አለብኝ ብዙ ስድብ
አንጀት የሚልጥ ልብ ሚያቆስል
ስሜን ለወጠው ቢያንቋሽሹኝ
በሃዘን በለቅሶ ድንግል መጣሁኝ
እንደ ሃና ሆኜ በቤተመቅደስ
በሚረ ሃዘን ነው እኔ የማለቅስ
ፍረጅልኝና ልማለስ ከቤቴ
ሃዘኔን በደስታ ለወጪው እናቴ
በግራ በቀኝም ጠላት ቢከበኝ
አብዝቼ እጮሃለው እናቴ ስሚኝ
መከራው በዝቶ ግራ ገብቶኛል
ድምፅሽን ልስማው የረጋጋኛል
የሰው ህይወቱ ብርቱ ሰልፍ ነው
ደስታና ሃዘን የሚፈለየው
በእጃችን ወድቋል ሲሉ
ጠላቶቹ
አሜልጥኳቸው ሰምሽን ጠርቼ
ሰው የዘራወን ያንኑ
ያጭዳል
በቆፈረው ጉድጓድ ራሱ
ይገባል

እናቴ እማቤቴ ብዬ ስጠራሽ
ከመከራ ሁሉ ታወጪኛለሽ
በምርኮ ሳለሁ በሰው ሃገር
ግፍ ወለውብኝ ስኖር በእስር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ተፈትቻለሁ
በተአምራትሽ እኔ ድኛለሁ
ቃልሽን ሰምቶ ጽንሱ ሰገደ
ብላለች ኤልሳቤጥ ነወሬ ተወገደ
የጌታዬ እናት እኔን አሰበችኝ
ታሪኬን ቀይራ ይኸው ባረከችን
የእማቤቴ ከሆንኩ ማን ይቃወመኛል
ወጀቡም ማዕበሉም ይታዘዝልኛል
ወይኑ እኮ አልቋል የዶኪማስ ቤት
ድንግል አማልጅው ነይ የእኛ እማቤት
ስምሽ ሲጠራ በየቦታው ይመላልና
የጎደለው
ግራ የገባው የጨነቀው ድንግልን
ይጥራ እንድትረዳው
ሳዝን ስተክዝ የምታፅናና
እናት አለችኝ ርህርሕይተ ልቦና
እናቴ እማቤቴ ብዬ ስጠራሽ
ከመከራ ሁሉ ታወጪኛለሽ

## 316. እኔ የእርሷ ልጅ ነኝ

እኔ የእርሷ ልጅ ነኝ እስከዘለአለም
እርሷም እናቴ ናት ቤዛዊተ ዓለም
ፍቅሯ በልቤ ወስጥ ጣዕሟም በአንደበቴ
ስሟም ስንቅ ሆኖኝ ታትሟል በህይወቴ

የክብርሽን ነገር ባልችልም ማዘርዘር
የመወለድሽን ምስጢር ቢያቅተኝ መናገር
ከቶ ዝም አልልም ባይኖሩኝም ቃላት
ምስጋና አቀርባለሁ ለፈጣሪዬ እናት

በዘመኔ ሁሉ ለማስግን ድንግልን
አብነት አድርጌ ቅዱስ ገብርኤልን
ምስጋና ለክብሯ ወዳሴን ለፍቅሯ
ዘወትር አቀርባለሁ ስለዳንኩ በልጇ

አንቺ ተናገርሽው ሰፍሯል በወንጌሉ
ብፅዕት እንደሚሉሽ ትውልድ መካከል
እኔም ስለሆንኩኝ ከትውልድ መካከል
ሰላም ለኪ እላለሁ ተፈስሂ ድንግል

ድንግል ስማጸንሽ ፊትሽ ተንበርክኬ
ሰአሊ ለነ ስልሽ አማልጂኝ ከአምላኬ
ንዒ ንዒ ስልሽ በያሬድ ቅብ ዜማ
ህይወቴን ታደጊያት ከኃጢአት ጨለማ

ከአንቺ ጋር ነውና እግዚአብሔር
ሰላም እንድናገኝ እንድንኖር በፍቅር
ከተወዳጅ ልጅሽ ምህረት ለምኚ
በአማላጅነትሽ ከእኛ ጋራ ሁኚ

## 317. ክብሬን ያየሁብሽ

ክብሬን ያየሁብሽ የሰማይ ሠሌዳ
የኃይማኖት ፊደል እንቁነሽ ፀአዳ
የፈውስው መድኃኒት በአንቺ ሲሰናዳ
በምድር አከበርንሽ በሰማያት ጋዳ/2/

የሕይወት መሰረት የዓለም ምሰሶ
ስደተኛው ልቤ በአንቺ ተመልሶ
ከዮርዳኖስ ማዶ ቆሜአለሁ ጌልጌላ
ራሴን በእጅሽ ሰጠሁ ገባሁ በመሀላ
ምልጃሽ አለምልሞኝ አፍርቻለሁና
ድንግል እመቤቴ ይድረስሽ ምስጋና

በወርቅ የተሸለምሽ የንጉሥ ሙሽራ
የእውነት መገለጫ የኮሬብ ተራራ
ድንግል ማርያም ብዬ ከአጸድሽ ስገባ
ያስጨነቀኝ አልፎ የኔ ንጋት ጠባ
ምልጃሽ አለም ልሞኝ አፍርቻለሁና
ድንግል እመቤቴ ይድረስሽ ምስጋና

እውነተኛ ረዳት የእኔ ታማኝ መሪ
ምስኪኑን ሰብስበሽ ከቤት አሳዳሪ
የለም የተገፋ የለም መጻተኛ
በርስትሽ እንድንቆይ ለምኚልን ለእኛ
ምልጃሽ አለምልሞኝ አፍርቻለሁና
ድንግል እመቤቴ ይድረስሽ ምስጋና

ስላንቺ ታረቀን የበደልነው ጌታ
ልጆቹ አደረገን በሸሸነው ፈንታ
ልጁ ሆይ ስትይው በፅድቅ እንድንመላ
ከጥፋት ምድር ወጣን ላናይ ወደኋላ
ምልጃሽ አለምልሞኝ አፍርቻለሁና
ድንግል እመቤቴ ይድረስሽ ምስጋና

## 318.ውዳሴ

ውዳሴ/2/ ወገናይ ለእመ አዶናይ
ብርሃን ዘወለደ በግሩምወሰናይ

ውዳሴ ወለተ ነቢያት
›› ስብከተ ሐዋርያት
›› እህተ መላዕክት
›› እመ ሰማዕታት
አንቀፀ ብርሃን መዓርገ ህይወት
ቅድስተ ቅዱሳን ማህደረ መለኮት

ውዳሴ ሚርያም ቡርክት›
›› እም ኩሉ ፍጥረት
›› ምልዕተ ወዳሴ
›› ሰአሊተ ምህረት
ጥዕነተ ምስራቅ እሙ ለብርሃን
ምክንያተ ድህነት ተስፋ ለሃጥአን

ውዳሴ ከመ ታስተሰርይ
›› ሀጢአተ ህዝበኪ
›› እም ኀበ እግዚአብሔር
›› ተበወአለኪ
ለወሉደ ሰብኢ ህይወት ዘለዓለም
ሰአሊነ ለነ ቅድስት ቤዛዊተ ዓለም

## 319.እመቤቴ ማርያም

እማቤቴ ሚርያም እለምንሻለሁ
በለቅሶ በዋይታ ፊትሽ ወድቄአለሁ
እማቤቴ ስሚኝ ተማፅኜሻለሁ/2/

ችግሬን ጉዳቴን ለማን እነግራለሁ
ችግሬን ጉዳቴን ለማን አዋያለሁ
እማቤቴ ስሚኝ ተማጽኜሻለሁ/2/

ሀዘኑ በዛብኝ ፈተናው ከበደኝ
እንደምን ልቻለው እኔ ብቻዬን ነኝ
የአማኤል እናት ፈጥነሽ ድረሽለኝ

በጣም ተንገዳገድኩ ልወድቅ ነው እኔ
እምአምላክ ደግፊኝ ቁሚልኝ ከጎኔ
ምንም አጋር የለኝ ከአንቺ በቀር ለእኔ

## 320. ፀጋን የተመላሽ ሆይ

ፀጋን የተማላሽ ሆይ ክብር ከአንቺ ይገባል
የአሸናፊ የእግዚአብሄር እናቱ ሆነሻል
ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ ተመርጠሻል
ሠላም ልበልሽ የጌታዬ እናት
ፅድቅ ያየንብሽ ምክንያተ ድህነት
ልባችን ያወጣ በጎ ነገር
ለዓለም እንማስክር የአንቺን ክብር
የምስራቅ ፀሀይ ኩራቴ ነሽ
እጅግ ልዩ ነው ደግነትሽ
ልቀኝ ለክብርሽ እንደ ያሬድ
የአበው ተስፋ ሰላም ወዳድ
የድል አክሊል ነሽ ሠላማዊት
ህብስተ መና ምግበ ህይወት
ከልቤ ሆኜ እስቲ ላድንቅሽ
እንደ አባ ኤፍሬም በዝቶልኝ
ምልጃሽ
የማቀሉ ስር ስጦታ ነሽ
ለዓለም ሜፅናናት የተሚጥሽ
የሚያቃልሉ ክብርሽን ንቀው
ይሚልላሉ ከፊትሽ ወድቀው

## 321. የልቤን በልቤ ይዤ

የልቤን በልቤ ይዤ ከፊትሽ ቆሜአለሁ

የሆዴን በሄዴ ይገፔ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
ካለኝ ነገር ሁሉ አንቺን መርጫለሁ
እናቴ ሆይ ስሚኝ አሜልጅኝ እላለሁ
ግራ ቀኝ ህይወቴ በእሾህ ታጥሮብኛል
በፊት በኋላዬ ማስናከል በዝቷል
እኔስ ያለምርኩዝ ጉዞዬ ከብዶኛል
እምአምላክ ደግፊኝ እጄ ተዘርግቷል/2/
ቆሜ ስራመድ ጠኔኛ እመስላለሁ
የወስጤን ጎዶሎ እኔ መች አወቃለሁ
ድንግል ሆይ ቅረቢኝ አይዞህ ልጄ በይኝ
የጭንቀቴን ካባ አወልቀሽ ጣይልኝ/2/
እናት ያለው ሰው ፍጹም አይተክዝም
አንድ ቀን ይስቃል አልቅሶ አይቀርም
ሀዘኔን በደስታ ለወጪው እናቴ
በሃሴት ልዘምር በቀረው ህይወቴ/2/
አሁንም ጎዶሎ በወስጤ አለና
ድንግል ሆይ ቅረቢኝ ዛሬም እንደገና
ለዚህች ለትንሿ ለጥቂቷ እድሜ
እንደከፋኝ አልኑር ቀና አርጊኝ እናቴ/2/

## 322. ማርያም በስምሽ

ማርያም በስምሽ ይዘናል ቀኖና
ትንሳኤሽን ልጅሽ ያሳየናልና
ፆም ማለት እንዲህ ነው ይኸው ነው ስርዓቱ
ሐዋርያት ፆመው ለእኛ አበረከቱ
ነፍስና ሥጋችን በመበል ተጣልተው
ሽማግሌ ሆኖ ፆም አስታረቃቸው
አብረው እያደሩ አብረው እየዋሉ
አያምርም አይሰምርም በመበል ሲጣሉ
ነፍሳችን ከስጋ ማለየቷን አወቃ
የዓለም ተድላዋን ደስታዋ ንቃ
በፆም በሱባኤ ትኖራች ታጥቃ
ነፍስም ለስጋዋ ትነግረው ጀመረች
በብዙ ምሳሌ እያመሳሰለች
ሥጋዩ ሞኝ ነህ መበልን አትወደደው
ከአዳም አንስቶ ከመጀመሪያው ሰው
መበል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መች አየነው/2/

## 323. በጎ መዐዛ

በጎ መዐዛ ሽቶዬ ነሽ
በሰዉ ሁሉ ፊት ዘመርኩልሽ
በአንቺ ጣፈጠ አልጫነቴ
እጠራሻለሁ ነይ እማቤቴ
ምሳሌም የለሽ ነይ እማቤቴ ዘመዴ ነሽ ነይ እማቤቴ
ያን ከፉ ዘመን ነይ እማቤቴ ያለፍኩብሽ ነይ እማቤቴ
በፍቅርሽ እሳት ነይ እማቤቴ ልቤ ነደደ ነይ እማቤቴ
እናትነትሽን ነይ እማቤቴ ስለወደደ ነይ እማቤቴ
የሰወስ ጉልበት ነይ እማቤቴ ምን ይረባኛል ነይ እማቤቴ
ሰረገላዬስ ነይ እማቤቴ መች ያድነኛል ነይ እማቤቴ
ከተሰወረ ነይ እማቤቴ ከፉ መከራ ነይ እማቤቴ
እድናለሁኝ ነይ እማቤቴ አንቺን ስጠራ ነይ እማቤቴ
ለስንፍናዬ ነይ እማቤቴ መቼ ልክ አለዉ ነይ እማቤቴ
ስለበደሌ ነይ እማቤቴ እተክዛለሁ ነይ እማቤቴ
ለአነጋገሬ ነይ እማቤቴ ማጣፈጫነሽ ነይ እማቤቴ
ተሰምቻለሁ ነይ እማቤቴ ድንግል ሆይ ስልሽ ነይ እማቤቴ
የመንገዴ ስንቅ ነይ እማቤቴ የርሀቤ መርሻ ነይ እማቤቴ
ለታመመ ሰዉ ነይ እማቤቴ ነሽ መፈወሻ ነይ እማቤቴ
የተማፀነ ነይ እማቤቴ በስምሽ አምኖ ነይ እማቤቴ
ማን አፍሮ ያወቃል ነይ እማቤቴ ፊትሽ ለምኖ ነይ

## 324. የሰላምታሽን ድምፅ

የሰላምታሽን ድምጽ ስሰማ እማቤቴ/2/
ሃዘኑ ጠፉልኝ በዛልኝ ሃሴቴ የሰላምታሽን ድምፅ
ከተራራው ሃገር >>
ከኤፍሬም ከተማ >>
ልቤ ተረጋጋ ድምፅሽን ሲሰማ >>
ቅድስት ኤልሳቤጥ ሆይ >>
በጣም ታደልሽ >>
የአምላክን እናት አፅናኝ አገኘሽ >>
ተገብቶኝ አይደለም >>
ቃሏን ለማስማት >>
ፍቃዷ ሆነና ተሞላሁ ሃሴት >>
አንተ የእግዚአብሐር ካህን >>
በደህና ሂድ በለኝ >>
የእማቤቴ ድምጿ ስንቅ እንዲሆንልኝ >>
**ነጎድጓድ ነው ቃሏ** >>
እኔን ያፅናናኝ >>
ቤተ መቅደስ ሄጄ ነው የሰማሁኝ >>
ፀጋ መንፈስ ቅዱስ >>
ይኸው ተሞላሁ >>

ምስጋና ለድንግል ለማቅረብ በቃሁ
> >
በቅዳሴ ማሃል
> >
ውብ ቃልሽ ይሰሜል
> >
ሁሉም ተረጋግቶ አንቺን ያዳምጧል
> >
የአዘነ ያፅናናል
> >
ትካዜን ያጠፉል
> >
ድንግልን የሰማ በተድላ ይኖራል
> >

## 325. ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም/2/
እናቱ ሆነሻል ለመድኃኔዓለም/2/
ንፅህት ስለሆንሽ //
እንከን የሌለብሽ //
የፍጥረታት ጌታ //
በአንቺ አደረብሽ //
የድንግል መሚጥ //
ይኸው አስገረመን //
እሳቱን ታቀፈች //
የሚይቻለወን
ምርኩዜ ልበልሽ //
ጥላ ከለላዬ //
ጋሻዬ አንቺ ነሽ //
ለእኔ መመኪያዬ //
በዓለም እንዳልጠፉ //
ሕይወቴ ሚሮብኝ //
እንደ ወይን አጣፍጪው//
ሜሪያም ድረሽኝ //
የምስራቅ ደጃፍ ነሽ //
የሁላችን ደስታ //
እሙለፀሃይ ፅድቅ //
የሁሉ ጠበቃ //
ድንግል የድል አክሊል //
ድንግል የፅድቅ ሥሬ //
ድንግል ማሳላል ነሽ //
የተዋህዶ ተስፋ //

## 326. የሰሎንዲስ ጥበብ

የሰሎንዲስ ጥበብ እወድሻለሁ
የናሆም መድሃኒት እወድሻለሁ
ሚርያም አከብርሻለሁ
ሚርያም እወድሻለሁ
ተጨንቄአለሁ ልንገርሽ
ምስጢረኛዬ እናቴ ነሽ
ሰው ያልሰማውን ብርቱ ምስጢር
ድንግል ሆይ ለአንቺ ላማክር
ለቁስለኛውም መድሃኒቱ
የአዳም ዘር ሁሉ ነሽ ህይወቱ
መፍትሄ አለ በእጅሽ
ተንበርክኸሽ ልማፀንሽ
ሳልናገረው የገባሻል
የወስጤ ሁሉ ይታይሻል
ድረሽ እናቴ ተረጂኝ
ያለአንቺ ለእኔ ማን አለኝ
ደስታዬ ደስታ የሚሆነው
በሃዘኔም የምፅናናው
አንቺ ከእኔ ጋር ስለሆንሽ
ተፅናንቻለሁ በስምሽ
ወንድሞቼ እንኳን ቢሸጡኝ
ሰው ሁሉ ጠላት ቢሆነኝ
በእመ አምላክ ሃይል ከብሬአለሁ
በጠላቴ ላይ ሰልጥኛለሁ
የረሱኝ ሁሉ ያስቡኛል
የተጣሉኝም ያከብሩኛል
አንቺ አንግሰሽኝ አልወድቅም
እቆማለሁኝ ዘለዓለም
መንገዴ ረዝሞ ደክሜበሽ
መከራው በዝቶ ታምሜበሽ
ወድቄ ሳዝን ድረሽኝ
ለባሪያሽ ሀይሉን እንድትሰጭኝ
ፍቅርሽ በወስጤ ተንሰራፋ
በእናትነትሽ ልቤ ሰፋ
የሚለየን ማንም የለም
ሚርያም ልበልሽ ለዘለዓለም

## 327. ደጅሽ ላይ ቆሜ ስለምንሽ

ደጅሽ ላይ ቆሜ ስለምንሽ
ባርኪኝ እናቴ ማርያም ስልሽ
ተደላደለልኝ ህይወቴ
በአንቺ በእናቴ በእመቤቴ

አንቺ በመሆንሽ የህይወቴ ፋና
አልፈራም ጨለማ ብርሃን አለኝና
አይጠፋም ዘለዓለም ስምሽ ከአንደበቴ
አለ በደሜ ውስጥ ፍቅርሽ በህይወቴ
አልቀርም ከደጅሽ ለዘለዓለም/2/
ከአንቺ የሚለየኝ ማንም የለም/2/

እጅግ የተገፋ ደካማ ሰው አለ
መቅደስሽ የቆመ አማልጂኝ እያለ
ይቁም ይሄ ልጅሽ ሀዘን የሰበረው
ከአንቺ በቀር ወገን መጠጊያ የሌለው
ያንሳው ኪዳንሽ ከውድቀቱ/2/
ያርግ በእጆችሽ ያ ጸሎቱ/2/
ፅልመት የለበሰ ፈታኝ አደከመኝ
የምቋቋምበት ጉልበት አስፈለገኝ
በርትቼ እንድጸና ሳይጎዳ ነፍሴ
ሁኚኝ እናቴ ሆይ ግርማና ሞገሴ

ልፅና ደግፊኝ እመቤቴ/2/
ይውለቅ ከእጇ ላይ ሰንሰለቴ/2/

አበው የለበሱሽ የክብራቸው ካባ
መዓዛሽ የሚስብ የሮማን አበባ
ለውጪው በምልጃሽ የህይወቴን ቃና
ባዶው ጋኔን ምልጃሽ ወይን ያስሞላውና
አፅድልኝ በእድሽ ማድጋዬን/2/
በወይን አስሞይው እንስራዬን/2/

## 328. ፅላት ዘሙሴ

ፅላት ዘሙሴ እፀጻጦስ ዘሲና/2/
ፅናፅል/5/ ለአሮን ካህን እኽ/3/
ፅናፅል/5/ ለአሮን ካህን
አልፌአለሁና እመቤቴ ያን ሁሉ መከራ
ከእኔ ጋር ስለሆንሽ ሰምሽን ስጠራ/2/
በዚያ በጭንቅ ቀን » እድግ በሚያስፈራ
ማን ያድነኝ ነበር » ሰምሽን ባልጠራ
በሞትና በህይወት » መካከል ብሆንም
ታምርሽ አነሳኝ » ማሪያም/ድንግል/ አልተውሽኝም/2/
- አዝ -
እድግ የከበደ ነበር ያገኘኝ ፈተና
ታሪክ ሆኖ ቀረ በአንቺ ዳንኩኝና/2/
ዙሪያው የሚያስፈራ » ፅኑ ነው ገደሉ
በዚያ የወደቁ » እንዴት ይተርፋሉ
ስምሽ ድጋፍ ሆኖኝ » ከስር ተነጠፈ
በሚያሰደንቅ ምስጢር » ህይወቴ ተረፈ/2/

## 329. አክሊሌ ነሽ

አክሊሌ ነሽ ማርያም ሞገሴ ነሽ
አክሊሌ ነሽ
አክሊሌ ነሽ ማርያም ሞገሴ ነሽ

ዮሴፍም ይናገር በስደት ተፅናንቷል
በቁምም በህልሙ መሰላሉን አይቷል
የበገናው ምስጢር ምን እንደነበረ
ፅዮን ሆይ እያለ ዳዊት መሰከረ

ትውልድ እንዲጠቀም ስምሽን አንስቶ
እነኳት ብሎናል ጌታ ተሰውቶ
የፍቅር ስጦታ የድሆች እናት
የክብር አክሊል ናት ዘውድ ሽልማት

ሙሴ በበረሀ ምን ተገለጸልህ
ሀመልማል በእሳት ሳይቃጠል አየህ
ነብያት ተነሱ ትንቢት ተፈፅሟል
ቃል ከሰማይ ወርዶ ሥጋን ተዋህዷል

ለዓለም ሞኝት ነው በስምሽ ማመኑ
ታምርሽን መስማቱ ውዳሴ መድገሙ
እኔስ ምስክር ነኝ ዛሬም ለዘለዓለም
ማርያምን ሳይጠሩ ከቶ መፅደቅ የለም

## 330. ድንግል ትንሳኤሽን

ድንግል ትንሳኤሽ እስከምናይ ድረስ
ገብተናል ሰላኤ በአንድነት በመንፈስ
ለእኛ እስኪገለጥ ቶማስ ያየው እዉነት
አንወጣም ከደጅሽ ኪዳነ ምህረት/2/
ሞትን የረገጠ ልጅሽ ከአንቺ ጋር ነው
ወጦ የሚያስቀርሽ የቱ መቃብር ነው
የዕርገትሽን ዜና ከቶማስ ሰምተናል
ትንሳኤሽ እዉነት ነው ሰበንሽን አይተናል
ሞትማ በሞት ተሸንፏል
በአንቺ ላይ እንዴት ኃይል ያገኛል
ድንግል ትንሳኤሽን----------
ልናው ወደድን የቶማስን ክብር
ለምን ተሰወረን የትንሳኤሽ ምስጢር
በራችንን ዘግተን በጸሎት ወድቀናል
ተገልፀሽ አብሪልን ልጆችሽ ናፍቀናል
መዝሙሪኛው አባትሽ ዳዊት ፅፎልናል
ሞትን የማያይ ሰው ማን አለ ብሎናል
ይህ እዉነት በዘመን አንቺ ላይ ቢደርስም
በሞት ተሸንፈሽ መቃብር አትወርጂም
ቶማስ ከደመናው ወርዶ ሲያናግረን
ስለሆነው ነገር እጅጉን ተማጥነን
እኛም ይህን ክብር ተመኘን ለማየት
ድንግል አሳስቢልን ኪዳነ ምህረት

## 331.ማርያም/2/ ብዬ

ሚርያም/2/ ብዬ ስምሽን ልጥራው
አይደከመኝም እኔስ ብደጋግመው
አሁንም ጡራህሽ አላስችልህ ቢለኝ
አወቀዋለሁስምሽን እናቴ ስትወልደኝ/2/

ገና በማህጸን በእናቴ የምጥ ቀን
ደጋግሜ ሰማሁ ሲጠሩ ስምሽን
በሰከንዳት አድሜ የማውቃት አንዷት ቃል
ልቤ ላይ ያለው ስም ሚርያም ሚርያም ይላል/2/
ሚርያም----

ሔዋን ማጠ ቀሎ ልጆችዋን ታቀፈች
በአማጇነትሽ እናቴም ታማች

በተወለድኩባት በመጀመሪያው ቀን
ስምሽን እየጠራሁ ወጣሁ ከማህፀን/2/
ማርያም----

ከቃል ኪዳን ስም ጋር አደኩኝ አብሬ
ምልጃሽ ሳይለየኝ አለሁ እስከ ዛሬ
የህይወቴን ፊደል ከአንቺ ላይ ቆጠርኩኝ
በልጅሽ አምኜ ዳግም ተወለድኩኝ/2/
ማርያም----

የከፉ ቀን ስንቁ ያዘልኩሽ በልቤ
የህይወቴ ምግብ የእንጀራ መሶቤ
እንደትላንትናው ዛሬም እጠራሻለሁ
የማቀል ስር ክብሬን እንዴት እረሳለሁ
የማቀል ስር ክብሬን እንዴት እተዋለሁ
ማርያም----

## 332. ማርያም አርጋለች

ማርያም አርጋለች ወደ ገነት/2/
የሰማይ መላዕክት እያረጋጓት
እርሷም እንደ ልጇ ተነስታለች
የአባቷን ዳዊት ትንቢት ልትፈፅም
ወርቁን ተጎናፅፋ በቀኙ ልትቆም
ወደ አምላክ ሙሽሪያ ወደ ሰማያት
አረገች በእልልታ ድንግል የእኛ እናት
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
ሠማይም የከፈት ደመናም ይዘርጋ
ዝምታም አይኖርም እመ አምላክ አርጋ
አንደበት ይከፈት ማርያምን ያመስግን
ከዘለዓለም ጥፋት በምልጃዋ እንድንድን
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
የአምላክ ሙሽሪያ ያ ቅዱስ ስጋሽ
አምላክን ያቀፉት እነዚያ እጆችሽ
መቅና መቃብር ይዞ አላስቀራቸው
ተነስተዋል በክብር በእምነት አየናቸው
አርጋለች ማርያም ተነስታለች
**ሐዋርያት አበው እንኳን ደስ ያላችሁ**
በክብር አረገች ማርያም ሞግሳችሁ
ወደ አለምም ወጡ ሰበኗን ይዛችሁ
የድንግል ዕርገቷን ንገሩ ተግታችሁ
አርጋለች ማርያም ተነስታለች

## 333. ስምሽን ጠርቼ

ስምሽን ጠርቼ መቼ አፍራለሁ
ማርያም ብዬ መቼ እወድቃለሁ
የምፅናናበት ስምሽ ነዉና
ድንግል ሆይ ላቅርብ ላንቺ ምስጋና
ወጦኝ በጠላት አገር
ለዘመናትም ስረገጥ ስኖር
ዲያቢሎስ ማርኮ ሲያሰቃየኝ
የዓለሙ መድህን ወለድሽልኝ
ከአባቶቼ ርስት ከአገር ወጥቼ
በአህዛብ አገር ስኖር ተሸጬ
ደርሰሽ አፅናንተሽ አከበርሺኝ
ብቸኝነቴን አስረሳሽኝ
ድንኳኑ ሞልቶ ሰዉ ታድሞ
አስተናባሪዉ በጭፃቀት ቆሞ
ምን አቀርባለሁ ብዬ ስቸገር
ምልጃሽ ደርሶልኝ ዳንኩኝ ከሜዲር
የሰብኩት ሀሳብ ደመና ሆኖ
ቢበተንብኝ እንደጉም ተኖ
ይሆናል ያልኩት ሳይሆን ቢቀርም
በእማምላክ እኔስ ተስፋ አልቆርጥም
እናት አባቴ ባያስታዉሱኝ
ይህች ዓለም ንቃ ገፍታ ብትተወኝ
አንቺ ካለሽኝ ምን እሆናለሁ
አዎሎ ነፋሱን ባህሩን አልፋለሁ
ጠላቴ ደርሶ ቢያነገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨፃቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ወለታሽ ድንግል አለብኝና
ከፉዎች ደርሰዉ ቢዝቱብኝ
አንቺን መውደዴን አያስተዉኝ
በአህዛብ መሃል ስምሽን ስጠራ
መከታ ሁኚኝ እናቴ አደራ
ጠላቴ ደርሶ ቢያነገላታኝ
መከራ አብዝቶ ቢያስጨፃቀኝ
አላቋርጥም ያንቺን ምስጋና
ወለታሽ ድንግል አለብኝና

## 334. ለማርያም

ለማርያም/2/
እንዘምራለን ለዘላለም/2/
የተዘጋች ደጅ ለዘላለም ህዝቅኤል ብሏል //
ንፅህት ናት በእዉነት // በፍፁም ድንግል //
አብነት አድርግን // እኛም እርሱን //
በፍፁም ፍቅር እንዘምራለን/2/
የዋሂት ርግብ // ሰላም አብሳሪ //
የጨለመ ህይወቴን // ብርሃንን አብሪ //
እምጁንሻለሁ // ድንግል ለነፍሴ //
አደራ ቅድስት አንቺ ነሽ ዋሴ/2/
እጅግ የበዛ ነው // ያለኝ ፍቅር //
አይነገርም // አይወሰንም //
በእርሷ ደስ ይለኛል ሃሴት አደርጋለው
ስሟን እየጠራሁ እዘምራለሁ/2/
ንዒ ንዒ ስላት // ቀንና ሌሊት //
አትለየኝም // ለእኔስ ቅርቤ ናት
እፁብ እፁብ ብለው // አመስገኗት //
ክብሯን ሊገልፁ ቢያጥራቸው ቃላት/2/

## 335. የያሬድ ውብ ዜማ

የያሬድ ውብ ዜማ ድንግል እማቤቴ ስጦታዬ ነሽ
በምን አንደበቴ እንዴትስ ባለ ቃል ማርያም ልበልሽ/2/
ምድሪና ሰማዩ ተአምርሽ ይንገሩ
ፍጥረታት በሙሉ ስለአንቺ ይመስክሩ

ተነግሮ ያማያልቅ ድንቅ ነው ስራሽ
ድንግል ሆይ እናቴ አምሳያም የለሽ
ማርያም ድንግል እረዳቴ
የምትደርሽኝ ነይ ስልሽ በጭንቀቴ
ተአምርሽ በአይኔ አይቻለሁ
ጽዮን ሆይ ስልሽ ድንግል ሆይ እጠግባለሁ
የእግዚአብሔር ጥበቡ በአንቺ ተገለጠ
የአዳም ዘር በሙሉ ከሞት አማለጠ
የመዳን ምክንያት ማርያም አንቺ ነሽ
ለፍጥረቱ ሁሉ ማሳላል የሆንሽ
ነገን ባለወቅ እኔንም ቢያስፈራኝም
አንቺ ካሽልኝ በፍጹም አልወድቅም
በፊትሽም እንድቆም ለምስጋና
ማርያም ልበልሽ በትህትና
ትወልዱ በሙሉ ለምስጋና ይቁም
በአንቺ ስለሆነ የቀረለት ሞገም
አዳም ከነ ልጁ በሠማይ በምድር
ማርያም ማርያም ይበል ተአምርሽን ይናገር
ጨለማው ከፊቴ ተገፈፈ
ማርያም በምልጃሽ ልቤ አረፈ
ከጎኔ ነይ ስልሽ እፅናናለሁ
እሳት ገደሉን ሁሉንም አልፈዋለሁ

## 336. ይኩነኒ

ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ/2/
አለች የእኛ እናት በትህትና
በስጋ በነፍስም ንፅህት ናትና
አለች የእኛ እናት በትህትና
ድንግል በክሊዬ ንፅህይት ናትና
የአዳም ቃል ኪዳን ሚፀማየው ሲደርስ
ላከው ገብርኤልን ወደ ቤተ መቅደስ
በእግዚአብሔር ህሊና ተስላ የነበረች
ከሰማይ የመጣ ቃሉን ተቀበለች
**ዳግማይ ሰማይ አርያም ሆነች**
**ይደረግ ብላ በትህትና ተቀበለች**
ማርያም ሆይ አትፍሪ ብሎ እያረጋጋት

ከአንቺ የሚወለደው መድሃኒት ነው
አላት
ወንድ ስለማላወቅ ይህ እንዴት ይሆናል
ብላ ጠየቀችው ድንግልም ደንቋታል
**ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ**
**በህግ ሳይሆን በድንግልና ትወልጃለሽ**
ህይወት ሊቀዳባት አድሯል በማህፀንዋ
አይኖርም ከእንግዲህ የሄዋን ሞገሟ
ለአዲሱ ኪዳን አዲስ ብስራታችን
ምክንያተ ድህነት አለች እናታችን
**ቃሉህ ይፈፀም ይደረግ ብላ**
**ታምር ተሰማ ኢየሩሳሌም ናዝሬት ገሊላ**
እጅግ አስገረመን የገብርኤል ዜና
የእነ ዘካሪያስ ከቶ አይደለምና
ለተሚጠችው የደረሰው ብስራት
አለምን ከማጥ ከሞገሟ ዋጃት
**ከሴቶች መሃል አንቺ ልዩ ነሽ**
**በህግ ሳይሆን በድንግልና ትፀንሻለሽ**

## 337. ወገን ዘመድ

**ወገን ዘመድ ማንምረዳት በሌለበት ዘመን**
**ደርሰሽልኛል ድንግል ማርያም**
**ወለታሽን አልረሳም**
ባይኖረኝምእንኳ የኤልያብ ወበት
ሆንሽልኝ ኤታፌስ ቀንዲሉ እንዲከፈት
ከቅርነ ቅቡ ስር ዘለለ ዘይቱ
ልጄ ባርከውብለሽ ለምን ሽ እናቱ(2)
ለችግሬ የማቆምሳጣታማኝ ወገን
ቆምሽ ልኝ እናቴ በፈታኙ ዘመን
የዳዊት ዘር ድንግል ደጓ እማቤቴ
በመቅደስሽ ስቆምአላፈረምፊቴ(2)
ማቄን ቀየርሽልኝ አለበስሽኝ በፍታ
ሀዘኔን እረሳሁ ተሞልቼ ደስታ
ጠፉ ስብራቴ ልቤም ጠነ ከረ
ምልጃሽ በረከትሽ አብሮኝ ስላደረ(2)
ዓለም ብትዘነጋኝ ከነ ሚጠሬ
ባንቺ ደምቄያለሁ ሆነ ሽልኝ ክብሬ
በጅችሽ ቢባረክ የቤቴ ማከሩ
የናቁኝ በሙሉ በደጄ ሰፈሩ(2)

## 338. እንደ ኤልሳቤጥ

እንደ ኤልሳቤጥ ላማስግንሽ
ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ
የጌታዬ እናት የእኛ እማቤት
አዛኝ ነሽ ከልብ ፍጹም የዋህት
ርህራሄሽ ያስደስተኛል
ስለ ሀጢአቴ ምልጃሽ ይቀድማል
የሰላምታሽ ድምፅ ደስ ያሰኘኛል
ከትካዜዬም ያሳርፈኛል
ድምጽሽ ሲሰማኝ ልቤ ይረካል
ሀዘኔ ቀርቶ ፊቴ ፈካል
በእናትነት አንቺን ለሰጠን
ቸሩ አምላካችን ይክበር ይመስገን
የሁሉ እማቤት የሁሉ አፅናኝ
የዓለም መድሃኒት ከአምላክ አገናኝ
ዛሬም በልቤ ደስታ ጨምሪሽ
እንደ ኤልሳቤጥ ሰላም ልበልሽ
ከሴቶች መካከል ሞጦ ቀድሰሻል
ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉሻል
በልዩ ውዳሴ ያመግኑሻል
ድንግል ንግስታችን በቀኙ ቆመሻል
ሰላምታሽን ድምፅ ልቤ ሲሰማ
ነፍሴን ደስ አላት ቀለላት ሸክሟ
ድንግል ለክብርሽ ስንበረከክ
እጅሽ ይዘርጋ ለማባረክ

## 339. ለውዳሴሽ ልትጋ

ለወዳሴሽ ልትጋ ስምሽ ግርማ አለው/2/
እማቤቴ እኸ እማቤቴ ስልሽ እወላለሁ
ከልቤ አቀርባለሁ ምስጋና ለስምሽ
ማላመኛዬ ነው ፅኑ ቃል ኪዳንሽ
በሰላምታ ድምፅሽ ያልፀና ማን አለ

ፅንሱ በማህጸን በደስታ ዘለለ
ሚና ወተት ነው የስምሽ ስያሜ
እማቤቴ ስልሽ ይቀላል ሸክሜ
ቅኔ ማህሌቱ ሰዓታት ማዘመሙ
ያማስግኑሻል ምድርና ጠፈሩ
እናቱ ነሽና አንቺ ለአዶናይ
ማስደኩኝ ከፊትሽ ይቅርታወን እንዳይ
ሰአለለነ ብዬ ይኸው ተርፌአለሁ
በአንቺ ተደግፌ ነገም እኖራለሁ
ነይ ነይ እልሻለሁ እንደ ካህናቱ
በሰዓታት ጸሎት ቆሜ በሌሊቱ
ዝም አልልም እኔ አወድስሻለሁ
የዓለምን ጣከራ እረሳብሻለሁ

## 340. የታመነች ታዛዬ

የታማኝ ታዛዬ
ስጨቅ ሚፈያዬ
ሚያም/2/ እላለሁ
ከሃዘኔም እፅናናለሁ
በስደት እንኳን ሆኜ
ስጨቅ ተከፍቼ
ሲተርፈኝ እንባ ብቻ
ለአይኖቼ ጣከፈቻ
እጇ ነው የሚዝየኝ
ስሟ ነው የሚቀለኝ
ሲመተር ያለኝ ተስፋ
ቢወረስ በነቀፋ
ለነገ ምንም ሳጣ
ዛሬንም እንዳልወጣ
አየኋት አሻግሬ
ዋሴ ናት ለመኖሬ
አስጎንብሶኝ ቀንበሩ
ተዘግቶ ደስታ በሩ
መዝጊያወን ተደግፌ
ትቢያዬን አራገፋልኝ
ከእልፍኟ አሳረፈችኝ
አልጎልም ከምስጋና
ሞልቶኛል የሷ ቃና
ለዓለም እነግራለሁ
የክብሬን ምስጢር ዜና
ሰላሜን ያለበሰኝ
በእቅፏ አለኝና

## 341.የኤፍሬም ውዳሴ

የኤፍሬም ወዳሴ ሚያም ድንግል
ሞገሴና ክብሬ በሠማይ በምድር
እኔስ አቀርባለሁ አዲሱን ምሥጋና
ሶልያና ብዬ ድንግል ሶልያና/2/
እንደ ገብር-ኤ-ል ላማስግንሽ
መጥቼአለሁ ሚያም ልቆም ከፊትሽ
**እንደምትባርኪኝ አወቃለሁ ሚያም**
**ከአንቺ ጋር ስላለ መድኃኔዓለም** 2
ፊደል ናት ሚያም ፊደል ናት/2/
ሁላችን ከእርሷ የተማርንባት
ፊደል ናት ሚያም ፊደል ናት
የኤልሳቤት ልጅ ነኝ ግቢልኝ ከቤቴ
ደምፁሽን ሲሰማ ይጸናል ጉልበቴ
**ዮሐንስም አወቆሽ በማህጸንሽ ሰግዷል**
**አንቺ የምትሠጪው ዓለም ያስደንቃል**
2
በዋዛ ፈዛዛ የኖርሽ አይደለሽም
በቤተ መቅደስ ነው አስተዳደግሽም
**አያቁም ወሃና ወለዱ ሠማይ**
**ድንግል ተዘጋጀች ለአስርቆ ጸሀይ 2**
ወዳሴሽን ሲያደርስ አባ ጽጌ ድንግል
ከፍ ከፍ እያለ በሠማይ ይበራል
**ምስጋናሽ በዝቶልኝ ለእኔም ለባርያሽ**
**በአበው አጠራር ሶልያና አልኩሽ**

## 342. እናቴ ሆይ ደነቀኝ ፍቅርሽ

እናቴ ሆይ ደነቀኝ ክብርሽ
ያንን ግሩም እሳት ማዘልሽ
ተአምር ነው ለልቤ የምደነቅበት
አለማትን ይዞ በአንቺ ያደረበት 2
ወደት ተጋረደ የእሳት መጋረጃው
ዓለም ያልቻለወን ሆድሽ እንዴት በቃው
መጣጡን መወሰን የሌለበት ጌታ
<u>እንዴት ተወሰነ በማህፀንሽ ቦታ/2/</u>
የኪሩቤል ዘፋን ወደት ተተከለ
ታናሿ ማሻራ ለአንቺ እንዴት ቀለለ
በሆድሽ በግራ ወይንስ በቀኝ ነው
<u>**ለአንቺ የሆነወን ከፍጥረት ማን ቻለው/2/**</u>
በንፋስ ትከሻ ተጭኑን ብንበርም
ይህን ምስጢር ማወቅ ህሊናም አይችልም
ገረድ ከእናትነት እንደምን ያለ ነው
<u>ከገሊላ ማደር ሲባል የሰማነው/2/</u>
በሰሜን በደቡብ በምስራቅ በምዕራብ
ትወልድ ተጋረደ በአንቺ ፍቅር ደባብ
የሚዳሰስትን ያንን ግሩም እሳት
<u>**አጣጠምነው ቀምስን ስጋወን በመብላት/2/**</u>

## 343. ልቤ መልካሙን ነገር አፈለቀ

ልቤ መልካሙን ነገር አፈለቀ/2/
የአዛኝቷን ፍቅር ስለሰነቀ
ልቤ መልካሙን ነገር አፈለቀ
ስምሽን ስጠራ በምኔደበት
ይሰምራል ማንገዴ የልቤ ሚኘት
ሀብት በረከት ነሽ እናቴ ለሁሉ
ይባረኩብሻል የእግዚአብሔር የሆኑ/2/
አትርሺኝ እናቴ በልብሽ ፃፊኝ
ነኝና ብቸኛ ማንም የሌለኝ
የልቤን ታውቂያለሽ ብዙ ሃዘኔን

ሞተሽ ወደ ፅድቁ አድርሺኝ
እኔን/2/
ታላቁን ዘመቻ ጀምሬአለሁና
ቁሚ ካጠገቤ ሀይል ሁኚልኝና
ጌታዬን ላስደስት ሚልካም ይውጣ ከኔ
የቅደስና ምንጭ ሁኚ እናቴ ለኔ/2/
ማቀሉ ስር ቆማሽ ለልጅሽ ስታዝኚ
ተሰጠሽን ለእኛ እናት እንድትሆኚ
ፅድቅን አስተምሪኝ ልደግ እንደ
ዝግባ
ምህረት ተሞልቼ ወደ ቤቱ ልግባ

## 344. ታማልደናለች

ታማልደናለች ታማልደናለች/2/
ሚርያም/2/ ቤዛዊት ዓለም/2/
ሚካኤል ሚልአክ ሊቀ ሚእክት/2/
ዘአወረደከ/2/ሚና ከደሚና/2/
ገብርኤል ሚልአክ አብሰራ ትስብእት/2/
ዘአብሰራ/2/ ለሚርያም ንፅህት/2/
ሩፋኤል ሚልአክ ሊቀ ሚዕከት
ዘአብርሃ/2/ዓይኖ ለጦቢት/2/
ዑራኤል ሚልአክ ለዕዝራ ነብዩ/2/
ዘአስተዮ/2/ ፅዋዕ ልቦና/2/
ሰሎሞን ይቤላ/4/
ዕርግብየ ሠናይትየ ሰሎሞን ይቤላ/2/
ገብረ ሚንፈስ ቅዱስ/2/
ሐዋርያ/2/ ዘእስክንድርያ/2/
ተክለ ሐይማኖት/4/
ሐዋርያ/2/ ዘኢትዮጵያ/2/
ብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳወሎስ
አዕሚዶ/2/ ቤተክርስቲያ/2/

## 345. ውዳሴ ማርያም

ውዳሴ ሚርያም እጮሃለው
ድንግል እናቴን እጣራለሁ
እንደ አባ ኤፍሬም ነይ ባርኪኝ
ወደሰኒ ልጂ በይኝ
ውዳሴ ሚርያም በሰርክ ፀሎት ላይ
// ዜማ ስናደርስ
// ድንግል ትመጣለች
// ከቤተ መቅደስ
// የብርሃን ምንጣፍ
// ከፊቷ ተነጥፏል
// ቅዱስ ኤፍሬም
// ታጥቶ የማኅግናታል
// አባ ህርያቆስ
// ምስጋና ያደርሳል
// የቅዳሴው ዜማ
// ልብን ይማስጧል
// በጎ ነገር ልቤ
// አወጣ እያለ
// ዳዊት በገናወን
// እየደረደረ
// የንፅህናችን
// ማሰረት ነሽና
// አንቺን ለሙጣገን
// ልቡናዬ ይብራ
// ተፈስሂ ድንግል
// አ ቤተልሄም
// ካንቺ ተወለደ
// ሚድሃኔዓለም
// ቅዱሳኑ ሁሉ
// ዙሪያሽ ከበዋል
// አባ ጊዮርጊስም
// ንዒ ድንግል ይላል
// በወርቅ ዙፋን ላይ
// ተቀምጠሽ ሳይሽ
// ልቤ ተሰወረ
// ድንግል በግርማሽ

## 346. በምን በምን እንመስላት

በምን በምን እንማስላት ድንግል ሚርያምን/2/
ምሳሌ የላትም የላትም ከብሯን የሚሞጉን/2/
የማኤ ፅላት ነሽ የምህረት ቃል ኪዳን
የያዕቆብ ማሰላል የአብርሃም ድንኳን
የብርሃን መውጫ የኖህ ድንቅ ሚከብ
የማዕከት እህት **__የሩህሩሃን__**
**__ርግብ/__**2/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ ማስንቆ የጌዲዮን ፀምር
ድንግል እማቤት ናት ያፃድቃኖች በር
ሆና የተገኘች **__የአምላክ ማደር/__**2/
የቅዱሳን እናት የዓለም ንግስት
ችላ ተሸከመች ማላኮት እሳት
ብርሃን ትሁትን ጨለማን ገላልጣ
አማልዳ ታስምረን **__ከዚህ ዓለም__**
**__ጣጣ/2/__**
ከሚር ይጣፍጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቅፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለም ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ፅዮን **__ይድረስሽ ምስጋና/2/__**

## 347. በሃዘኔ ደራሽ ነሽ

በሃዘኔ ደራሽ ነሽ በጭንቀቱ በችግሬ ደራሽ
ነሽ
የአምላክ እናት ጌታዬ እናት
ድንግል እሜቤቴ ወላዲተ ቃል/2/
ሚልካሚቱ ርግብ ድንግል እሚቤቴ
ሚርያም እናቴ ነሽ // ገናና የከበርሽ //
የኃዘኔ ሚጽናኛ // እንባዬን አባሽ ነሽ //
ዋሻ ማጠለያ // የዘላለም ቤቴ //
ማነገድ ስሄድ ስንቄ // ማጠጤ ነሽ
ምግቤ //
እመ አምላክ ስጠራሽ // ይጠፋል
ረሃቤ //
የእናትነትሽን // ፍቅርሽን አየሁት //
ጎጆዬን ስትሞይው // ባዶ የሆነውን //
አንቺ እያለሽልኝ // ምን እሆናለሁኝ //

## 348. እመቤቴ ማርያም ሆይ

እማቤቴ ሚርያም ሆይ ሰላም እልሻለሁ
እንደ ኤልሳቤጥ ዘመድሽ እሳለምሻለሁ
ጭቅቀቴ እንዲወገድ ድንግል በምልጃሽ
የልቤን ልነግርሽ መጣሁ ከደጅሽ
ማከራው ፈተናው ከልቤ ተጋርጦ
እንደምን ልቻለው ልቤ ተስፋ ቆርጦ
ማን አለኝ እንደ አንቺ እንባዬን የሚያብስ
ደስታን አጎናፅፎ የልብን የሚያደርስ
ለችግሬ ደራሽ ማከጠረኛዬ ነሽ
ቋጠሮዬ ይፈታል የልቤን ሳዋይሽ
ይብቃኝ ለውጪልኝ ሐዘኔን በደስታ
ሰላሜ ልሁን ድንግል የእኔ አለኝታ
ከእጅሽ በረከት ሞልቶ ታየ ቤቴ
መንፈሴም እረካች ጠገበች ህይወቴ
የእናትነት ፍቅርሽ ፍጹም ሆነኝ ተስፋ
ትካዜዬም ቀረ ሃዘን ከእኔ ጠፋ
በዘመኔ ሁሉ ድንግል ላማከግንሽ
ከእቅፍሽ ሳልወጣ ሳልርቅ ከቤትሽ
በተከላዎች መሀል ነወና ኑሮዬ
ጥበቃሽ አይራቀኝ ድንግል ከለላዬ

## 349. ትህትናሽ ግሩም ነው

ትህትናሽ ግሩም ነው ደግነትሽም/2/
እናቱ ሆነሻል ለመድሃኔዓለም/2/
ንፅህት ስለሆንሽ // እንከን የሌለብሽ //
የፍጥረታት ጌታ // በአንቺ አደረብሽ //
የድንግል መሚትጥ // ይኸው አስገረመን //
እሳቱን ታቀፈች // የማይቻለወን //
ምርኩዜ ልበልሽ //
ጥላ ከለላዬ //
ጋሻዬ አንቺ ነሽ //
ለእኔ መማኪያዬ //
በዓለም እንዳላጠፋ //
ሕይወቴ ማርዐብኝ //
እንደ ወይን አጣፍጪው //
ሚርያም ድረሽልኝ //
የምከራቅ ደጃፍ ነሽ //
የሁላችን ደስታ //
እሙለፀሐይ ፅድቅ //
የሁሉ ጠበቃ //
ድንግል የድል አክሊል //
ድንግል የፅድቅ ሥሬ //
ድንግል ማሳላል ነሽ //
የተዋህዶ ተስፋ //

## 350. ላመሰግንሽ ማርያም

ላማከግንሽ/2/ ሚርያም የአምላክ እናት/2/
ሚዳሪያ የሆንሽ ዘፋን ለማኮት/2/
ላማከግንሽ በአምላክ ልቦና
ላማከግንሽ ቀድሞ የታሰበ
ላማከግንሽ በማዕት አንደበት
ላማከግንሽ የተማከገነ
ላማከግንሽ ምን ዓይነት ድንቅ ነው
ላማከግንሽ የአንቺ ንፅህና
ላማከግንሽ ታስበሽ ኖረሻል
ላማከግንሽ በአምላክ ህሊና
ላማከግንሽ ሚርያም እናታችን
ላማከግንሽ በአንቺ ደስ ይለናል
ላማከግንሽ ምህረትን የሚያድል
ላማከግንሽ አምላክን ወልደሻል
ላማከግንሽ የሰላምታሽን ድምፅ
ላማከግንሽ ወድያውኑ ስትሰማ
ላማከግንሽ ከፊትሽ ወደቀች
ላማከግንሽ ኤልሳቤጥ ተሳልማ
ላማከግንሽ ድንግል እናታችን
ላማከግንሽ እኛ ደካሞቹን
ላማከግንሽ በረድኤት ጎብኚን
ላማከግንሽ ምልጃሽም አይራቀን
ላማከግንሽ ተማጽነናልና
ላማከግንሽ በአንቺ አማላጅነት
ላማከግንሽ ሁሉን ታደርጊያለሽ
ላማከግንሽ ኪዳነ ምህረት
ላማከግንሽ በመንፈስ ተሞልቶ
ላማከግንሽ አባ ህርያቆስ
ላማከግንሽ ለአንቺ ተቀኝልሽ
ላማከግንሽ ቅኔ መወደስ
ላማከግንሽ አባታችን ኤፍሬም
ላማከግንሽ ያማከግንሻል
ላማከግንሽ ቅድስት ሆይ ለምኚ
ላማከግንሽ አሚልጂን ይልሻል

## 351.በማህጸን ቅኔ

በማህፀን ቅኔ ለሚርያም ተሰማ
በተራራረው ሃገር በኤፍሬም ከተማ
ዮሀንስ ይናገር በረሃ ያደገው
ድንግል ስትናገር ምን እንዳዘለለው
የእናቱ ማህፀን የቅኔ ርስት ሆነች
ድንግል የአምላክ እናት ፊቱ ስለቆመች
በሃሴት ዘለለ ዘሚሪ በደስታ
ከድንግል ሲወጣ ታላቁ ሰላምታ
ከድንግል ማሕፀን ስላየ ጌታውን
ከመወለድ ቀድሞ ሰማ ው መዝሙሩን
ትንቢቱ ሲፈፀም በሆዱ ሲነግስ
ሠገደ ለአምላኩ የ 6 ወር ጽንስ
ጀማሪ ስብከቱን ገና ሳይወለድ
ተፈጥሮ ሜች ቻለ ነብዩን ለማከድ
አፉ ተከፈተ በታላቅ ምከጋና
ከእናቱ ማህፀን ድምፁን አሰማና
የዮሃንስ እናት ኤልሳቤጥ ገረማት
ልጇ በማህፀን ቅኔ ሲቀኝላት
ድምፁን ከፍ አረገች አለም እንዲሰማ
ሞላት መንፈስ ቅዱስ በመዝሙሮ በዜማ

## 352. ቋንቋዬ ነሽ ድንግል

ቋንቋዬ ነሽ ድንግል መግባቢያዬ
ሜለስ የማገኝብሽ ከጌታዬ/2/
ባንቺ ቀርቤአለሁ ከአምላኬ ፊት
ቤቱ ሜቶልኛል በበረከት /2/
በምን ስራዬ ነው በፊትሽ የቆምኩት
መቼ በቅቼ ነው ስመኝ የጠራሁት
አስታራቂ እናት አንቺን ስለሰጠኝ
ስለቃልኪዳንሽ አቤት ልጄ በይኝ /2/
ቅድስና ህይወት ከኔ ተሰወሮ
በወሸት በሀሜት አንደበቴ ታስሮ
በእሜሜላክ ምልጃ አዲስ ሰው ሆኛለሁ
እንደሜላእክቱ ይኸው እዘምራለሁ /2/
ስለ እሜሜላክ ብሎ ያፈረ የለም
በአንቺ ያለከበረ ሰው አይገኝም
እንደ ባለሚግ እኔም ሰው መባሌ
አንቺን አግኝቼ ነው ድንግል ማሳሌ
/2/
ሰላም ለኪ ብዬ ስጀምር ጸሎቴን
ሀሴት ይመላዋል ሜላ ሰውነቴን
እንደ ቅዳስ ኤፍሬም በምስጋናሽ ልፅና
በእጅሽ ያለው አምላኬ ነው እና /2/

## 353. ድንግል ወላዲተ ቃል

ድንግል/2/ ወላዲተ ቃል/2/
አሟሟሽ በጥር ነሀሴ መቃብር ድንግል
የአንቺስ ለብቻው ነው ትንሳኤሽ ሲነገር
ድንግል
ሥጋሽ በምድር ላይ የታለ እንደ ፍጡር
አርጓል ወደ ሰማይ ከክርስቶስ ማንበር
ሥጋሽን ሲያሳርጉ ማዕክት በሰማይ
ድንግል
ቶማስ በደመና ሲመጣ መንገድ ላይ
ድንግል
መገነዝ ተረከበ ለሃዋርያት ሊያሳይ
ድንግል
ትንሳኤሽን ሸተው ግራ ሲገባቸው ድንግል
ሐዋርያት ያመው ተገለፅላቸው ድንግል
ተቀብራ አልቀረችም በምድር ከደጁ ድንግል
ወደ ላይ አረገች እሷም እንደ ልጇ
ለሞት ሲጓጉ የድንግል ትንሳኤ
ድንግል
እርገቷን አወቁ በብዙ ሰላኤ ድንግል
እኛም እንፀልይ ደጃችን እንዝጋ
ድንግል
ከወላዲት አምላክ እንድናገኝ ዋጋ

## 354. እናት አለኝ

እናት አለኝ የምታብስ እንባ
አያታለሁ ስወጣ ስገባ
ኪዳነ ምህረት/2/ አምባ ማጠጊያ ናት

ሐዘን ሰጥታኝ ከበለሱ ፍሬ
እራቁቴን ብቆምም አፍሬ
ልብሴን ይዘሽ ወደ እኔ መጥተሻል
ደጓ እናቴ ቤቴን አደምቀሻል
ኪዳነ ምህረት------

ለዘለዓለም ንጽህት በመሆኗ
ከእኔ ጋር ነው ህያው ቃል ኪዳኗ
ደስተኛ ነኝ ሀዘኔን አልፌ
አፅናኝ ሆናኝ የሚቀል ስር ትርፌ
ኪዳነ ምህረት----

ከጥፋቱ ወሃ ሚሪፊያዬ
ሚከቤ ነሽ ከሞት ማምለጫ
የአምላክ እናት ምልጃሽ ሆኖኝ ክብሬ
በህይወት አለሁ ጥልቁን ተሻግሬ
ኪዳነ ምህረት----

በእናትነት ህይወቴን ጎብኝታው
ልቤ አረፈ ተነቅሎ በሽታው
ሰንሰለቴ ከእጄ ተቆረጠ
ሜራራዬ በልጅሽ ጣፈጠ

## 355. ለጥያቄዬ መልስ ስላጠሁ

ለጥያቄዬ ሜልስ ስላጣሁ
መጣሁ ከደጅሽ ሰላኤ ገባሁ
ማን አፍሮ ያውቃል ባንቺ ለምኖ
በኪዳንኪ ተማፅኖ
የነፍሴ እረፍቷ ታዛ ማጠጊያ
ካንቺ ተገኝቷል የሞቴ መውጫያ
በሠላታሽ ደምጽ ተባርኳል ቤቱ
የጌታዬ እናት ለእኔም እናቴ
ሚርያም ኩኒ
ለህይወትየ ፀወኖ
እስመ ተማፅጸንኩ
እንሰ ተማፅኖ
ለሥዕልኪ ሥዕለ አድኅኖ ንሰግድ ለኪ
ለጥያቄዬ------

ቀንን ስናፍቅ በሌሊት ሆኜ
አላተረፍኩም በሰው ታምኜ
ቁልፋ ልጅሽ ነው ለቋጠሮዬ
አሳስበሽልኝ አልፏል ስቃዬ
ኪዳነምሕረት ኩኒ ለልቦናየ ብርሃኖ
እስመ ተማኅፀንኩ አንሰ ተማኅጽኖ
በሥዕልኪ ሥዕለ አድኅኖ
ንሰግድ ለኪ
ለጥያቄዬ---------
ጉልበቴ ዝሎ ቀልዬ ሳለሁ
በኪዳን ጥላሽ ተስፋ አግኝቻለሁ
ደጅሽ መጥቼ ኃይሌ ታደሠ
ያሳዳጆቼ ምክር ፈረሰ

ወላዲተ አምላክ ኩኒ ለዕርቃንየ ከዳኖ
እስመ ተማኅጸንኩ አንሰ ተማኅፀኖ
በሥዕልኪ ሥዕለ አድኅኖ ንሰገድ ለኪ

የዝናቡ ምንጭ ፈጣን ደሜ
ከሴቶች ሁሉ ክብርሽ ገናና
እንድያ ልጅሽ ወይን አድርጎኛል
ከትላንት ይልቅ ዛሬ ባርኮኛል
ለይያቄዬ----------

## 356. ድንግል ማርያም

ድንግል ሚርያም በቤተምቅደስ
አስምታ ትናር ነበር
ሜልአኩ ገብርኤል ከነገረኝ በቀር
ሌላ ምንም አላወቅ ያወቃል እግዚአብሔር/2/

ከመቅደስ ቁጥ ብዬ ትንቢት እየሰሜሁ
ሐር ወርቁን አስማምቼ ጥበብ እየፈተልኩ
ሳለሁ በማረም ያንን ቃል አስቤ
አምላክ ሰው ሆነ ብኝ ተመሠጠ ልቤ
ማ ናት ብዬ ሳስብ ያቺ ብላቴና
ገብርኤል ደረሰ
ዞፋኑ አደረገኝ
የባሪያይቱን ወርደት ተሜልከቷልና

እንዴት ያለ ሜህጸን ሰሜይን ይሆናል
የልዐሉ ዞፋን ወዴት ይተከላል
እያልኩኝ ስጠይቅ በልቤ ለራሴ
የመንፈስ ቅዱስ ሃይል አደረ በእራሴ

እሳት የሜይበላው ሀሜልሜል አይኖርም
እንዲህ ያለ ቅጠል ናዝሬት አይገኝም
ህሊናዬ መጥቆ ሰብር ወደሲና
አንቺ እኮ ነሽ አለኝ ገብርኤል መጣና
ሜኅት ብዬ----

እንዴት ከድሃ ቤት ይሄ ንጉስ ያድራል
ለእርሱ የተገባ ከወዴት ይገኛል
ገሊላን አሰብኳት ዛሬ በህሊና
ለካስ ተሸንፏል በባሪያው ትህትና

## 357. አወድሰኝ ኤፍሬም

አወድሰኝ ኤፍሬም ብላ ጠየቀችው ድንግል
እናታችን
ባርከኒ ብሎ ወገቡን ታጠቀ ኤፍሬም አባታችን
የልጄ በረከት ይደርብህ ብላው ጀመረ ምስጋና
ወደ ብርሃን ድንኳን ወደ ተከበረው ደራሲው
ገባና 2
ልቡ ያዘነ አዳም ሊያድን ጌታ ወደደ
ዳግሜቱ ሰሜዩ ሜደሪያው ልትሆን እርሱ ፈቀደ
የሰሜዩ ምስጢር በሜህፀንሽ ተከናወነ
ከዘሩ ቀርተሽ በንፅህናሽ የሰው ዘር ዳነ
ሰአሊ ለነ /2/
አእምሮወን ልቡን ሳይብን አሳድሪብን
ጸጋወን ክብሩን እንዳይነሳን ለምኚልን
በሄዋን ምክንያት በለሷን በልተን ገነት
ቢዘጋ

በአንቺ እናትነት ዳግም ተዛመድን
ከአምላካችን ጋር
ትወልዱ ሁሉ ስምሽን በክብር አመሰገነ
የሰኦል ቀንበር በላያችን ላይ ስላልተጫነ
ሰአሊ ለነ /2/
የእዳ ደብዳቤ ተቀዳደደ የባርነቱ
አዳም ሄዋን ከዕስራታቸው ወጡ ተፈቱ
የሰኦል ፅልመት በልጅሽ ጠፍቶ ብርሃን ሆነ
ዕረፍት አገኘን የምህረት ዓመት በአንቺ ዘመነ
ሰአሊ ለነ /2/
ሜኬ በሲና ሳትቃጠይ ያየሽ ሀሜልሜል
እግዚአብሔር ሚርጦሽ በሜህፀንሽ ዞፋኑን
ተከሏል
የዲያብሎስን ጥበብ እንዲያፈርስ አምላክ
ሰው ሆነ
በልጅሽ መሞት መዳናችንም ተከናወነ
ሰአሊ ለነ /2/

## 358. የጠሩሽ አንቺን ተማፅነው

የጠሩሽ አንቺን ተሜፅነው የዳኑብሽ
የበላየሰብ እሜቤት የአምላክ እናት
ድንግል አዛኝቱ ሚርያም ቅድስት
በቃል ኪዳንሽ ብዞዎች ድነዋል
በምልጃሽም ፅድቅን አግኝተዋል
የአምላክ ቸርነቱን አይተዋል/2/
የእሳት ባህር በአንቺ ተሻግረዋል
የሰይጣንን ቁልፍ በአንቺ ድል ነስተዋል
ለሰሜያዊው ክብር በቅተዋል/2/
ነፍሳቸውም ፅድቅን አግኝታለች
ህይወታቸውም በአንቺ ትድናለች
ድንግል ሆይ አትጣይን ትላለች/2/
እኔም በአንቺ እታመናለሁ
የአምላክ እናት አትርሺኝ እላለሁ
በአማላጅነትሽ እድናለሁ/2/
እኛም በአንቺ እንታመናለን
የአምላክ እናት አሳስቢ እንላለን
በአማላጅነትሽ እንድናለን/2/
ምዕመናንም በአንቺ ይታመናሉ
አምክ እናት አሳስቢን ይላሉ
በአማላጅነትሽ ይድናል/2/

## 359. የልቤን በልቤ ይዤ

የልቤን በልቤ ይዤ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
የሆዴን በሄዴ ይዤ ከፊትሽ ቆሜአለሁ
ካለኝ ነገር ሁሉ አንቺን ሚርጫለሁ
እናቴ ሆይ ስሜኝ አሜልጅኝ እላለሁ
ግራ ቀኝ ህይወቴ በእሾህ ታጥሮብኛል
በፊት በኋላዬ ማሰናክል በዝቷል
እኔስ ያለምርኩዝ ጉዞዬ ከብዶኛል
እምአምላክ ደግፊኝ እጄ ተዘርግቷል/2/
ቆሜ ስራመድ ጤነኛ እመስላለሁ
የወስጤን ጎዶሎ እኔ መች አወቃለሁ
ድንግል ሆይ ቅረቢኝ አይዞህ ልጄ
በይኝ

የጭንቀቴን ካባ አወልቀሽ ጣይልኝ/2/
እናት ያለው ሰው ፍጹም አይተክዝም
አንድ ቀን ይስቃል አልቅሶ አይቀርም
ሀዘኔን በደስታ ለወጪው እናቴ
በሃሴት ልዘምር በቀረው ህይወቴ/2/
አሁንም ጎዶሎ በወስጤ አለና
ድንግል ሆይ ቀረቢኝ ዛሬም እንደገና
ለዚህች ለትንሷ ለጥቂቷ እድሜ
እንደከፋኝ አልኑር ቀና አርጊኝ
እናቴ/2/

## 360. ማርያም በስምሽ

ማርያም በስምሽ ይዘናል ቀኖና
ትንሳኤሽን ልጅሽ ያሳየናልና
ፆም ማለት እንዲህ ነው ይኸው ነው ስርዓቱ
ሐዋርያት ፆመው ለእኛ አበረከቱ
ነፍስና ሥጋችን በመብል ተጣልተው
ሽማግሌ ሆኖ ፆም አስታረቃቸው
አብረው እያደሩ አብረው እየዋሉ
አያምርም አይሰምርም በመብል ሲጣሉ
ነፍሳችን ከስጋ ማለየቷን አወቃ
የዓለም ተደላዋን ደስታዋ ንቃ
በፆም በሱባኤ ትኖራች ታጥቃ
ነፍስም ለስጋዋ ትነግረው ጀመረች
በብዙ ምሳሌ እያመሳሰለች
ሥጋዬ ሞኝ ነህ መብልን አትወደደው
ከአዳም አንስቶ ከመጀመሪያው ሰው
መብል ሲጎዳ እንጂ ሲጠቅም መች አየነው/2/

## 361. የአብ ቃል አክብሮሽ

የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ
እግዚአብሔር በቃሉ ፍጹም ያከበረሽ
የምንመካብሽ ማለላችን ነሽ/2/
ቅድስና ለአንቺ ፅድቅም ለአንቺ ሆኖ
ዓለም የፈጠረ በአንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ህይወት ያፈራሽ
አንቺን ለሚጠ አንቺን ላነጻሽ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላክሽ/2/
አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ
ኤፌሶን ወንዝ ወርቅ የሚፈስብሽ
የጊዮን ሜበል ኢትዮጵያን የቀደሰሽ
ዮርዳኖስ ሆነሽ አህዛብን ፈወሽ
በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ/2/
ጸአዳሽን ወዶ ወልድ ዋህድ ዋጀሽ
አብም በሠምሮት በህሊናው ጸፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ
እመካብሻለሁ እሜቴ ስልሽ/2/
ወልድ በመወደዱ ከአንቺ መወለዱን
ንጹህ ሆኖ አግኝቶሽ ቅዱሱ ስጋሽ
ለቃሉ ሚሪያ ጽላትና ታቦት
በብሩህ ደመ ተመስለሽለት
ከስጋሽ ተከፍሎ ከደምሽ ደም ወስዶ

## 362. የሠማይ የምድር

የሰማይ የምድር የአርያም ንግስት
አንቺ ነሽ እሜቴት የአምላክ እናት
እኸ ድንግል አሜልጂን እኽ ቅድስት ተራጂን
ለሐዋን ተስፋዋ ለአዳም ዘር ሕይወት
ለደህነቱ ምክንያት አንቺ ነሽ ብጽህት
የኦሪት መጽናኛ ሐዲ ኪዳን በር
የወንጌል መሠረት የአምላክ ማነደር
የአብርሃም እርሻ የምስጢር ዋሻው
እናትና ድንግል ሁለቱን ሆንሺው
የኤፍሬም ወዳሴ ያየሬድ ወብ ዜማ
የማትጠልቂ ጸሐይ የሃይማኖት ሻማ

## 363. ወየው እያለች

እሜቴ ማርያም ወየው እያለች
አምርራ አለቀሰች እየተዳፋች
ወየው አንድ ልጄ
እህቴ ሰሎሜ ወዴት ነው ያለሽው
በግብጽ በረሃ አብረሽኝ የዞርሽው
ወየው አንድ ልጄ
ዘመዴ ኤልሳቤጥ ወዴት ነው ያለሽው
እንድታላቅሰኝ ወየው እያለች
ወየው አንድ ልጄ
የሚረ ሀዘን ዛሬ ደርሶብኛል
ልጄን አንገላተው ገርፈው ሰቅለውታል
ወየው አንድ ልጄ
ማቀሉ ስር ሆና እያለቀሰች
ወየው መድሃኔቴ ወየው እያለች
ወየው አንድ ልጄ
አልችልላት ብሎ የወላድ አንጀት
ደም እያለቀሰች እንባዋ አልቆባት
ወየው አንድ ልጄ
ተጠሞሁኝ ስትል ጠቴን ጨቀው
እንደ ልጅነትህ ባጠበህ ምነው
ወየው አንድ ልጄ
አንድ ልጄ እኮ ነው የሌለው ወንድም
እረ እንዴት ልቻለው መድሃኔዓለም

## 364. የልቤን ሁሉ

የልቤን ሁሉ ለማን ላማክር
እሜቴ ሆይ ከአንቺ በቀር
የደካማው ሰው ማጠጊያ እኮ ነሽ
ሃዘን ጭንቀቴን የምረሳብሽ
ቅዱሳን አበው አንቺን ሚጠ/2/
ከሲኦል ዓለም ስላማለጡ
ፃድቅ በስራው ያኔ ሲድን/2/
እጠራሻለሁ ድንግል አንቺን
የጭንቄ ደራሽ አክከሌ ነሽ/2/
ቂም በቀል አያውቅ የዋህ ልብሽ
ልቤ ለፍቅርሽ ሰፊ ስፍራ አለው/2/
በአዘንኩኝ ሠዓት እጠራሻለው
ዋሴ ነሽ ለእኔ ድንግል እናቴ/2/
ስምሽ ጠበቀኝ ከልጅነቴ
ሁሌጊዜ ለእኔ የሆንሽኝ/2/
ምን ልበል ለአንቺ ቃላት የለኝ
ለአዘንኩኝ ለእኔ ደስታዬ ነሽ/2/
ያረጋጋሽኝ ፈጥነሽ ደርሰሽ

ስምሽ ሃጥአንን የሚቀድስ/2/
ከሞት ወደ ህይወት የሚመልስ
የማገዴ ስንቅ የርሃቤ ሞሻ/2/
ለታመመ ሰው ነሽ ሚዜወሻ
የተማጸነ በስምሽ አምኖ/2/
ማን አፍሮ የወቃል አንቺን ለምኖ

## 365. ግርማዬ ነሽ ድንግል

ግርማዬ ነሽ ድንግል ሁል ጊዜ መፅናኛ
ስንገላታ ድጋፍ ስጠፉ ማግኛ
ፍቅርሽን በልቤ ሳይልኝ እናቴ
እንዳማሳግንሽ ተከፍቶ አንደበቴ
አማናዊት ታቦት አምላክ ያደረብሽ
ክብሩን በአንቺ ገልጦ ሰወን ያዳነብሽ
ምክንያተ ደህን የአዳም ዘር ትምክህት
እቴ መሸራዬ ነይ በረድኤት
ፍቅርሽ ከወይን ፍሬ እጅጉን ይበልጣል
ልቤን አንበርክኮ ምርኮኛ አድርጎታል
ነፍሴ ተሳፈረች በሰረገላሽ
ከአንቺ ጋር ልትኖር ልትገዛልሽ
የፅዮን ደናግል ለምስጋና ወጡ
ንግስቲቱ መጥታ እንዳትቀማጡ
ከዕልፍ አእላፋት የተሚጠች
ከደጃችሁ አለች ጌታን ያስገዛች
ልብስሽ መአዛ አለመን ያወዳል
ስምሽ አጋንንትን ፈፅሞ የርቃል
ቃልሽ ያሚ ነው ለሰሚው ይደንቃል
አጥንት አለምልሞ ነፍስ ይቀድሳል

## 366. አድኘኝ እናቴ

አድኘኝ እናቴ ከሥጋ ፈተና
ሥጋዬ ከኃጢያት ከቶ አልራቀምና
ሸክሜ የከበደኝ ብቸኛ ሆኛሁ
አትለይኝ ድንግል አደራ እልሻለሁ
የአማኑኤል እናት የተዋህዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሃል እንድትሆኚን ሃይል
ምንም ቢበዛብሽ የእኛ ጉስቁልና
ከእኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና
ተስፋዬ ነሽና እማካብሻለሁ
ግራ ቀኝም አልል ምርኮኛሽ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ
እግዚአብሔር ይመስገን ከአንቺ
ያስጠጋኝ/2/
በሥጋ ደክሜ በነፍሴ እንዳልጠፉ
እማፀንሻለሁ ድንግል የእኔ ተስፋ
የመንግስቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ
መልካም ስራ ማስራት እኔን አስተምሪኝ
አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁም የደረቀ ህይወት የተለየው
በመሃከል ገብተሽ መዪ የጎደለወን
ሰርጉ ተደግሷል ጎብኚልን ጓዳወን

## 367. የብርሃን ጎርፍ ናት

የብርሃን ጎርፍ ናት ድንግል እናታችን
ከሰማዪ እያበራ ደስ አለው ልባችን
ፍቅርሽም ሰላምሽም ደህንት ይሁነን አአ
ፍጥረት በሙሉ/2/ ፊትሽ ይወድቃሉ
ጸጋሽ ይድረሰን/2/ ይሰጠን እያሉ
የእኔ ልብ ምን ፅድቅ አለው አንቺን
ለማስተናገድ
የኃጢያት ጎተራ ነው የተሞላ በስስት
እረ እንዴት/2/ ድንግል ትኑርበት
አአ
አትጸየፍም እኔን ልብ ታሰናዳዋለች
ስለ ኃጢያቴ የእኔ እናት ምልጃ
ታቀርባለች
ልባቸወን የዘጉ ድንግልን ላለማስገባት
ልቦናቸው ይመለስ እንጸልይ ለዚህ ጥፋት
አምላክን ይዛ ነው ድንግል የምትመጣው አአ
እርሷን ስንመልስ ልጇን ነው የምናስቀይመው
እርሷን ስንመልስ ጌታን ነው የምናስቀይመው

## 368. እመቤቴ የአምላክ እናት

እመቤቴ የአምላክ እናት/2/
መንፈስ ቅዱስ ያረጋጋት
በፍጥረታት የተወደደች
በሰማያት ተመስገነች
ግርማ ለብሳ ግርማ ያላት ድንግል
ቤተ መቅደስ ስታገለግል
ቅዱስ ፋኑኤል ክንፉን ከልሎ
መና ሰጣት ትመግብ ብሎ
በትህትና የተወደደች
ለጌታ ክብር የተወሰነች
እም ቅድመ ዓለም የተዘጋጀች
የአማኑኤል እናቱ እኮ ነች
የከበረች አምላክ በመውለድ
በመላዕክት የምትወደድ
በሰማዕታት የምትፈቀር
የቅዱሳን የደስታ ባህር

## 369. የአብ ቃል አክብሮሽ

የአብ ቃል አክብሮሽ እናት ያደረገሽ
እግዚአብሔር በቃሉ ፍፁም ያከበረሽ
የምንመካብሽ ማሳላል አንቺ ነሽ/2/
ቅድስና ለአንቺ ጽድቅም በአንቺ ሆኖ
ዓለምን የፈጠረ በአንቺ ተወስኖ
የገነት ፍሬ ነሽ ሕይወት ያፈራሽ
አንቺን ለሚረጠ አንቺን ላነጻሽ
ምስጋና ይድረሰው ለቸሩ አምላክሽ/2/
አዳም የኖረብሽ የኤዶም ገነት ነሽ
የኤፈሶን ወንዝ ወርቅ የሚሊልቅብሽ
የግዮን ሚዐበል ኢትዮጵያን የከበብሽ
ዮርዳኖስ ሆነሽ አህዛብን ፈወስሽ
በልጁ ቃልነት አብም አከበረሽ/2/
ፀአዳሽን ወዶ ወልድ ዋህድ ልጅሽ
አብም በሰማያት በህሊናው ፃፈሽ
መንፈስ ቅዱስ መጥቶ አንቺን አከበረሽ

እመካብሻለሁ እሚቤቴ ስልሽ/2/
ወልድም በመወደዱ ከአንቺ መወለዱን
ንጹህ ሆኖ አግኝቶት ቅዱሱ ስጋሽን
ለቃሉ ሚደሪያ ፅላትና ታቦት
በብሩህ ደመና ተመስለሽለት
ከሥጋሽ ተከፍሎ ከደምሽ ደም ወስዶ
ከነፍስሽ ነፍስን <u>ፍፁም ተዋህዶ/</u>2/

## 370. <u>*እመቤታችን ለአንቺ*</u>

እሚቤታችን ለአንቺ ሰላምታ ይገባሻል/2/
ከሴቶች ሁሉ/3/ ተመርጠሻል
ሐርና ወርቁን እያስማማች ስትፈትል/2/
ተዘጋጀላት/3/ የመሚጥ ዕድል
እያረጋጓት የሰማዩ መላዕክት/2/
ቤተ መቅደስ ኖረች/3/ 12 ዓመት
መንፈስ ቅዱስም እንደቀረባት
አወቆ/2/
ሰገደላት/3/ ዘካሪያስ ወድቆ
መንፈስ ቅዱስም እንደ ቀረባት አወቃ/2/
ተሳለመቻት/3/ ኤልሳቤጥም ወድቃ
አያሳዝንም ወይ የሚርያም ትህትና/2/
ውሃ ስትቀዳ/3/ የአምላክ እናት ሆና
የምንጭ ውሃ የሚያመለክተው/2/
የአምላክ ማኛ ምንጭ/3/ እርሷ መሆኗን ነው

## 371. <u>*ጌታዬ ከሰጠኝ*</u>

ጌታዬ ከሰጠኝ አልፈራም ልወስድሽ/2/
የሀዘኔ መርሻ ሚሪያም እናቴ ነሽ
እናት አግኝቻለው ከመስቀሉ ግርጌ
ስሚን እየጠራሁ ከፍ እንዲል ሚዕረጌ
ምርኩዝ ድጋፍ ሆኖኝ ድንግል ሆይ ፀሎትሽ
በእፎይታ ሞልቶኛል የሰላምታ ድምፅሽ
ፍጹም አይረሳኝ ገብቶ በደም ስሬ
ይቀሰቅሰኛል ክብርሽ ለዝማሬ
በልጅሽ መከራ ቀራንዮ ያለሽ
አትዘነጊኝም ዛሬም ከእኔ ጋር ነሽ
መታወክ መጨነቅ ከቤቴ እንዲነቀል
የበረከቴን ቁልፍ ሰጥቶኛል ከመስቀል
ከጣሪያዬ በታች መጨደስታ
ለጠቆረው ፊቴ እሚቤቴ አብርታ
በራስ ቅል ተራራ በነፍስሽ ሰይፍ አልፎ
አሳረፈኝ ፍቅርሽ በልቤ ተፅፎ
እነኋት እናትህ ሲለኝ በርትቻለሁ
በልጅነት ክብር ከፊትሽ ቆሜአለሁ
የመስቀል ስጦታ እነኋት እናቴ
ማንንም ሳልፈራ ወሰድኳት እቤቴ
በመስቀል ላይ ሆኖ ልጅሽ ራራልኝ
በእናትነት ፍቅርሽ ቤቴን ሸፈነልኝ
በሚያፅናናው ቃሉ መሰበሬን ክሶ
በልቤ ተከለ አፅናኟን ምሶ
ሞኝነት አይደለም ነገረ መስቀሉ
እጅግ ማትረፊያ ነው አንቺን መቀበሉ

## 372. <u>*ውብት ነሽ*</u>

ወፀት ነሽ ለቤቴ ለኑሮዬ ፋና
ድንግል ሆይ አትለይኝ ብቻዬን ነኝና/2/
በሀዘን ጠቋቁራ ተከፍታለች ነፍሴ
አጎንብሻለሁኝ አፍሬ በለምኜ
ወልቋል ከላዬ ላይ የብርሃን ልብሴ
ሀብቴ አንቺ ብቻ ነሽ ያለሽኝ ሞገሴ/2/
ለአምላኬ የማቀርበው አጣሁ በጎ ስራ
ነፍሴ ተጨነቀች በምግባሬ ሚራ
ጥላሸቱ በዝቶ ተዳፍኗል ጎጆዬ
ብርሃን የለወም ካልበራሽ ሻማዬ/2/
የምታመንበት አንዳች ነገር የለኝ
በነፍስም በስጋ ሁሉ የጎደለኝ
እጠብበቃለሁ የእጅሽን በረከት
ከቤቴ ላይ አርፎ እስከባረክበት/2/
የጎጆዬ ክብር የቅጥሬ ድምቀት ነሽ
አይኔን የምትሞይው በመቅረዜ በርተሽ
የፅልመት ጭላንጭል ጠፍቷል የለም ዛሬ
የብርሃን እናት ስላለሽ ከበሬ

## 373. <u>*ለምኚ ድንግል ለምኚ*</u>

ለምኚ ድንግል ለምኚ/2/
ለኃጥአን/3/ አይደለም ለፃድቃን
ለምኚ ታላቅ ስጦታዬ >> አዛኝ ሩህሩህ ነሽ
>> የጌታዬ እናት >> ፀጋን
የተሞላሽ
>> የአምላክ ሚደሪያ >> ለምነሽ
አስምሪኝ
>> አማፃዊት ፅዮን >> ከእኔ
አትለይኝ
>> ሐዘንሽ ሐዘኔ >> ለእኔ ይሁን
ድንግል
>> የተንከራተትሽው >> በሃገረ
እስራኤል
>> ትዕግስትሽን ሳየው >> ልቤ
ይመሰጣል
>> የሀዘን እንባ ጎርፍ >> ኣይኔን
ይሞላዋል
>> በቀራንዮ አንባ >> በዚያ የፍቅር ቦታ
.. በዕግረ መስቀሉ ሥር >> ከክርስቶስ ጌታ
>> ለእኛ ተሰጥተሻል >> እናት እንድትሆኚን
>> ልጆችሽ ነንና >> ምልጃሽ አይለየን
>> አንደበቴን ጌታ >> በምስጋና
መላው
>> ደስ ይበልሽ ብዬ >> እኔም
ላመስግናት
>> አንደበቴን ጌታ >> በምስጋና
መላው
>> ደስ ይበልሽ ብዬ >> እኔም
ላመስግናት

**በሃዘኔ ደራሽ ነሽ**

በሃዘኔ ደራሽ ነሽ በጭንቀቴ በችግሬ ደራሽ
ነሽ

የአምላክ እናት ጌታዬ እናት
ድንግል እማቤቴ ወላዲተ ቃል/2/
ሜልካሚቱ ርግብ ድንግል እማቤቴ
ሚርያም እናቴ ነሽ //
ከፍጥረታት ሁሉ //
ገናና የከበርሽ //
የኃዘኔ መጽናኛ //
እንባዬን አባሽ ነሽ //
ዋሻ ማጠለያ //
የዘላለም ቤቴ //
ማንገድ ስሄድ ስንቄ //
ማጠጤ ነሽ ምግቤ //
እመ አምላክ ስጠራሽ //
ይጠፋል ረሃቤ //
የእናትነትሽን //
ፍቅርሽን አየሁት //
ጎጆዬን ስትሞዪው //
ባዶ የሆነውን //
አንቺ እያለሽልኝ //
ምን እሆናለሁኝ //

## 374. የዶኪማስ ጓዳ

የዶኪማስ ጓዳ ሆኖብኛል ቤቴ
ያንቺን ድንቅ ስራ ናፍቃለች ህይወቴ
ጊዜዬ እናዳያልፍ በዋዛ ፈዛዛ
ያለኝን ሰምቼ ለእርሱ እንደገዛ
የልቦናዬ ጋን ባዶ ሆኗልና
አሚልጅኝ ከልጅሽ በቃሉ እንድሞላ/2/
ማነው ወስጠን ያየ የጎደለውን
የዶኪማስን ልብ ያስጨነቀውን
እስኪ እንጠይቀው ዕድምተኛውን
ወይኑን አጣጥሞ ያደነቀውን/2
አስቀድሞ ያለኝ መናኛ ነበረ
አሁን ግን ምስጢሩን ልቤ ሚሚ
የአንቺን እናትነት አምኖ ተናገረ
ድንቅ ስራሽንም ለዓለም ማከረ/2/

## 375. ኪዳነ ምህረት

ኪዳነ ምህረት እማቤት/2/
ነይልን/2/ ካለንበት
ከሰማዮት በላይ ካለው ከሚዳሪያሽ/2/
ዝማሬ ከሞላው ከዘላለም ቤትሽ
የምድር ፍጥረታት ሚርያም/2/ ሲሉሽ
የቃል እናት እማቤቴ ነይ በሰረገላሽ/2/
ከፀጥታ ወደብ ከፍቅር አወድማ/2/
ከሰላሙ መንደር ከእውነት ከተማ
ሰዓሊ ለነ ቅድስት ውዳሴ ሲሰማ/2/
ከሚካኤል ከገብርኤል ጋር ነይልን
ከራማ/2/
ዘርፋፋ ቀሚስሽ ይወረድ ከሰማዮት/2/
ዕንባችን የታብስ በአንቺ አማጅነት
የፅዮን ዝማሬ ተሞላ ነፍሳችን/2/
ንዒ/3/ እንበል እንደአባቶቻችን/2/
ፍጥረታት ሊድኑ በአማላጅነሽ/2/
የዘለዓለም ኪዳን አማኑኤል ሰጠሽ
ትወልድ ይህን አምኖ ብፅዕት ይሉሻል/2/
እናቴ መመኪያዬ ምርኩዜ ሆነሻል/2/
የልብን ሲያዋዩሽ ሰምተሽ ዝም አትይም/2/
ችግረኛን አይቶ ልብሽ አይጨክንም
ከዓይን ጥቅሻ ፈጥነሽ ትደርሽለታለሽ/2/
ከሐዘን ከመከራ ታሳርፊዋለሽ/2/

## 376. አንቺ ነሽ ተስፋው

አንቺ ነሽ ተስፋው ለአዳም ኪዳነ ምህረት
በተሰደደ ጊዜ ከገነት/2/

## 377. ኪዳነ ኪኮነ

ኪዳነ ኪኮነ/3/ኪዳነ ምህረት
ለሃጥአነ ተስፋነ /2/
ቤዛነ ኪዳነ ምህረት

## 378. ኪዳነ ምህረት እናቴ

ኪዳነ ምህረት እናቴ አሚልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የፍቅር እናት ነሽና አሚልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የሠላም እናት ነሽና አሚልጅኝ እኔን ከልጅሽ
የተገለጠው ብርሃን ከምስራቅ
የተወለደው
በፍቅር ሰንሰለት አስሮ ይህንን አለም
አዳነው/2/
በርሃውን ባሰብኩት ጊዜ የግብጽን የአሸዋ
ግለት
አንቺ ትንሽ ብላቴና እረ እንዴት ቻልሽው
በእውነት/2/
ዝም ብዬ ይደንቀኛል የአምላክን ስራ
ሳስበው
ምክንያት አንቺን አድርጎ ይህንን
አለም አዳነው/2/

## 379. ኪዳነ ምህረት ለእኔ

ኪዳነ ምህረት ለእኔ መመኪያዬ
ለችግሬ ደራሽ ነሽ ማጠለያዬ
ህይወቴ ጎስቁሎ በነፍሴ ብዝልም
በምልጃሽ ታምኜ በኪዳንሽ ልቁም
እጅግ ምስኪን ሆኜ ለሰዎች ብታይም
ሞልቶ የተረፈ ጥሪት ባይኖረኝም
አንቺ ካለሽልኝ ጓዳዬ ሙሉ ነው
አፍሮ አያውቅምና የተማፀነሽ ሰው
ዲያብሎስ እቅዱን በልቤ ቢያገባ
ተገፍቼ ባጌጥ በሰናኦር ካባ
የኃጢአን ደመወዙ እንዳይከፈለኝ
በሞት እንዳልጠፋ ድንግል ተለመኚኝ
ወገን የለኝ ዘመድ ፍፁም ከአንቺ
በቀር
እኔን የሚረዳ በዓለም ስቸገር
አይዞህ በይኝና ደግፊኝ እናቴ
የፀጋ ልብስ ሁኚኝ ሰራቆት ህይወቴ
ነፍሴ እንድትቀደስ ከርኩሳት አምልጣ
ከሴኬም ልሰደድ ወደ ቤቴል ልወጣ

ገሪዛን ልበልሽ ድንግል ሜሻዬ
እዮአታም ልጅሽ መጣሁ አንቺን ብዬ

## 380. ኪዳነ ምህረት እናቴ

ኪዳነ ምህረት እናቴ
ፈጥነሽ ደራሽ ነሽ በሃዘኔ/2/
የከበበኝ ጭንቀት ተወግዷል
ፍቅርሽ እምአምክ እኔን ሞርኳል/2/
የችግሬ ደራሽ የጭንቀቴ ነይ እናቴ/2/
እናቴ በአንቺ ሰው ሆኛለሁ
ከሞት አፋፍ ላይ ተርፌአለሁ
ስምሽን ስጠራ ቀን ሌሊት
ትሆኝኛለሽ መድሃኒት
አለኝ የምልሽ ፍጹም ሀብቴ
ከሊባኖስ ነይ መድሃኒቴ
የአደራ ልጅ ነኝ የአንቺ ልጅ
ተሰጥቼሻለሁ በአዋጅ
ክብርሽ ልዩ ነው እማቤቴ
ተነግሮ አያልቅም በአንደበቴ
በክርስቶስ ቀኝ ትቆሚያለሽ
ፍጥረትን ሁሉ ታስምሪያለሽ
ኑሮ ሲሚረኝ ሳመ ታ
ወደ አንቺ መጣሁ ጠዋት ማታ
ከስዕልሽ ፊት አልቅሻለሁ
ሜሉን በፍጥነት አግኝቻለሁ

## 381.ደጅ ጠናሁ

ደጅ ጠናሁ ቆይቼ ኪዳነ ምህረትን
ተጽናናሁኝ ረሳሁ ሀዘኔን
የአምላክ እናት እማቤታችን
ሞገስ ሁኚኝ ቀሪው ዘመኔን
የመከራው ዘመን አለፈ እንደዋዛ
አንቺን ተጠግቼ የአለሜን ቤዛ
የልጅሽ ቸርነት ያንቺም ደግነት
ባሪያሽን ፈወሰኝ ካስጨፈቀው ሞት
እናቴ ስምሽን ስጠራ አለፈ ያ ሁሉ መከራ
እንባዬ በፊትሽ ፈሰሰ እምዬ በአንቺ እየታበሰ
ሰላም ለኪ
ልቤ በአንቺ ፀና ከፍ ከፍም አለ
በጠላቶቼ ላይ አፌ ተናገረ
በማዳንሽ ስራ ባሪያሽ ደስ ብሎኛል
የሃያላኑን ቀስት ልጅሽ ሽብሮልኛል
እናቴ----------
እጄ ባዶ ሲሆን ወዳጆቼም ሸሹኝ
በሚገም ምክራቸው ሊለያዩኝ ሲሹ
እርሱ የሰጠኝን እርሱ ወሰደ አልኳቸው
እማቤቴ አለችኝ ብዬ አሳፈርኳቸው
እናቴ-----
ከአወደ ምህረቱ ሆኜ ስጠራት
ዘንበል ብላ አየችኝ ኪዳነ ምህረት
ሃሳብሽን ምንም የለም የሚሻለው
እረፍት ያገኘሁት እናቴ በአንቺ ነው
እናቴ-------

## 382. ማርያም እንወድሻለን

ሚርያም እንወድሻለን /2/
ስለወለድሽ የሕይወት ምግብን
ሚርያም እንወድሻለን
ደክመቴን አትዩ >> በሃጢያት መወደቄን
>>
ተስፋዬ አንቺ ነሽ >> እስከ ዕለተ ሞቴ >>
ላልከዳሽ ምያለሁ >> ከስርሽ ላልጠፋ >>
ገጸ በረከቴ >> የህይወቴ አለኝታ >>
የምህጫን ወለት>> ዘወድ አክሊላቸው
>>
ድንግል አንቺ እኮ ነሽ >> የማገድ
ስንቃቸው
ምክር ነኝ ለአንቺ >> እንደ
ነብያቱ >>
ስጦታ ማሆንሽን >> ለአዳም ልጆች
ሁሉ >>
ሞገስና ጸጋ >> በጌታ ፊት ያለሽ >>
ከሰይጣን ማሻሻ >> ዋስ ጠበቃችን ነሽ >>
እንደት ነበር ያኔ >> ጌታን ስትወልጂው >>
የእረኞቹ ደስታ >> የመላዕክት ዝማሬ>>

## 383. ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ይእቲ/2/ ክብረ ቅዱሳን
መዳየ መና ግሩም መዳየ መና ግሩም መዳየ መና
የቅዱሳኑ ክብር ነሽና እንሰጥሻለን ቅኔ
ምስጋና
የወለድሽልን የህይወት መና ዝናብ ያለብሽ
ታናሽ ደመና
ትህትና ልብስሽ ፍቅር ወለትሽ
ዕንስ ያዘልላል ሠላምታ ድምፅሽ
እሳቱን ወልደሽ እሳት ታቅፈሻል
ሳንዘምርልሽ መቼ ይመሻል
የፀሀይ መውጫ ምስራቅ ሆነሽ
ታላቁን ብርሃን አየንብሽ
አትጨልምም ህይወታችን
ልጅሽ ስላላ ፀሃያችን
ሠአሊ ለነ ሠላም ለኪ
ተመህፀኒ በኪዳንኪ
ንኢ ርግብየ ምስለ ወልደኪ
ሠማይ ወምድር ይዌደሱኪ
ክብረ ቅዱሳን ይዕቲ/2/ ክብረ ቅዱሳን
መዳየ መና ግሩም መዳየ መና ግሩም
ግሩም መዳየ መና/3/

## 384. የጽድቅ በር ነሽ

የጽድቅ በር ነሽ የመኤ ጽላት
አክሊለ ሰሜታት ምዕራገ ጸሎት
የጌታዬ እናት ንጹህ አክሊላችን
ሃሜልማል ሲና እማቤታችን/2/
እማቤታችን ለእኛ ምርኩዝ ነሽ >> ከለላም
ሆንሽ

>> የእሳት ሜዳይ >> እሳት ታቀፍሽ
>> በብርሃን ተከበሽ >> ወርቅ ለብሰሽ
>> ከሴቶች ሁሉ >> አብ ሚጠሽ
>> ድንግል ሆይ ልጆችሽ >> ዘወትር ይጠሩሻል
>> ስምሽን ለልጅ ልጅ >> ያሳስቡልሻል
>> በተሰጠሽ ጸጋ >> በአማላጅነትሽ
>> ምህረትን አሰጪ >> ከማሪው ልጅሽ
>> ያልታረሰች እርሻ >> ዘር የለተዘራባት
>> የህይወትን ፍሬ >> ሰጠችን የእኛ እናት
>> የታረደው ማሲህ >> እናቱን ወደዳት
>> በቀኑ ቆማለች >> ድንግል እማቤት ናት
>> የእውነት ደመና >> ዝናብ የታየባት
>> ወዳናለች ድንግል >> የታተመች ገነት
>> ክብርት ለሆነችው >> ኑ እንዘምርላት
>> ደስ ይበልሽ እንበል >> ለብርሃን እናት

## 385. ኪዳነምህረት እናቴ

**ኪዳነምህረት እናቴ**
ፈጥነሽ ደራሽ ነሽ በሀዘኔ
የከበበኝ ችንቀት ተወግዷል
ፍቅርሽ እመአምላክ እኔን ማርኳል
የችግሬ ደራሽ የጭንቀቴ
ነይ እናቴ ነይ እናቴ

እናቴ በአንቺ ሰው ሆኛለሁ
ከሞት አፋፍ ላይ ተርፌአለሁ
ስምሽን ስጠራ ቀን ለሊት
ትሆኚኛለሽ መድኃኒት
ኪዳነምህረት------
የችግሬ ደራሽየጭንቀቴ----

አለኝ የምለሽ ፍጹም ሀብቴ
ከሊባኖስ ነይ መድኃኒቴ
ያደራ ልጅ ነኝ የአንቺ ልጅ
ተሰጥቼሻለሁ በአዋጅ

ክብርሽ ልዩ ነው እመቤቴ
ተነግሮ አያልቅም በአንደበቴ
በክርስቶስ ቀኝ ትቆሚያለሽ
ፍትረትን ሁሉ ታስምሪያለሽ

ኑሮ ሲመረኘር ሳመነታ
ወደአንቺ መጣሁ ጠዋት ማታ
ከስዕልሽ ፊት አልቅሻለሁ
መልሱን በፍጥነት አግኝቻለሁ

## 386. አንቺን የያዘ ሰው

አንቺን የያዘ ሰው ምን ይጎድልበታል
በምልጃሽ በ ረከት ቤቱ ሞልቶለታል
ዘር መከር ባይኖው ጎተራው ባይሞላ
ሁሉምይሸፈናል በረድኤትሽ ጥላ

በረከትሽ ብዙ የደናግል ገንዘብ
የምስኪናን እናት የርሁባ ቀለብ
ለሁሉ መጋቢ ጸ ጋሽ የማይጎድል
ስምሽ ጥዑም ምግብ ከረሀብ የሚያስጥል/2/

አንቺ ብትመጪ ከምስኪኗ ቤቴ
እንደ መጥምቁ እናት በዛልኝ ሐሴቴ
የአዲ ኪዳን ቁርባ መንበር ጠረጴዛ
ጽድቅን አሸተትን የሕይወትሽን መዓዛ/2/

ልቤ ተጠራጥሮ ኪዳንሽን ካልከዳ
ልመናም አልወርድም አልይዝም አቁማዳ
ሁሉን እየሞላሽ መመገብ ታውቂያለሽ
ቢዝቁት የማያልቅ ጸጋና ሀብት አለሽ/2/

የእግዚአብሔር ማረፊያ ኮረባዊት ዋሻ
የህይወት ውሃ ምንጭ የህግ መፍሰሻ
ነበልባል ተዋህዶሽ ሙሴ አንቺን አይቷል
ጫማውን አውልቆ በፊትሽ ተደፍቷል/2/

## 387. ተወልዳለችና

ተወልዳለችና የጌታ እናት የእኛ መድሃኒት/2/
እናመስግናት እናወድሳት እንወደዳት/2/
የአምላክን እናት

## 388. ኢያቄም ወሃና

ኢያቄም ወሃና እናት አባትሽ
ቤተ መቅደስ ወስደው ስዕለት የሰጡሽ
መና ከደመና የወረደልሽ
ዕፀ ብ ድንቅ ፅዮን ማርያም አንቺ ነሽ
ኦ/2/ እመ ክርስቶስ ማርያም አንቺ ነሽ

## 389. ዮም ፍስሀ ኮነ

ዮም **<u>ፍስሀ ኮነ /</u>**2/ በእንተ ልደታ ለማርያም
በባርነት ሳለን ›› ሀጢአት በዓለም ነግሳ
››
በድንግል መወለድ ›› ቀረልን አበሳ ››

እግዚአብሔር ሚጠሽ >> ልትሆኚ እናቱ >>
ይኸው ተፈፀመ >> የዳዊት ትንቢቱ >>
የሐዋን ተስፋዋ >> የአዳም ህይወት >>
የኢያቄም የሀና >> ፍሬ በረከት >>
ምክንያተ ደህነት >> ኪዳነ ምህረት >>
ድንግል ተወለደች >> የአምላክ እናት >>
በሐዋን ምክንያት >> ያጣነውን ሰላም >>
ዛሬ አገኘነው >> በድንግል ሚርያም >>
የምስራች እንበል >> ሀዘናችን ይጥፋ >>
ተወልዳለችና >> የአለም ሁሉ ተስፋ >>

## 390. <u>*አክሊለ ፅጌ*</u>

አክሊለ ፅጌ ሚርያም
ቀጸላ መንግስቱ ለጊዮርጊስ
ክበበ ጌራ ወርቅ/2/ አክሊለ ፅጌ
**<u>ትርጉም፡ –</u> ሚርያም በጊዮርጊስ ንግስ/ክብሩ/**
**ጊዜ አክሊል ናት የአበባ ዘወድ እርሷ ክብነት**
**ያለው የወርቅ ዘወድ ናት**

## 391.<u>*ረሀበ ወፅምአ*</u>

ረሀበ ወፅምአ አዘክሪ ድንግል ረሀበ ወፅምአ
ምዳቤ አዘነ አዘክሪ ድንግል

## 392. <u>*ንዒ ንዒ ማርያም ንዒ ንዒ*</u>

ንዒ ንዒ ማርያም ንዒ
ድንግል ሆይ ንዒ ንዒ
ያን የአሳት ባህር ከቶ እንዳላይ

በሐመረ ኖህ የተመሰልሽ
በአሮን በትር የተመሰልሽ
የምሥራቋ በር/2/ ቶሎ ድረሽ

በተራራማው በኤፍሬም ሀገር
እንግዳ የሆንሽ ለኤልሳቤጥ በክብር
ነይልኝ ወደ እኔ/2/ ከአንቺ ጋር ልኑር

ዓለም ከብዶብኝ ተጨንቄአለሁ
ሐዘን በዝቶብኝ ብቸኛ ሆኜአለሁ
እረ ነይ ድንግል ሆይ/2/ እጠራሻለሁ

ጥበቡ አንቺ ነሽ ለሰሎንዲስ
ነይ ብሎ የሚጠራሽ ሶላናጢስ
አትጥፊ ድንል ሆይ/2/በእጅስ ልዳሰስ

ምሥጢር የገለጽሽ ለሕርያቆስ

ፈጥነሽ ያማለድሽ በቤተ ዶኪማስ
ነይልኝ እናቴ/2/ ልቤ ይፈወስ

ድንግል ቀርባለች ጩኸቴን ሰምታ
የኃጢአቴ ገመድ እስሩ ተፈታ
አከብራታለሁ/2/ ልጇ በእልልታ

## 393. <u>*ነይ ነይ ማርያም*</u>

ነይ ነይ ሚርያም ወላዲተ አምላክ የፃድቃን እማቤት
የመላዕክት እህት/2/
ሁላችሁ እሜት ከልብ አማእጅ ናትና በእውነት
እናማስግናት እናወድሳት እንወደዳት አማእጅ
ኪዳነ ምህረት/2/

## 394. <u>*ከመጽጌ ሮማን*</u>

ከመጽጌ ሮማን ከመጽጌ/2/
አበባዬ/2/ ወላዲተ አምላክ ሲሳይ
**ትርጉም፡ –** እንደ ሮማን አበባ ያሚኒች
የአምላክ እናት ሚርያም ሲሳይ ናት

## 395. <u>*ንግስተ ሰማያት*</u>

ንግስተ ሰማያት ወምድር ማርያም ድንግል
ተፈጸመ/5/ ማኅሌተ ጽጌ

ገሊላ እትዊ

ገሊላ እትዊ/2/
ሀገርኪ ገሊላ ዕትዊ/2/
ገሊላ ግቢ/2/
ወደ ሀገርሽ ገሊላ ግቢ/2/

## 396. <u>*እንዘ ተሃቅፍዮ*</u>

እንዘ ተሃቅፍዮ ለህጻንኪ <u>ድንግል</u>/2/
ንኢ ንኢ ሚርያም/2/

## 397. <u>*ገሊላ እትዊ*</u>

**እማቤቴ እስከ መቼ ባዕድ አገር ትኖሪያለሽ**
**ገሊላ ግቢ/4/ አገርሽ ገሊላ ግቢ/2/**
**ገሊላ እትዊ/4/ አገረኪ ገሊላ እትዊ/4/**

**እማቤቴ ሚርያም ገሊላ እትዊ ስደቱ ይበቃሻል >>**
**ንጉሥ ሞቷል ብሎ >>ገብርኤል ነግሮሻል**
**የእሳት ሠረገላ>> ኡራኤል ይመራሻል**

**የዝናቡ ጌታ>> እናቱ ሆነሽ ሳለ**

**ሰይጣን በሰው አድሮ >> እያስከለከለ**
**ወሀ ጥም ፀንቶብሽ >>አፍሽ ደርቆ ዋለ**
**ይበቃል እናቴ >> ርሃብ ጥማትሽ**
**ሂጂ ወደ ገሊላ >>ወደ ዘመዶችሽ**

**የሰሜታት አክሊል >> የጻድቃን እናት**
**ባርከሽ ሰጠሻቸው >> ማካራን ስደትን**
**እኛም ይታደለን >> የአንቺው በረከት**

**ገጽሽ ብሩህ ሜላካም >> ልክ እንደ ጸሀይ**
**እግዝዕትነ ማርያም >> እሙ ለአዶናይ**
**አይገባም ለአንቺ >> ማካራ ስቃይ**

## 398. አዘክሪ ድንግል

አዘክሪ ድንግል አዘክሪ
ለልጅሽ አሳስቢ >>
ለኃጥአን አኮ ለጻድቃን
ከአንቺ መወለዱን >> በቤተልሔም >>
በጨቅ ማጠቅለሉን >> መኝታው ግርግም
በዚያ በብርድ ወራት >> የገበሩለትን
የአድግና የላም >> እስትንፋሳቸውን
>>
በግብጽ በረሃ >> ማሳደድሽን
የአሽዋወን ግለት >> ረሀብ ጥሙን
በመቃብሩ ዘንድ >> ባነባሽው ዕንባ
አሳስቢ ድንግል ሆይ >> ገነት
እንድንገባ

## 399. ወደ ምስራቅ እዩ

ወደ ምስራቅ እዩ ወደ ምስራቅ መውጫ
ድንግልን ክበቧት እንበል ሃሌ ሉያ
ለአምላክ እናት ለአዛኝት እልል በሉ እንዘምርላት/2/
ወገኖች ተነሱ እናታችን መጣች
ስሟን ስጠራ መቼ ትቀራለች
የተከዘ ልታጽናና ነይ ስላት ትመጣለችና
የፅጌው ማህሌት በጸሎት ሲጀምር
ማርያም ትመጣለች በደመና በአየር
ንኢ ስንል በሰዓታት
ልትባርከን ትመጣለች በእውነት
ፍልሰታ ሲጀምር ቃል ኪዳን ገብታለች
የሌሊት ወዳሴን ንኢን ትሰማለች
ከሰአታቱ በበረከት
ልትጎበኝ ትመጣለች በእውነት
በፍፁም ቸርነት እንዲምረን ጌታ
በአማላጅነትሽ ሁኚልን መከታ
እናታችን አለኝታችን
እንድናለን ድንግል አንቺን ይዘን

## 400. ድንግል መከራሽን

**ድንግል ማካራሽን ጥቂት ባስታወሰው**
በሄሮድስ ዘመን ፍጥረት ያለቀሰው
አንቺ የአምላክ እናት ደግሞም እመቤት
እንደ ችግረኛ ተነሳሽ ስደት
እረ ለማሆኑ እንዴት አለቀልሽ
ስትንከራተቺ በረሃወን አቋርተሽ
ይገድሉታል ብለሽ ለልጅሽ አስበሽ
በሄሮድስ ዘመን ማካራሽን አየሽ
ማካራሽን ማካራሽን አየሽ
አዛኝቷ ማርያም በጠራሁሽ ጊዜ
እንድትደርሽልኝ በማካራ ጊዜ

ማካራን ያየ ሰው መቼም አይጨክንም
አትጨክኚብኝ እማቤቴ ማርያም
እማቤቴ እማቤቴ ማርያም
አቤት የዚያን ጊዜ ያየሽው ማካራ
ያለቀሽው ለቅሶ መቼም አይወራ
የማካረኛ እናት እናት አንቺ ማካረኛ
ዕድሜሽን ጨረስሽው ሆነሽ ሀዘንተኛ
ሀዘንተኛ ሆነሽ ሀዘንተኛ

# የቅዱሳን መላዕክት መዝሙር

## 401. መአዛ ሰናየ

ማኣዛ ሰናየ/2/ /2/
እኽ ሚኪኤል ማኣዛ ሰናይ/2/

## 402. ዝኬ ውእቱ

ዝኬ ወእቱ ሚኪኤል ህብስተ መና
ዘአወረደከ/2/
ወከመ አያያት ማኣር/2/ ጥኡም ፍድፊድ ሊቀ
መላዕክት

## 403. ሚካኤል ሥዩም

ሚኪኤል ሥዩም/2/ ሊቀ መላዕክት
ማዝገበ ርህራሄ/3/ የዋህ

## 404. ልዑል ውዕቱ

ልዑል ወዕቱ ልዑለ ማንበር
ሚኪኤል/ 2 ልዑለ ማንበር

## 405. ሰራዊተ መላዕክቲሁ

ሰራዊተ ማላዕክቲሁ
ለመድሃኔዓለም ይቀወሙ

የመድሃኔዓለም አገልጋዮቹ
ይቆማሉ ከፊቱ/2/ አገልጋዮቹ

## 406. የሰሙ ትርጓሜ

የሥሙ ትርጓሜ ማን እንደ እግዚአብሔር ነው
የሰውን ወደ አምላክ የአምላክን ወደ ሰው
እኛን የሚረዳን ዘወትር በምልጃው
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚኪኤል ነው
ከጉድጓድ ተጥሎ ፍፁም ከሚያስፈራው
ከተራቡ አናብስት ዳንኤልን ያዳንከው
እኛንም ተራዳን ቸል አትበለን
ሰይጣን በተንኮሉ ወጥመድ ሳይጥለን
የክፉ ሰው ሥራው ክፉ ሃሳብ ነውና

በቅንነት ማገድ ከቶ አይሄደም እና
የሞቱን ደብዳቤ ለባህራን ሰሰጠው
ሚከኤል አጥፍቶ በደስታ ለወጠው
ገና ብላቴና ሳለሁ አንድ ፍሬ
ሰው ሁሉ ሲንቀኝ ምክጋናን ጀምሬ
ጸጋዬን አብዝቶ ላበቃኝ ለዚህ ክብር
የሚከኤል አምላክ ይመስገን እግዚአብሔር

## 407. ኃያል ኃያል

ኃያል ኃያል /2/
ሰዳዱ ሳጥናኤል/2/ ኃያል ገባሬ ኃይል
ባህራንን ያዳነው ተላፊኖስን የረዳው
መልአኩ ሚከኤል ነው/2/ የሞቱን ደብዳቤ የለወጠው
ከእደ ረበናት/2/ሶስናን የዳናት/2/
ሚከኤል መልአከ ምህረት
ዲያብሎስን የዋረደከው በእሳት ሠይፍ የቀጣኸው
ሚዛንህ ትክክል ነው/2/
ሚከኤል ክብርህ ድንቅ ነው
በሀዘን በትካዜ ያለሁትን ብላቴና/2/
አፅናናኝ አረጋጋኝ/2/ ሚከኤል ሊቀ ደብረ ሲና

## 408. ውዕቱ ሊቆሙ

ወፅቱ ሊቆሙ ለመላዕክት ወሚአኮሙ ስሙ ሚከኤል
ልብሱ ዘመብረቅ አይኑ ዘርግብ ሊቀ መላዕክት

## 409. አ ሚካኤል

አ ሚከኤል/2/ ሊቀ መላዕክት
በኃጢያት እንዳንወድቅ እንዳንሞት
ፈጥነህ ተራዳን አፅናን በእምነት
ለያዕቆብ ወገን ሚከኤል ለእስራኤል //
ጠባቂያቸው ነህ // መልአከ ኃይል //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚከኤል የእኛ አባት/2/
ነጸብራቃዊ // ተከህኖ ልብስ //
ሀሜልማል ወርቅ // ዓይኑ ዘርግብ //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚከኤል የእኛ አባት/2/
በስዕልህ ፊት // እሰግዳለሁ //
ቀርበህ አነጋግረኝ // አለሁ በለኝ //
ፍቅርን አድለን ምህረትን ቅዱስ ሚከኤል የእኛ አባት/2/

## 410. አምላከ እስራኤል

አምላከ እስራኤል ታማኝ ጌታችን
ለእስራኤል ለሚሔ የሆንከው መድህን
ፈርኦን ተነስቶ በትዕቢት ቢገን
ለእስራኤል አርበኛ ሚጥከው ሚኤን
አማላጅ ነው ሚከኤል/2/የአምላክ ባለሟል
የእነ ሚኤ የህዝበ እስራኤል
ፈርኦን እንደገና ልቡ ተፀፅቶ
በከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ነበር ሚከኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
ፈርኦን እንደገና ልቡ ተፀፅቶ
በከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
እስራኤል ተጨንቀው ሜጃቸው ጠፍቶ
አፅናናቸው ሚኤ የአምላኩን ስም ጠርቶ
ሚኤ እንደታዘዘው አነሳ በትሩን
እጆቹን ዘረጋ ገሰጸው ባህሩን
እንደ ግንብ አቆማት ባህረ ኤርትራን
በደረቅ አለፉ እስራኤላውያን

## 411. አማላጅ ነው

በፍጡሩንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰወን ለማገልገል
ተራዳዩ መልአክ ጠባቂ የእስራኤል
የመላዕክት አለቃ ስሙ ነው ሚከኤል
አማላጅ ነው ሚከኤል/2/
የአምላክ ባለ ሟል
ለእነ ሚኤ ለህዝበ እስራኤል
ፈርኦን በእስራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
በከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ነበር ሚከኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና
ከባህር ያወጣሽው ጸጋዘአብን
ከአረሜው ንጉስ እግዚአርአን
ከልልህ የጠበክ ብብዙ ተአምራት
እኛንም ጠብቀን ከበደል ከኃጢያት
በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላዕክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁላን እረዳት
መልአኩ ሚከኤል አማላጃችን
እንለምንህለን እንድትብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ጻድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚከኤል አደራ

## 412. ቅዱስ ሚካኤል

ቅዱስ ሚከኤል/3/ ነፍሴ ሲጨነቅ ሲዝል ሥጋዬ
ፈጥነህ ተራዳኝ ዋስ ጠበቃዬ
አንተ ስለሆንክ ሚከኤል የአምላክ ባለ ሟል
ልመናህ ፈጥኖ ሚከኤል ከአምላክ ያቀርባል
የዋህ መልአክ ነህ አዛኝ ለሰው
ምልጃህ ፈጣን ነው ለምናምነው/2/
ደዌ የፀናበት ሚከኤል በአንተ ይድናል
በአደባባይህ ሚከኤል ምስክር ሆኗል
ከቤቱ መጥቶ የተማፀነ
በቃል ኪዳንህ ሕይወቱ ዳነ/2/

## 417.ተወከፍ ጸሎትነ

ተወከፍ ጸሎትነ ወስተ ኖኃ ሰሚይ/2/
ከመ ማኢዛ ሡናይ/4/ ሊቀ መላዕክት

## 418. ሰፊሆ ክነፊሆ

ሰፊሆ ክነፊሆ/2/
ክነፊሁ ይጸልል ዲቤነ ;2/
ትርጉም፡ - ክንፉን ዘርግቶ እኛን ይጋርደን
ይጠበቀን

## 419. በእደ መልአኩ

በእደ ሚልአኩ ይቀበነ /2/
ሠላመ እግዚአቡ እግዚአብሔር የሀበነ

## 420. ይበራል በክንፉ

ይበራል በክንፉ ሚልጃወም ፈጣን ነው
የአምላክ ስም አለበት ስሙ ሚካኤል ነው
ያሳደገኝ ሚልአክ ዛሬም ከእኔ ጋር ነው/2/
ከፊቴ ቀደመ ደሜን ዘርግቶ
እንዳልደናቀፍ ጉድባዎቼን ሞልቶ
ዛሬ ላለሁበት ብርቱ ጉልበት ሆነኝ
ሠው ለመባል በቃሁ ሚካኤል ደገፈኝ
በእናቴ እቅፍ ገብቼ መቅደሱ
ይኸው እስከዛሬ አጥሮኝ በመንፈሱ
የህይወቴን ሰልፎች አለፍኩ ከእርሱ ጋራ
ተፅፏል በልቤ የሚካኤል ስራ
በዙሪያዬ ተክሎ የእሳት ምሶሶን
ፅድቅ እየመገበ አሳደገኝ ልጁን
የአምላኬን ምስጋና ዘወትር እያስጠናኝ
እርሱ ነው ሚካኤል በማዘመር የሞላኝ
ፊት ለፊት ተተክሎ ከታናሿ መንደር
ይሠማኝ ነበረ ቅኔው ሲደረደር
ይወስደኛል ደጁ እየቀሰቀሰ
ታላቁን በረከት በወስጤ አፈሰሰ
ሲከፋን እንዳላይ ክንፎቹን ጋረደ
ሜራኝ ወደ ህይወት መዳኔን ወደደ
የሞአብን ቋንቋ ከአፌ ላይ አጥፍቶ
በጸጋው ቃል ቃኘኝ በበረከት ሞልቶ

## 421. ምስራች ነጋሪ

ምስራች ነጋሪ ገብርኤል ገናና
ይዞ መጣ ቤቴ የበረከት ዜና
የምቅናናበትን ሰላም አበሰረኝ
ያስጨነቀኝ ጠፉ ሸክሜ ቀለለኝ
ብርሃናዊው ሚልአክ ገብርኤል
ዙሪያዬ ሰፈረ ››
ወረደ ከራማ ››
ቅጥሬ ተከበረ ››
የሞቴን ማዛገብት ቤልሆር ሲከምር
አሳደደው ገብርኤል አጠፉው ከምድር
አትፍሪ እያለ ››
አፅናናኝ ደጋግሞ ››
እግሮቼን አጸና ››
ማቀሉን አሳልሞ ››
ጋረደኝ በክንፉ እስኪያልፍ ማከሩ
ታደገልኝ ነፍሴን ልዘምር ለክብሩ
ሌጊዮን አይችልም ››
ሊገባ ከቤቴ ››
የእሳት ቅጥር ነው ››
ገብርኤል አባቴ ››
ይንከባከበኛል ፍሬ እስከሜፈራ
በሚልጃው አለፍኩኝ ታላቁን ሚከራ
እግሮቼን ያቀናል ››
ህይወት ወዳለበት ››
አምላኬን ወዳሴ ››
ወደምከሚከት ››
ቤቴን በበረከት ያትረፈርፈዋል
ሚሉ ነው ማሶቤ ከፅዋዩም ተርፏል

## 422. ሀያል ነህ አንተ ሃያል

ሃያል ነህ አንተ ሃያል ደጉ ሚልአክ ገብርኤል
ይወደቅ ይሸነፍ ጠላት አንተ ተራዳን
በእወነት/2/
በዱራ ሜዳ ላይ **ገብርኤል** ጣኦት ተዘጋጅቶ
**ገብርኤል**
ሊያሚልከት ወደዱ **ገብርኤል** አዲስ አዋጅ ወጥቶ
**ገብርኤል**
ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ፀኑ
ጣኦቱን ረግጠው በእግዚአብሔር አመኑ
ተቆጣ ንጉሱ **ገብርኤል** በ3ቱ ህፃናት
**ገብርኤል**
ጨምሯቸው አለ **ገብርኤል** ወደ እቶን
እሳት **ገብርኤል**
ከሰሚይ ተልኮ ደረሰ ሚልአኩ
ከሞት አዳናቸው በእሳት ሳይነኩ
ከእቶኑ ስር ሆነው **ገብርኤል** ዝሚሬ ተሞሉ
**ገብርኤል**
ገፍተው የጣሏቸው **ገብርኤል** በእሳቱ ሰበሉ
**ገብርኤል**
አልተቃጠለችም የራሳቸው ፀጉር
አዩ ሙኳንንቱ የእግዚአብሔርን ክብር
ናቡከደነፆር **ገብርኤል** እጁን በአፉ ጫነ
**ገብርኤል**
ሰለስቱ ደቂቅን **ገብርኤል** ከእሳት ስላዳነ
**ገብርኤል**
ይክበር ጌታ አለ የላከ ሚልአኩን
ሊያሚልከው ወደደ ስላየ ማዳኑን

## 423. ገብርኤል መልአክ

ገብርኤል ሚልአክ ተጨንቃለች ነፍሴ
በል ሚልደህ አስታረቀኝ ከቅድመ ስላሴ/2/

ከእሳት የሚያወጣ ገብርኤል ሜልአክ እምነት
ባይኖረኝ >>
የጌታ ባሪያ ነኝ >> ፈጥነህ አድነኝ
>>
ፈታኜ ብዙ ነው >> የነፍሴ ጠላት
>>
ክንፍህ ይሸፍነን >> በቀን በሌሊት
>>
ማን አፍሮ ይሄዳል >> አምኖ
በስላሴ >>
አምላኬ እግዚአብሄር ነው >> ዋስ
ሁናት ለነፍሴ >>
በጥቂት በብዙ >> ማዳን ይቻልሃል
>>
የተፍለቀለቀ >> ውሃን አብርደሃል
>>
አያሎጣም ትምጣ >> ማዳንህን ታውራ >>
ቁርቆስም ይናገር >> ያንተን ድንቅ ስራ
>>
ነገስታት ተገርመው >> አፋቸውን ያዙ >>
ገብርኤል አንተ ነህ >> ተአምራተ ብዙ
>>

## 424. ገብርኤል

ገብርኤል/2/ስለው ሰምቶ
መጣ ወደ እኔ ፈጥኖ
ሰንሰለቴን በጠሰው የአንበሶቹን አፍ
ዘግቶ/2/
ገብርኤል ስጋዬ ሳይረግፍ በአናብስቱ ጥፍር
>> ታድጎኛል ምልጃው የሜልአኩ ክብር
>> በረሃብ ለነደዱ አናብስት ሲጥሉኝ
>> አንተ አለሽኝና ክንፎችህ ከለሉኝ
>> ከአፎቱ ሲመዘዝ የጠላቴ ሰይፍ
>> አፅንቶ ይዞኛል ፍሬዬ ሳይረግፍ
>> አደገድጋለሁ አለኝና ፍቅሩ
>> በእሳት ክንፍ ታጥሯል የደጁ ድንበሩ
> በሰይፍ ተመትሯል የከፉዎች ከህደት
>> ሀብሉ ተበጣጥሷል የአመፁ ሰንሰለት
>> ከቅዱሱ ድንጋይ ህይወት ከሚያፈልቀው
>> እንዳልለይ ረዳኝ ከብሬን ከፍ አረገው
>> አለው ልዩ ሥልጣን ከአምላክ የተሰጠው
>> ይመጣል ወደ እኛ እሳቱን ሊጠፉው
>> እኛም እናምናለን ሰምተናል አይተናል
>> የመላዕክት አለቃ ከአምላክ ያማልዳል

## 425. ቅዱስ ገብርኤል

ቅዱስ ገብርኤል ነው አብሳሪው ሜልአክ/2/
ትርጓሜውም ሰው እና አምላክ/2/
ቅድስት እናታችን በቤተ መቅደስ/2/
እንዲህ አላት ደስ ይበልሽ
ደስ/2/
ሰላምታ በማጠት እንዲህ በማለት/2/
አበሰራት የአምላክን ልደት/2/
ቁርቆስ እየሎጣ ከእሳት ሲጣሉ/2/
ወሃ ሆነ ጣፉ ነበልባሉ/2/
ሰልስቱ ደቂቅን ከእሳት ያዳነ/2/
ገብርኤል ዛሬም ያድነን/2/

## 426. ገብርኤል ሃያል

ገብርኤል ሀያል ሜልአክ ሰላም ሜልአክ ብስራት
የምታወጣ የእግዚአብሔርን ህዝብ ከሚድ እሳት
ፍቅርህ ተስሏል ከልባችን ፊትህ ቆሞናል
ባርከን ልንልህ
የፅናታቸው ዝናው ሲሰማ
ከዛች ባቢሎን ከሞት ከተማ
ህፃናት ሳሉ በራ እምነታቸው
ቆመህ ተገኘህ ማካላቸው
ውሃው ሲዘልም ቢያስደነግጥም
በጋኖቹ ወስጥ ቢነዋወጥም
ጸንተው ዘመሩ ልጅና እናቱ
አንተ ስትደርስ ከዚያ ከሳቱ
ቁርቆስም ፀና ሞትን ሳይፈራ
አንተ ስላለህ ከእነርሱ ጋራ
አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ
አምነው ድል ነሱ ያንን መከራ
እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ
ቆመኸ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ
ከፉውን ዘመን የሚልፍበት
ፅናትን ስጠኝ ድል ልንሳበት

## 427. የራማው ልዑል

የራማው ልዑል ገብርኤል/2/
ተመላለስ መሃላችን ስምህን ጠርተን ና ስንል
የምስራች ነጋሪ ድንቅ ልደት አብሳሪ
የፅድቅ የፋና የህይወት ጎዳና/2/
የአናንያ የአዛርያ ሚሳኤል ተስፋቸው
ከእሳት ነበልባል ያዳንካቸው/2/
ተስፋችን ነህ መጠጊያችን ነህ
ቅዱስ ገብርኤል አባታችን ነህ/2/
ላመኑብህ ለተማጸኑብህ
ፈጥኖ ደራሽ አለኝታችን ነህ/2/
እሳት ለብሰህ ብርሃናዊ ሜልአክ
አንተ አማልደን ከመሃሪው አምላክ/2/

## 428. የመላዕክት አለቃ

የመላዕክት አለቃ ገብርኤልን ላከው
ሀያሉ እግዚአብሔር በሠሞኘት ያለው
የባህሪ ልጁ ወደ አንቺ ይመጣል
ብለህ ለጽዮን ልጅ ንገራት ለድንግል
ሀይለ ልዑል ወልደም ሥጋሽን ይለብሳል
በተለየ አካሉ ወደ አንቺ የመጣል
ከስጋሽም ስጋ ከነፍስሽም ነፍስ ነስቶ
ይዋሃዳል
በገጸ ህጻናት ከአንቺ ይወለዳል
ደንቆሮ ሊሠማ ድዶች ሊናገሩ
በጌታ ተአምራት ዕወራን ሊበሩ
ሙታን ይነሱ ዘንድ በሚህጻንሽ ፍሬ
ከእግዚአብሔር ወደ አንቺ ተልኪአለሁ ዛሬ
ደስ አሠኛት አለው ልዩ ሠላምታ

ሀሴት እንዳታደርግ ምስራቹን ሰምታ
ድዳ እንዳደረከው ካህን ዘካርያስ
እንዳታሳዝናት ከእርሷ ጋር ስትደርስ
ገብርኤል በደስታ ምስራቹን ይዞ
ከሠማይ ወረደ በአምላኩ ታዞ
በሊባኖስ ማንደር እስኪሰማ ድረስ
ክንፉን እያማታ መጣ ሲገሰግስ
ደስ ይበልሽ አላት እየተሳለማት
ሀርን ከወርቅ ጋር ስትፈትል አግኝቷት
እውነተኛው ንጉስ ከአንቺ ይወለዳል
ለአንቺ ፍቅርና አንድነት ይገባል

## 429. ገብርኤል ነው

ገብርኤል ነው አምላክ የሾመው/2/
አናንያን አዛርያን ሚካኤልን ከእሳት ያዳነው
ናቡከደነጠፎ አንተን በግለፅ አይቶ
ለእግዚአብሔር ሰገደ ያንተን ምስል ትቶ
ሀሰቴን እንደሆን ይመስክሩ ሶስቱ
ከዛች ከባቢሎን/2/ የወጡ ከእሳቱ
ለአለመ ማላዕክት ከቅዱሱ ቦታ
የሰወን ልጅ ሚጥክ ልትረዳ ጠዋት
ማታ
እንደ ጌቤናይቷ ቅድስት ኢየሉጣ
ትመስክር ስለአንተ/2/ ከነልጇ ትምጣ
ልመስክር ስለአንተ ነህና ህይወቴ
ገብርኤል/2/ ሠሚ ስዕለቴ
የአናብስትን አፍ የዘጋኸው መልአክ
ገብርኤል አንተ ነህ/2/ በእኛ ሁሉ የታመነክ

## 430. ይቤላ ህፃን

ይቤላ ህፃን ለእሙኢትፍርሂም እም/2/
ነበልባለ እሳት/2/
ለአናንያ ወአዛርያ ወሚካኤል ዘአድኃኖሙ
ወፅቱ ያድህነነ
**ትርጉም፡ –** ህፃኑ ቂርቆስ ለእናቱ እንዲህ
አላት
የእሳቱን ነበልባል አትፍሪ አናንያ አዛርያንና
ሚካኤልን ያዳነ አምላክ ያድናነል

## 431.ቅዱስ ገብርኤል ነው

ቅዱስ ገብርኤል ነው አብሳሪው መልአክ
ትርጓሜውም ሰው እና አምላክ/2/
ቂርቆስ ከእናቱ ጋር ከእሳት ሲጣሉ
ወሃ ሆነ ጠፉ ነበልባሉ

## 432. መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላዕክት ገብርኤል/2/
ሰአል ወፀሊ በእንቲአነ አይርግ ጸሎትነ
ቅድመ መንበሩ ለመድሃኔዓለም

## 433. ህጻን ወእሙ

ህጻን ወእሙ/3/
ኪሌሆሙ ፈጸሙ ገድሎሙ/2/

## 434. እልፍ አእላፋት

እልፍ አእላፋት ወትልፊት
ቅዱሳን ንጹሃን መላዕክት
ቆሙ ለአገልግሎት ጸንተው በአንድነት
ቅዱስ/3/ አምላክ በማለት
ኢዮር ራማ ኤረር የመላዕክት ሀገር
የሀይማኖት ፍቅር የምልክት ክር
እውነት የታየብሽ የመላዕክት ክብር
አፅናን ሲል ገብርኤል በአለንበት ቦታ
በሳጥናኤል ነገድ ነበረ ሁካታ
ግሚሹ እየካደ ቀሪው ሲያመነታ
የሳጥናኤል ምኞት እንደ አበባ ረግፎ
ሚካኤል ተሾመ በእምነት ተደግፎ
ሳጥናኤል ወደቀ ጸጋወን ተገፎ
ቅዱሳን መላዕክት በእምነት የጸናችሁ
በታላቅ አክብሮት ሰላም እንበላችሁ
ስግደት ዘበፀጋ እንስገድላችሁ

## 435. ይቤ ዕዝራ

ይቤ ዕዝራ ወመጠወኒ ኡራኤል ሊቀመላዕክት
ፅወአ ምሉአ ዘህብሩ ይመስል እሳተ
እኸ አንሠ ሠተይክዎ ወሶበ ሠተይክዎ
ጉስአ ልብየ ጥበበ ወምክረ

## 436. . ሊቀ መላዕክት

ሊቀ መላዕክት/2/ ኡራኤል ሊቀ መላዕክት
ፅወአ ልቦና ለእዝራ ሱቱኤል/2/
ኡራኤል/2/ ሊቀ መላዕክት

## 437. ኡራኤል ገባ

ኡራኤል ገባ ከጎጆዬ ጸሎቴን | ሰምቶ
ቤቴን ባረከው በምልጃው ብርሃንን ሰቶ 2
ኃይልን አደለኝ ብርታት ሆኖ
ጋሻ መከታ ለእኔ ሆኖ
ልጁን ሰምቶኛል ስሜጸነው
የጭንቅ ቀኔ አባቴ ነው
የዕውቀትን ፅዋን አጠጥቶኝ
ጥበብ ሞላኝ ልጁ እንድሆን
ጩኸቴን ሠምቶኝ ላልዘነጋኝ
ስለ ወለታው ለእርሱ ልቀኝ
ሀዘን ከላዬ እንዲጠፉ
ቅዱስ ኡራኤል ሁነኝ ተስፋ
ደስታ በቤቴ ሞላልኝ
በምልጃው ፈጥኖ ሲቀርበኝ
እልል እላለሁ በአንደበቴ
ደስታን ስላየሁ በረዳቴ
እኔን ሳይንቀኝ ላከበረኝ
እዘምራሁ ስለረዳኝ

## 438. ርዕዩ አበዮ ለቅዱስ ኡራኤል

ርዕዩ እበዮ ለቅዱስ ኡራኤል

እወራን ይሬዕዩ ወፅኡማን ይሰምዑ
እለለምፁ ይነፅኡ እለወው ሀቤሁ
ኑ እዩ የኡራኤልን ተአምራት እወሮች ያያሉ
ደንቆሮዎች ይሰሚኡ ለምፃሞችም ይነፃሉ ወደ
እርሱ ይመጣሉ፡፡

# የፃድቃን፣ የሰማዕታት፣ የቅዱሳን መዝሙራት

### 439. ጋሻውን ይዞ በፈረስ

ጋሻወን ይዞ በፈረስ አቤት ማሞዱ ቅዱስ
ጊዮርጊስ
ቤሩታዊትን አዳናት ዘንዶ እንዳይበላት
ደራጎን/2/
ጋሻወን ይዞ በወጣትነቱ >> ፅድቅን
ለይቶ አወቆ
ለዘመቻ ወጣ >> ጋሻ ጦሩን ታጥቆ
>> በህጻንነቱ >> በአምላኩ ተጠርቶ
>> ድል ነሣ ጠላቱን >> ጥበብን ተሞልቶ
>> ሀያሉ ጊዮርጊስ >> የፅድቅ
ወታደር
>> በተጋደለው ጻና >> በአምላኩ
ሳያፍር
>> አራት ሞትን ሞተ >> ለስጋው ሳይሳሳ
>> ለአምላኩ ክብር >> ተቀበለ አበሳ
>> የልዳው ንጉስ << ቅዱሱ አንበሳ

### 440. አ ፍጡነ ረድኤት

አ ፍጡነ ረድኤት/2/
የእግዚአብሔር አገልጋይ ቅዱስ ሰማዕት
ሠላም ለአንተ ይሁን ፍጡነ ረድኤት
የልዳው ጸሀይ >>
በጨካኝ ንጉስ ፊት ቆምክ አደባባይ
ታማኝ አገልጋይ ነህ >>
ሥቃይ ያልበገረህ >>
አክሊልን አገኘህ መከራን ታግሰህ
የፈጣሪወን ስም >>
ስለመሰከረ >>
ጊዮርጊስ ሰማዕት በሠይፍ ተመተረ
የስቃይ መሣሪያ >>
ያላዘናጋህ >>
መንፈሳዊ አርበኛ ጊዮርጊስ አንተ ነህ
ለእምነት ተጋዳይ >>
ታማኝ ወታደር 〃 >>
በነገር አያልቅም የተሰጠህ ክብር
ሥቃይ ቢያደርሱብህ >>
በመታገስህ >>
ሲወሳ ይኖራል ዘለዓለም ስምህ
ለሠማው ይደንቃል
የአንተ ሰማዕትነት
ምሳሌ ይሆናል ለሁሉ ፍጥረት
ገድሉ ይነገራል
ክብር እንደተሰጠህ
ጊዜ የማይሽረው ምግባር ሀይማኖት ነው

### 441. ጊዮርጊስ ሃያል

ጊዮርጊስ ሃይል/2/ ማስተጋድል
ገባሬ ተአምር/2/ ኮከበ ክብር

### 442. ለፍቅረ አምላኩ

ለፍቅረ አምላኩ ጊዮርጊስ/2/
ተጋደለ/2/ ወፈጸመ ገድለ

### 443. ፈጥነህ ቅረበን

ፈጥነህ ቅረበን ጊዮርጊስ/2/
ለአምላክህ የታመንክ እስከ ሞት
አክሊልን አገኘህ ፍጡነ ረድኤት
መከራን ታገሰ በወጣትነቱ
ስለጌታው ፍቅር ጊዮርጊስ ሰማዕቱ
የረገጥክባቸው የእግሮችህ ፋና
ይመሰክራሉ ጊዮርጊስ የአንተን ዝና
በመከራው ጸና ሩጫውን ፈፀመ
የህይወትን አክሊል ጊዮርጊስ ተሸለመ
ሥጋወን ለማገዝ ነፍሱን ለአምላክ ሰጥቶ
ተጋድሎ አሸነፈ በእምነቱ ፀንቶ
ስለጌታው ፍቅር ጊዮርጊስ ሞት አፈረ
እኔ ክርስተያን ነኝ ብሎ መሰከረ
ኢየሱስ ክርስቶስ አብዝቶለት ፀጋ
ለነፍሱ ተገዛ ሳይሳሳ ለስጋ
ሀያሉ ጊዮርጊስ የልዳው ጋናና
ከጠላት አድነን ፈጥነህ ድረስና
አወሬው በዙሪያችን ሊወጠን ሲያደባ
ስም ጋሻ ሆነን መከለያ አንባ

### 444.

### 445. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

ለሃገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተሃቅብ/2/
አባ አ አባ/2/ ገብረ መንፈስ ቅዱስ/2/አባ

### 446. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

**ገብረ መንፈስ ቅዱስ**
**የአምላክ በለመዋል ፃድቅ**
**ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ስራቸው**

### 447. አባ አቡነ

አባ አቡነ/2/ መምህር አባ
ተክለሃይማኖት "/2/
እምአእላፍ ህሩይ/2/ አባ/6/
አቡነ ተክለሃይማኖት

## 448. ነፍሴን አደራ

እይራየኒ አይነ ሙት
ወይርከበኒ ኩነኔ
ነፍሴን አደራ በሰማይ/2/ ተክልዬ ፀሃይ
ፅላሌ ዞረሪ ነይ ማስክሪ
የተክለሃይማኖትን ዝና አወሪ
የእንቁርቁሪት ጸበል ማር ውተት
ሁሉም ተፈወሱ ሲጠጡት/2/
ትህትናህ ግሩም ነው ቅድስናህ
ሀይቅ እስጢፋኖስ አገልግለህ
ደብረ ዳሞ ዘልቀህ ክንፍ አወጣህ
ደብረ ሊባኖስ ላይ አርፏል አፅምህ/2/
ፈተታና ዳሞት ተሻግረህ
ባርያንን ሁሉ አሳፈርክ
በንብ ቀፎ አርገው ቢጥሉህ
ሚካኤል በክንፉ አቀፈህ/2/
በደብረ አሰቦት ጦር ተክለህ
29 ዘመን ተጋድለህ
ወዝህ ያረፈበት ነጠበጣቡ
ድውይ ይፈወሳል ቃል ኪዳኑ/2/
ይህን ሁሉ ጸጋ ተችረሃል
ቁጥርህ ከማዕከት ተስተካክሏል
አባቴ/2/ እኔ ስልህ
ነፍሴን ታደግልኝ በምልጃህ/2/

## 449. ሐዋርያው መነኩሴ

ሐዋርያው መነኩሴ የሚጠፀ ሶላሴ/2/
ዋስ ጠበቃ ሁናት ተክልዬ ለነፍሴ/2/
ዳሞት ተናገረ የአንተን ሃዋርያነት
የወንጌል ገበሬ የጣኦታት ጠላት
ጸሎተኛው ቅዱስ አባ ተክለሃይማኖት
ክንፍ የተሸለምከው እንደ ሰማይ መላዕክት/2/
ብራናው ሲገለጥ ግድለ ተክለሐይማኖት
ከሰው ልጅ ልቦና ይወጣል አጋንንት
የቅዳሴው ዕጣን ሲወጣ ከዋሻው
ምድርን ይባርካል ጸሎተ ምህላው/2/
የኢትዮጵያን ምድር አረሰው በማስቀል
ጫጫጭው ፈራረሰ ተዘራበት ወንጌል
ትናንት የዘራኸው ዛሬ ለእኛ ሆኗል
አምላከ ተክልዬ ብለን ተሟጅነናል/2/
ከሱራፌል ተርታ ቆመህ በማጠን
ቅዱስ ቅዱስ ብለህ ስታመሰግን
ፀሎት ትሩፋትህ ምህላ ስግደትህ
ጾምህ ክንፍ አወጥቶ ሰማይ አደረሰህ/2/
ዛፉ ሲመነጠር አምላክ የተባለው
በቶሎሚ ሲፍር ትልቅ ሰው ነኝ ያለው
የተክልዬ ጸሎት ብዙ ምስጢሩ
ስድስት ክንፍ አወጣ ቢቆረጥ አንድ እግሩ/2/

## 450. እፁብ ድንቅ ነው

እፁብ ድንቅ ነው ስልጣኑ ክብሩ
የተክለሃይማኖት ገድሉ ታምሩ
ፈወስ አግኝተናል በእምነት ፀበሉ
ክቡር መንፈሱ ሳበው መንፈሴን
ለወጦልኛል የከፋት ገድሌን
ፀድቋል ማዘገቡ በምልጃው ዕፎት
ፀጋው በዝቶልኝ የተክለሃይማኖት
የገድሉ ቃሎች ስንኞች ወርደው
አቁመውኛል ህመሜ ሽረው
ከዕጣኑ ጭስ ጋራ ወጥቶ ፀሎቱ
በረከት ይዞት ታየኝ ምህረቱ
ባለመድህኒት ያጣው ህመሜ
ገድሉ ሲነበብ ቀለለ ሸክሜ
እረፍት አግኝቼ ደስታን ተነፈስኩ
አዲስ አካሌን ከደጁ ሰበሰኩ
ቅዱሱን እምነት ቤቱ ነስንሼ
ተነሳሁ በክብር ፀጋን አፍሼ
በእግሮቼ ፍኖት ልጁ ተራመድኩ
ገድል ታምሩን እየተሸከምኩ

## 451. ኢትዮጵያዊው ጻድቅ

ኢትዮጵያዊው ጻድቅ ማነው ብዬ ጠየኩ
በረከት ፈልጌ ልሳለመው ናፈኩ
ክብሩን ልመሰክር ተፈታ ምላሴ
ከደጁ ደርሼ ፍቅሩን በመቅመሴ

በኢትሳ ምድር ዘር ሆነህ በቅለህ
ተለይህ ለአምላክ ዓለምን ጥለህ
ደብረ ሊባኖስ ህያው ምስክር
ስለ አንተ ዝና ስለ አንተ ክበር
ተክለሃይማኖት ወዳጄ
ተባርኳል በአንተ ጓዳ ደጄ

አክባሪው አምላክ ስላከበረህ
ዛሬም ከእኛ ጋር በመንፈስ አለህ
እጅ እንነሳለን በትህትና
የጻድቅ ፀሎት ሀይል አላትና
ተክለሃይማኖት ፀሀይ
ፀጋ ይምጣልኝ ከሰማይ

ወደ ለምለም መስክ ስበኸ መራኸን
የቃሉን ወተት አጠጥተኸን
ያቀጣጠልከው የወንጌል ችቦ
የአምላክ አድርጓል ትውልዱን ስቦ
ተክለሃይማኖት ወዳጄ
ተባርኳል በአንተ ቤቴ ደጄ

ሰላሳ ስልሳ መቶ ያፈራህ
በደብረ አስቦ ቆህ በአንድ እግርህ
የመቶሎሚ መሻት ቀረና
የጌታ መንገድ ጥርጊያውም ቀና
ተክለሃይማኖት ወዳጄ
ተባርኳል በአንተ ጓዳ ደጄ

በኢትሳ ምድር ዘር ሆነህ በቅለህ
ተለይህ ለአምላክ ዓለም ጥለህ
ደብረ ሊባኖስ ህያው ምስክር
ስለአንተ ዝና ስለአንተ ክብር
ተክለሃይማኖት ወዳጄ
ተባርኳል በአንተ ጓዳ ደጄ

## 452. ተክለ ሀይማኖት

ተክለ ሀይማኖት ባህታዊ
ምድራዊ ሲሉህ ሰማያዊ
በአደባባዩ ተተክለሃል
ተክልዬ ሜልካሜን ፍሬ አፍርተሃል
ቃልኪዳን አለ የገነነ
ምህረት የሚያሰጥ የታመነ
በስምህ ወሃ አጠጥተን

ዋጋችን በዝቷል አባታችን
እኛም ሆነናል ልጆችህ
ሚርኮ አስቀርቶን ምግባርህ
በምልጃ ጸሎት ትሩፋት
ቤታችን ሞላ በረከት
ምህረት ይዘንባል ከሰማይ
በአንድ እግርህ ቆመህ ስትጸልይ
ብዙ ተጋደለህ አትርፈሃል
ያገለገልከው አከብሮሃል
ተሰባበሩ ጣኦታቱ
አምነው ሰገዱ መኳንንቱ
የበረታው ቃል ከአፍ ወጥቶ
የአምላክ አድርጎሃል ሁሉ ገዝቶ

## 453. ገድሉ ተአምራቱ

ገድሉ ታምራቱ እጅግ ብዙ ነው
ጣኦትን አዋርዶ የተሸለመው
የተዋህዶ ኮከብ ተክለሃዋርያ
አባ ተክለሃይማኖት ዘኢትዮጵያ
ዳግማዊ ዮሃንስ ጠፍር የታጠቀ
ንፅህ ባህታዊ ጠለት ያስጨነቀ
የፀጋ ዘአብ ፍሬ ዛፍ ሆኖ በቀለ
በደብረ ሊባኖስ መናኝ አስከተለ
ደካማ ማስሏቸው በአንድ እግሩ ቢያዩት
ባለ 6 ክንፉ ተክልዬ የእኔ አባት
እርሱ አንበሳ ነው ይነበብ ደብረ አስቦ
ሌጊዮን ሲዋረድ እፍረት ተከናንቦ
ከካህናት ማካከል ዕሩይ ነው ተክልዬ
መጣሁ ከገዳምህ ልሳለምህ ብዬ
ኢትዮጵያዊው ቅዱስ አባ ተክለሃይሞኖት
ወልድ ዋህድ ብለህ ምድሪቷን ቀደስካት
የባረከው ወሃ የረገጥከው ሜት
ገላህ ያረፈበት ሆኗል ፀበል እምነት
ኑና ተመልከቱ ድውያን ሲፈቱ
ይሰብካል ተክልዬ ዛሬም እንደ ጥንቱ

## 454. አባ አባ ተክለሀይማኖት

አባ አባ ተክለሀይሞኖት
አባ አባ ተክለሃይመኖት አበየ /2/
በለኒ በለኒ ወልድየ /2/

አባ አባ እንኳን ሰው ምድሪቱ
>> ጠም አያሳድርም
>> አምላክ ተክልዬ
>> ብዬ አፍሬ አላወቅም
>> ምድራዊ መልአክ ነህ
>> የኢትሣ አንበሳ
>> ለደብረ ሊባኖስ
>> እንተነህ ሞገሷ

>> ስምኒ ብያለሁ
>> ሳለህ በሰማይ
>> ከኪሩቤል ተርታ
>> ሆነህ ስትታይ
>> ስምህም ሲጠራ
>> ገድልህ ሲነገር
ዕፀብ ድንቅ ያሰኛል
>> የተሰጠህ ክብር

>> አባቴ እልሀለሁ
>> ልጄ ሆይ በለኝ
>> የአባትና የልጅ
>> ፍቅርህ ይፅናለኝ
>> ንፍሮ ወሃ ጠጥቼ
>> ተአምር አይቻለሁ
>> እባብና ጊንጠን
>> ተረማምጃለሁ

ዕለት በዕለት ሄጄ
ደጅ ስጠናው
ይሰማል ተክልዬ
ዛሬም ህያው ነው
እንቆቅልሽ ፈቶ
ደስ አሰኝቶኛል
የተክለሃይማኖት
በራኬው ደርሶኛል

## 455. ለተክለሃይማኖት ጻድቅ

ለተክለሃይማኖት ጻድቅ
መጠነ በዝህ ህማሙ
ትቄድሶ ደብረሊባኖስ ገዳሙ/2/

እስመ በውስቴታ ተገብር
ፍልሰተ ስጋሁ ወአጽሙ
ትቄድሶ ደብረሊባኖስ ገዳሙ/2/

እምነ አድባራት ኩሎን ዘተለዓለት በስሙ
ትቄድሶ ደብረሊባኖስ ገዳሙ/2/

ኢየሱስ ክርስቶስ እንተ ቀደሳ በደሙ
ትቄድሶ ደብረሊባኖስ ገዳሙ/2/

## 456. በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐወር እምኃይል ወስተ ኃይል
ካህን ካህን ወነቢይ (2) ዮሐንስ መጥምቅ
ትርጉም፡ ከኃይል ወደ ኃይል በመንፈስ ሄደ
(ይሄዳል) ካህንና ነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ

## 457. ወአንተኒ ህጻን

ወአንተኒ ህጻን ነቢየ ልዑል (2)
አርኩ ለመርዓዊ ትሰሚይ (2) ነቢየ ልዑል
ትርጉም፡ አንተ ህጻን የልዑል ነቢይ የሚሽራው
ክርስቶስ ማገድ ጠራጊ ትባላለህ (ትሰኛለህ)

## 458. እምሔሶ ለሄሮድስ

እምዚሶ ለሄሮድስ ይብላዕ ማዝሉሁ (2) እም
ያምትር ርዕሶ ለዮሐንስ
ዐቢይ ነቢይ (2) ሰባኬ ጥምቀት

ትርጉም፡ ሄሮድስ ታላቅ ነቢይ የሆነውንና የጥምቀት ሰባኪ የሆነውን የዮሐንስን አንገት ከሟየስቆርጥ ማላወን ቢበላ ይሻለው ነበር

## 459. ምን ሰማ ዮሀንስ

ምን ሰማህ ዮሀንስ በማህፀን ሳለህ/2/
ህፃን ሆነህ ነብይ ለፅድቅ የተጠራህ/2/
እንደ እንቦሳ ጥጃ ያዘለለህ ደስታ/2/
ምን አይነት ድምጽ ነው ምን አይነት ሰላምታ/2/
ከተፈጥሮ በላይ ያሰገደህ ክብር
እንዴት ቢገባህ ነው የአምላክ እናት ፍቅር/2/
ሌላ ድምፅ አልሰማም ከእንግዲህ በኋላ
ለወጦኛልና የሰላምታ ቃሏ/2/
በረሃ ያስገባህ ለብዙ ዘመናት
ምን ያለ ራዕይ እንዴት ያለ ብስራት/2/
እንደ አዲስ ምስጋና ስዕለቱ የተዋበ
ተደምጥ የማየወቅ ጭራሽ ያልታሰበ/2/
ከሴት ከተገኙ ከደቂቀ አዳም
ድንግል ስለሆነ በህይወቱ ፍፁም/2/
ከማህጸን ሳለ ተመርጦ በጌታ
ለማዳመጥ በቃ የኪዳን ሰላምታ/2/

## 460. የጫማውን ጠፍር

የጫማውን ጠፍር መፍታት የማልችል ነኝ/2/
ይመጣል ከኋላዬ እኔን የሚበልጠኝ
ይመጣል ጌታዬ እርሱ ነው የላከኝ
ይመጣል ጌታዬ እኔኝ የባረከኝ

ከአብ ጋር የነበር ዓለምን ሲፈጥር
ሁሉ በእርሱ ሆኖአል እኔ ነኝ ምስክር
በ 6 ወር እድሜ እኔ እበልጠዋለሁ
በማህፀን ሳለ ለእርሱ ሰግጃለሁ
በማህጸን ሳለሁ ለእርሱ ሰግጃለሁ

መንገዱን ለመጥረግ እኔ ተልኬአለሁ
እርሱ ሊሄድበት አስተካክላለሁ
ጠማማውም ይቅና ጎባጣውም ይቅና
ካልተስተካከለ መንገድ የለምና

የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው
የዋህ በግ ክርስቶስ በፊታችሁ ነው
ወደእርሱ ለማድረስ እሰብካሁ እንጂ
መንሹ በእጁ የሆነው እርሱ ነው ፈራጅ

የአዋ ነጋሪ ቃል በበረሃ አየለ
ወልደእጓለመህያው ይመጣል እያለ
መጥቶ ሲያጠምቃችሁ በእሳት በመንፈስ
ከአብ ጋር እኩል ነው ከመንፈስ ቅዱስ

## 461. እስጢፋኖስ

እስጠፋኖስ ሰማዕት ሊቀ ዲያቆናት በምዕመናን የተሾምክ/2/
የአምልክህን ትዕዛዝ በሥራ የፈፀምክ/2/

## 462. እስጢፋኖስ

በብዙ አገር የዞርክ
የጌታን ወንጌል ያስተማርክ
የድቁናን ሥራ በክብር የፈጸምክ
ክቡር ነህ/2/ እስጠፋኖስ ክቡር ነህ

## 463. ዘሳአል ወ ኬፋ

ዘሳኦል ወ ኬፋ/2/
አክሊለሙ/2/ ይኩነነ ተስፋ
ታማልደናለች/2/
ሚርያም/2/ ቤዛዊት ዓለም
ያማልዱናል/2/ መላዕክት/2/ ፃድቃን ሰማዕታት
ሚካኤል በሰይፉ ገብርኤል በፋና/2/
ያወጡናል የወጡናል ከሲኦል ጎዳና

## 464. ጳውሎስ አስተማረ

ጳውሎስ አስተማረ ቃለ ክርስቶስ/2/
ፈጽሞ ሳይፈራ ነገስታተ ነገስታተ ምድር/2/

## 465. መርቆርዮስ ኃያል

መርቆርዮስ ኃያል ማስተጋድል
በትዕግስቱ ዘፈጸመ ገድሉ

## 466. ቅዱስ ዮሴፍ

ቅዱስ ዮሴፍ አማለደን
ከመድሃኔአለም አስታረቀን
ሚገን ይቅር አለን/2/
አማኑኤል ታረቀን

## 467. ያሬድ ካህኑ ዘመረ

ያሬድ ካህኑ ዘመረ /2/
ዘመረ ያሬድ ዘመረ አምላኩን አመስገነ /2/
አርያም በማለት \'' ማህሌት ጀመረ \''
ዜማውን ከመልዕክት እያስጸባበረ
ምስጋና አቀረበ \'' በዜማ መሳሪያ \''
ፅናፅል አነሳ ከበሮ መቋሚያ
በግዕዝ በዕዝል \''
በአራራይ ዜማ \''
ከብሉይ ከአዲስ ምስጢር
እያስማማ
በዜማው ምልክት \'' የአምላክን
መከራ\''
የማስቀሉን ነገር የማዳኑን ስራ
ደሙ እየፈሰሰ \'' በጦር ተወግቶ \''

ሊቁ ማህሌታይ በመንፈስ ተቃኝቶ
በጥኡም ልሳኑ `‘’ በተሰጠው ፀጋ `‘’
ለንጉስ እግዚአብሔር ለአልፋ ኦሜጋ

ድጓ ፆመ ድጓ `‘’ ምእራፍ መዋሲት
`‘’
ምስጢር ተገልፆለት ከሰማይ
ማዕከት
የዜማ ማሰረት `‘’ ፈልፈለ ዝማሬ
`‘’
የኢትዮጵያ ኩራት የተዋህዶ ፍሬ

## 468. መሠረተ ዜማ

መሠረት ዜማ ወጠነ /2/ ያሬድ ካህኑን
ያሬድ/3/ ያሬድ ካህን ጥኡመ ልሳን

## 469. ነይ አርሴማ ቅድስት

ነይ አርሴማ ቅድስት
ነይ አርሴማ
ነይ አርሴማ ቅድስት ሰማእት
አርሴማ/2/ ነይ አርሴማ
አርሴማ ስልሽ

እንድታማልጅኝ
ከአምላክ ፈጣሪሽ
በደሌን ጭፃቀቴን
ልናዘዝልሽ
ምሪኝ አርሴማ ሆይ
እጆቼን ይዘሽ
ወልዲያ ስሪንቃ
ልምጣ ከደጅሽ

እንድታማልጂኝ
ከንጉስ ራማ
ትለምንሻለች
ነፍሴ ደጅሽ ቆማ
ወልዲያ ስሪንቃ
ሄዶ ያየሽማ
ቅዱሱ ዝናሽን
ገድልሽን የሰማ
ጸበልሽ ፈወስ ነው
እናቴ አርሴማ

በጉብዝና ወራት
ፈጣሪህን አስብ
ብሎ እንዳስተማረን
በመጽሃፈ መክብብ
ስለ ጌታ ኢየሱስ
ስለ ዓለም መድኃት
ስለተዋህዶ
ስለጸናች እምነት
መከራ ተቀበልሽ
በጉብዝናሽ ወራት

አርሴማ/2/ ቅድስት/

አርሴማ/2/ ቅድስት/2/
ምስክር ፅኑ ሰማዕት
አርሴማ/2/ ቅድስት
አርሴማ በፍቅሩ ተስበሽ
ዓለምን ንቀሽ
ሰማእት ልትሆኚ
ሄድሽ በፈቃድሽ
የአትኖሲያ ለቅሶ
ሆድሽን ሲያባባው
መስቀሉን አንግበሽ
ጌታን ተቀበልሽው

ሊይዙሽ ሲቀርቡ
ምድር ተንቀጥቅጠል
ልብስሽን ላይነኩ
ሁሉም ፈርተውሻል
ሚካኤል ገብርኤል
ከጌታ ተልከው
እረዱሽ አርሴማ
በዙሪያሽ ተገልጠው

በጥፊ ሲመታሽ
የንጉስ ወታደር
ተከፍታ ዋጠችው
እንደ ዳታን ምድር
አውሬ እንዲበላሽ
የፈጢኝ ታስረሽ
መጥቶ ሰገደለክሽ
እግርሽን ሳመሽ

ለጣኦት እንድትሰግጂ
በእሳት ሲያስፈራሩሽ
አማትበሽ በመስቀል
ተወርውረሽ ገባሽ
ሰማዕታት ሁሉ
ገቡ ተከትለው
የእምነትሽ ፅናት
እሳቱን አጠፋው

## 470. ለሃሪትነ ሰላማ

ለሀገሪትነ ሰላማ ኪያከ ተሃቀብ
አባ ኦ አባ /2/ ገብረመንፈስ ቅዱስ/2/ አባ

## 471.እንዘሰውር

እንዘስወር እምዔነ ይእዜሰ ክሱተ ኮነ /2/
ተአምሪ ወመንክረ ገብረ መድኃነ በቃና
ዘገሊላ ክብካበ ኮነ ማየ ረስየ ወይነ

**ትርጉም፡ –** ጌታችን መድኃኒታችን ከእኛ ተሰወሮ የነበረውን አሁን ተገለጠ በቃና ገሊላ ውሃውን ወይን ጠጅ በማድረግ ተአምራትን አደረገ

### 472. እኸ ሀዲገ ተሰአ

እኸ ሀዲገ ተሰአ እኸ ውተሰአተ ነገድ/2/
እኸ ሜከለ ባህር ቆመ ሜከለ ባህር/2/

### 473. ዮሐንስ አጥምቆ

የሐንስ አጥምቆ ለኢየሱስ/2/
በፈለገ ዮርዳኖስ/2/ ፈለገ ርዳኖስ

### 474. ጠዋትና ማታ

**ጠዋትና ማታ አርሴማ እያልኩኝ**
**በምልጃዋ ከፈተና ዳንኩኝ**

### 475. ሃሌ ሃሌ

ሃሌ ሃሌ
ሃሌ ሃሌ ሉያ /2/
ሰማዕት /2 አርሴማ ቅድስት

### 476. አርሴማ

አርሴማ/2 ቅድስት ሰማእት
ሞገስ አግኝተሻል በክርስቶስ ፊት
አርሴማ ተአምርሽ ልዩ ነው
አርሴማ ገድልሽ አስደናቂ
አርሴማ ስምሽ ብርሃን ነው
አርሴማ ማእዳ ፈንጣቂ

አርሴማ ስምሽን እየጠራ
አርሴማ ጠግቧል የተራበ
አርሴማ ምስኪኑም ዘመረ
አርሴማከአንቺ አልፎ መከራ

አርሴማ ፅኑ ነው ኪዳንሽ
አርሴማ የተሰጠሽ ከአምላክ
አርሴማ በአይኔ አይቻለሁ
አርሴማ ጠላት ሲንበረከክ

አርሴማ ዓለም ይስማው ዛሬ
አርሴማ ዜና ተጋድሎሽን
አርሴማ ይገረም ይደነቅ
አርሴማ ይመክር ዝናሽን

## የሠርግ መዝሙራት

### 477. ያስደስታል

ያስደስታል/3/ የእኛ እምነታችን
የኦርቶዶክስ ተዋህዶ የጋብቻ ስርዓታችን
ተፈፀመ/2/ ዛሬ ሰርጋችሁ
ምስጋና ይግባው እንላለን/2/ ቸር አምላካችሁ

### 478. ደስ አላት

ደስ አላት ቤ/ክ በጣም ደስ አላት/2/
ሙሽሪት ሙሽራው ልጆቿ/2/ በተክሊል በቁርባን ተዋሃዱላት

### 479. በቃና ዘገሊላ

በቃና ዘገሊላ/2/
ዘገሊላ ክብካበ ኮነ/2/

### 480. . መፅአ መርዓዊ

መፅዓ መርዓዊ ፍስሃ ለኩሉ/2/
በሰላም ፃኡ ተቀበሉ/2/

### 481. ዳዊት ይሴብህ

ዳዊት ይሴብህ ወይዜምር ዕዝራ/2/
እንዘይብሉ ሙሽሪት ሙሽራ/2/

### 482. ትዌድሶ

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ/2/
ወልድ እሁየ ቃልከ አዳም/2/

❖ **ሙሽሪት ሙሽራውን ልጅ ወንድሜ ሆይ ድምፁህ ያሚ ነው ትለዋለች**

### 483. መፅአ

መፅአ ዘመፅአ እምላዕሎ/2/
መርአዊ መፅአ/2/ ተቀበሉ ፃኡ ተቀበሉ/2/

### 484. ወአንተኒ

ወአንተኒ ህፃን ነቢየ ልዑል/2/
አርኩ ለመርዓዊ ትሰሚ/2/ ነቢየ ልዑል
**ትርጉም፡ – አንተም ልጅ /ነብይ/ የመርዓዊ ክርስቶስ ወዳጅ ትባለለህ**

### 485. ይደሰት ሙሽራው

ይደሰት ሙሽራው በስርዓተ ተክለል ሲያገባ እኽ
አሸበረቀ ደመቀ አጌጠ በሙሽራ አበባ/2/
በሶፓ ወደሙፍፀም እንዳዘዘው ወንጌሉ እኽ
በሙሽሪት ነው ያሚው/2/ ስርዓተ ተክሉ/

## 486. ያፅናችሁ

ያፅናችሁ በዚህ ጋብቻችሁ/2/
መድሃኔዓለም/2/ ይጠብቃችሁ/2/
ድንግል ማርያም/2/ ትጠብቃችሁ/2/

## 487. . መርዓዊ ሰማያዊ

ማርአዊ ሠማዊ/2/
ለእመ ገብረ በአለ/2/ እኽ/3/
ይኑሩ በሰላም/3/ ጸንተው ዘለዓለም
ደናግል ተነሱ ያዙ መብራቱን
ሙሽራው ደረሰ አጉል እንዳንሆን
ወንጌልን ይዘዋል ጎዳናቸው ያምራል
አላማው ሚልካም ነው እነርሱን
እንምሰል
የድካም ዋጋቸው/2/
ብርሃኑን ያበራል በሃይማኖታቸው

## 488. ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ሔር/2/
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም/2/
እናመሰግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ/2/
በሥጋ ወደሙ ልጆችሽ አንድ ሆነዋል ዛሬ/2/
በሥጋ ወደሙ በተክሊሉ የተሳሰረ/2/
በማግስተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ/4/
እሚቤታችን እናታችን ማርያም/2/
ከእነርሱ አትለይ ሁልጊዜ ለዘለዓለም/4/
- አዝ-
ግነዩ ለእግዚአብሔር እስሙሔር/2/
እስመ ለዓለም ምህረቱ እስመ ለዓለም

## 489. መጣ ሙሽራው

እልል በሉ መጣ ሙሽራው ደስ ይበለን
እግዚአብሔር አድርጓል ሚልካሙን ነገር
ለሁላችን
ዘይቱን ሞልቶ መብራቱም ይብራ -- መጣ
ሙሽራው
ተወዳጁ ሰው መጣ ሙሽራው--- ደስ
ይበለን
በፊቱ ቁሙ ቆነጃጅቱ --- መጣ
ሙሽራው
የፍቅር ግብዣው ደርሷል ሠዓቱ -- ደስ
ይበለን
በልዩ ግርማ ተወቧል ዛሬ ----መጣ
ሙሽራው
አዲስ ምስጋና ታላቅ ዝማሬ ---- ደስ
ይበለን
እንደወደደ አድርጓል ጌታ --- መጣ
ሙሽራው
ማን ይገልጸዋል የእርሱን ወለታ --- ደስ
ይበለን
በልጆቹ ቤት በክብር ነግሷል ---
መጣ ሙሽራው
በነገር ሁሉ ራስ ሆኗቸዋል ---
ደስ ይበለን
ይህን ያለውን በጊዜው ሰራ ----
መጣ ሙሽራው
ይሄው ቆመዋል በክብር ስፍራ --
ደስ ይበለን

## 490. ሙሽራዬ

ሙሽራዬ/4/
በእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ ሆነዋል ዛሬ
በእመብርሃን ምልጃ አንድ ሆነዋል ዛሬ
የተሰጣቸውን ማካለት ሳይሸሽጉ
በበረከት ፍሬ በቅተዋል ለሥርጉ
በቃሉ ተቀኝታ ተወዳ ነፍሳችሁ
አምረዋል ሙሽሮች ተክለል ተቀዳጅተው
ከሀገረ ሰላም ወደቀው ከመቅደሱ
በረከትን አፍሰው በክብር ተነሱ
በወንጌል ታሽተዋል ጣፍጠዋል በቃሉ
ሆነዋል ሙሽሮች የእግዚአብሔር አካሉ
በደም ተገንብቷል የቤታቸው መቃን
ታጥረዋል በፍቅሩ በማይደፈርሰው
ኪዳን
ወደ ማደሪቸው አቀና ንጉሱ
ጠርተውታልና በሥርጉ ሳይርሱ

## 491. ይትባረክ እንደ አብርሃም

ይትባረክ እንደ አብርሃም
ዘለዓለም/4/ይትባረክ እንደ አብርሃም
የአካል አንድነት // በቁርባን
ተሳስሯል //
ከዛሬ ጀምሮ // ሁለትነት ቀርቷል
//
ከአካኩ ተጣብቃ // ዘመናት የኖረች
//
ዘሚች በደስታ // አካሏን አገኘች
//
ብሩክ ነው ምንጣሩ // ጸጋ
የከበበው
የሙሽሮች ድንኳን // አምላክ
ያልተለየው //
እልል በሉላቸው // ዛሬ ነው
ሰርጋቸው //
የተሚጠበት // ሚልካም ጋብቻቸው
//

## 492. ሐመልማለ ወርቅ

ሐሚልማ/3/ ወርቅ
ልብሱ የኛ ሙሽራ
ሐሚልማ ወርቅ
በባበሉን ምድር ያልተፈተለ ነው
በቤተመቅደሱ ሰለብሶት ያየነው
በክብር ካባው ላይ ፀጋው ተደርቦ
ሞላቸው ሞገሱ በላያቸው አርፎ
የሙሽራው ጠረን ማዛው ይስባል

በቅብዓ ሜሮን በእጣኑ ከብሯል
ያንጸባርቃሉ እንደ አልማዘ ድንጋይ
በረከትን አፍሰው ከምህረት እጁ ላይ
በዚህ ዓለም ዕንቁ አልከበረም ዘርፉ
በፆም በፀሎት ነው የሚዊው ሚገፉ
የሰው ዕጅ አይደለም የተጠበበት
ከላይ የመጣ ነው ዕድፈት የሌለበት

## 493. ዮም ፍሰሀ ኮነ

ዮም ፍሰሀ ኮነ
በእንተ ሚዐዊት ለሚዐዊ
ቆሜል ማሰረቱ // በእምነት ተገንብቶ //
ብርሃን ይታያል // ቤታቸወን ሞልቶ //
ተባርኳል ሜዕዳቸው // ፅዋቸወም ሞሏቷል //
በድካም የዘሩት // ዛሬ ብዙ አፍርቷል
የወንጌልን አጥር // በዙሪያቸው ተክለው //
ቅጥራቸው ተከብሯል // ጠላት እናዳይቀርበው //
በስጋ ወደሙ // ተጣምሯል ሥጋቸው //
ምከዋል በቃሉ // ምንም ላይለያቸው //
በእምነት ሠረገላ // ተሳፍረው ደረሱ
በቅድስና ልብስ // ተሸሙው ሊነግሱ

## 494. ይህን ለአደረገ

ይህን ለአደረገ ሃሌ ሉያ በሉ
እግዚአብሔር ታማኝ ነው ሁል ጊዜ በቃሉ
ሜሸሪት ሜሸራው እንኳን ደስ አላችሁ
የያዕቆብ አምላክ ሞገስ ሆነላችሁ
ስንቱን ተራራ አልፈነዋል
በሰገነት ላይ አቁሞናል
እስቲ እንዘምር በደስታ
ሁሌ ታማኝ ነው የእኛ ጌታ
ከእኛ የሆነ ምንም የለም
ተማስገን ጌታ ለዘለዓለም
ሥራህ አበራ በምስጋና
በሜሸሮች ላይ እንደገና
የሚይሆን ማስሎ የታየን
በእግዚአብሔር ሆኖ ስላየን
እንደ አሳፍ ልጆች ተሰለፍን
ስሙን በቅኔ ለማማስገን
የተባረከ በመዓፉ
ቅኔን ያፈሳል ሁሌ በአፉ
ከመላዕክት ጋር አንድ ሆነናል
የእግዚአብሔር ሥራ ማስጦናል
ጋኑ ቢጎድል የወይን ጠጁ
ያስባል ጌታ ለወዳጁ
መናኛ ይወጣ ከቤታችን
አዲስ እንጠጣ እርሱን ይዘን
አቤንኤዘር ነው መዝሙራችን
እየረዳን ነው አምላካችን
ፊታችን በራ በደስታ
ወብት ሆኖናል የእኛ ጌታ

## 495. ደስ ይበለን

ደስ ይበለን ደስ ይበለን
አምላክ አለ መሃላችን
ምን ይከፈል ለዚህ ስራህ
ገናና ነው አምላክ ክብርህ
እልልታ ነው በሰሞዖት
በሜሸሮች ብሩህ መበራት
በእግዚአብሔር ፊት ተንበርክካችሁ
የክብር አክሊል ስለሰጣችሁ
የፍቅር ህይወት ይሁንላችሁ
ምሳሌ ነው ዛሬ ሰርጋችሁ
የዓለም ደስታ ሳይሚርካችሁ
በእግዚአብሔ ቤት ሆነ ሠርጋችሁ
ለዚህች ዕለት አደረሳችሁ
በአምላክ እቅፍ ሆነ ነፍሳችሁ
የዘለዓለም ሜሸሮች ናችሁ
ለመዓን ቀን የተጠራችሁ

## 496. ሙሽሮች

ሜሸሮች እንኳን ደስ ያላችሁ/2/
ለዚህች ቀን ይኸው ደረሳችሁ
በአምላክ ፊት እጅግ ከበራችሁ/2/
በእግዚአብሔር ቸርነት በሜልካም ፈቃዱ
በቅዱስ ቁርባኑ ዛሬ ተዋሃዱ/2/
በሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ
በመድሃኔዓለም ፊት ጋብቻ ፈጸሙ/2/
በቤተክርስቲያን በፈጣሪያቸው ፊት
ሁለቱም አንድ ሆኑ በዚች ቅድስት ዕለት/2/
አንድ የሚያደርጋቸው ተነበ ወንጌሉ
በካህኑ ማስቀል በረከት ታደሉ/2/
ፀንቶ የሚያዘልቅ የሚይለያያቸው
ክቡር ቃል ስላለ በመካከላቸው/2/
አስከ ሜጨረሻው አንድ አካል ሆነዋል
የአማኑኤል ሥጋ አስተሳስሯቸዋል/2/

## 497. በሰርጋችን ዕለት

በሠርጋችን ዕለት እንድትባርከን
ጌታ ጠርተንሃል በእምነት ሆነን
ከእናትህ ጋራ ከእማቤታችን
ከመላዕክት ጋ ና በስጋችን
ከሃዋሪያት ጋ ና በሰርጋችን
ከወዳጆችህ ጋ ና በሰርጋችን
በገሊላ ማንደር እንደተገኘህ
ና በእኛ ድንኳን ጌታ ስጠራህ
ስለእናተህ ብለህ ጌታችን እንዳትቀር
አንተ ነህ ክብራችን የቤታችን ፍቅር

ነይ ከልጅሽ ጋራ እማቤታችን
እንድታሟሉልን የጎደለውን
ንገሪው ለልጅሽ ባዶው እንዲሞላ
በርከት የእርሱ ነው ቤታችንን ይሙላ
በጎደለው ሁሉ እየጨመርሽልን
ቤታችንን ሁሉ ሙዬው እናታችን
ለአገልጋዮቹም ድንግል ንገሪያቸው
ጠርተን እናዳናፍር ጋኖቹን ይሙሏቸው

## 498. ሙሽራዬ

ሙሽራዬ/3/ አበባዬ/2/
ክብርት የምትሆን እህት አገኘኸ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለኽ
የእግዚአብሔር ፈቃዱ ለዚህ ካበቃችሁ
ቤታችሁ ይሙላ በፍቅር ያፅናችሁ
ወንድም አግኝተሻል የሚያስብልሽ
የእኛማ ሙሽራ እንኳን ደስ አለሽ
እግዚአብሔር ይመስገን እኛም ደስ
ብሎናል
በቤተክርስቲያን ሰርጋችሁ ውብ ሆኗል
እንደ ነፍስህ አርገህ እንድትወዳት
አደራ ሰጠንኽ በጌታችን ፊት
እንድታስበለት አንቺም ለአጋርሽ
አደራ ትላለች ወንጌል እናትሽ
በሥጋ ወደሙ ህይወት አግኝታችሁ
ፍሬአችሁም ይብዛ ይባረክ ጎጆአችሁ
አምላክ ያለበት ነው ይሔ ጋብቻችሁ
እስከ ሚጨረሻው ኑሩ ደስ ብሏችሁ

## 499. ሁለቱም አንድ ሆኑ

ሁለቱም አንድ ሆኑ ዛሬ/2/
በእግዚአብሔር በህያው ቃሉ ሁለቱም አንድ ሆኑ
ዛሬ
ወንድና ሴት አርጎ የፈጠራቸው
በኋላም በቃሉ አንድ አረጋቸው
እናትና አባቱን የአዳም ልጅ ይተዋል
ከሚስቱ ጋር በሰላም በአንድ ይተባበራል
ሁለቱም አንድ ሥጋ አብረው ይኖራሉ
ብሎ አስተምሮናል ጌታችን በቃሉ
አንድ ሥጋ ናቸው አይደሉም ሁለት
የባልና የሚስት ህይወት ወደፊት
እንግዲህ እግዚአብሔር ካጣመራቸው
በሆነ ው ባልሆነ ው ሰው አይለያቸው
ለወንዶቻችሁ ምሳሌ ሆናችሁ
በክርስትናው ፍቅር በዓለም ያኑራችሁ
ምንጣፋችሁ ቅዱስ መኝታችሁ ቅዱስ
ስለሆነ ላችሁ እንኳን ደስ አላችሁ
ዓለም እንዳደነቅ ሰይጣን እንዲያፍር
በሀዘን በደስታ ይኑራችሁ ፍቅር